አምቦ-ውኃውን ብቻ ሳይሆን አምባ-ጓሮውንም ተመልከት !

ምዕራፍ ሰባት

ኢትዮጵያችን የዳቦ ቅርጫት የምትሆነው ወላጆች ልጆቻቸውን ለሥራ ማነሳሳት ሲችሉ ነው።

እውነት ለመናገር ልጆቻችንን በጣም ስለምንወዳቸው ስራ እንዲሰሩ የምናዛቸውና ሥርዓትም እንዲይዙ የምንቀጣቸው ካደጉ በኃላ ነው። ግን በልጅነታቸው የእናታቸውን ጡት ሲጠቡ ጀምሮ በሥነ-ስርዓት እንዲጠቡ ከማድረግ ጀምሮ ሥርዓትንና ሥራን እንዲለምዱ ማድረግ እጅግ አስፈላጊ ነው። አንዳንድ ወላጆች እኔ እናቱ ወይም አባቱ እያለሁ እንዴት ልጄ በቤት ውስጥ ስራ ይሰራል ይሉና እንዲሁ እያበሉ እያጠጡ ብቻ ያሳድጋሉ። ካደጉ በኃላ ልጆች ወይ በስራ ወይ በትምህርት ከቤተሰብ ተለይተው ለብቻቸው ሄደው ሲኖሩ ያኔ ማጣፊያው ያጥራቸዋል። በዚህ ዙሪያ አንድ የማውቀው ታሪክ አለኝ፡

ሦስት የኮሌጅ ተማሪዎች የቤት ኪራይ እንዲቀልላቸው ለ3 አዋጥተው በመከፈል አንድ ላይ ቤት ተከራይተው ይኖሩ ነበር ታዲያ ከመሀከላቸው አንዱ ልጅ ካልሲውን ማጠብና አልጋውን ማንጠፍ አይችልም ነበርና ቤቱ በሽታና በቁንጫ ይቸገር ነበር አልጋውን እንደምንም ብሎ አንዴ ካነጠፈ ለወር ያህል ሳይራገፍ ዝም ብሎ ይቆያል። እንዳይበላሽበትም ጓደኞቸው ማታ ሲተኙ በራስጌ በኩል ቀስ ብሎ ይገባ ነበረ ጠዋት ሲነሳ ደግሞ በዚያው በራስጌ በኩል ቀስ ብሎ ተመዞ ይወጣ ነበር። ምክንየቱን በኋላ ጓደኞቹ አጥንተው እንደደረሱበት ልጁ ከልጅነቱ ጀምሮ ምንም ሥራ ሳይለምድ ነው ያደገው ቤተሰቦቹ ሳያውቁ የጠቀሙት

መስሏቸው " ልጃችን የስለት ልጅ ነውና ምን በወጣው ሥራ ይሠራል" እያሉ እንደ እንቁላል ይዘው ነው ያሳደጉት ይህ ግን በጎላ ልጆችን ይጐዳል።

እውነተኛ ወላጅ ለልጆቹ ሁለት ነገሮችን እንዲያወርስ በዚህ መጽሐፍ ላይ አበክሬ እናገራለሁ።

እግዚአብሔርን መፍራት እና

እውቀትን እንዲያወርስ

እነዚህ ሁለቱ አብረዋቸው ይኖራሉ። ከዚህ ውጭ የምናወርሳቸው ኃብት ግን አብሮ አይኖርምና ወላጆች እናስብበት። ምክንያቱም ቃሉ በምሳሌ 12:27 *"ለሰው የከበረ ኃብቱ ትጋቱ ነው"* ይላልና ልጆች ገና በልጅነት ከአቅማቸው ጋር በተመጣጠነ ሁኔታ ሥራ ይስሩ አልጋቸውን ያንጥፉ ልብሳቸውን ይጠቡ መኝታ ክፍላቸውን ያጽዱ ወጥ እንዴት እንደሚሰራ እንጀራ እንዴት እንደሚጋገር ይወቁ ። አንዳንድ የከተማ ሴት ልጆች የዶሮ ብልት 12 መሆኑን የሚያውቁት በቁጥር እንጂ በተግባር አሳዩ ቢባሉ የሚደነጋገሩ ይመስለኛልና ሥራ ከልጅነት ይልመዱ። ካጠፉም እያጠፉ እውቀት እንደሚያገኙ በመረዳት የሚከፈለውን የጊዜም ሆነ የገንዘብ ዋጋ መክፈል ያስፈልጋል።

አንድ ቀን ፈረንጆች ከሚኖሩበት ግቢ ውስጥ የመግባት እድል ገጠመኝና ገብቼ የፈረንጁ ልጅ የሚያደርገውን ሥራ አይቼ ተበሳጨሁ። የሚያደርገው ነገር ምንድነው ትልቅ ኘላስተር ወስዶ ከአንድ ግንድ ላይ ያያይዝና ከሁለት ሜትር በላይ

ከሚርቀው ከዚያኛው ግንድ ጋር ደግሞ ያያይዝና ቆም ብሎ ቀጥ ያለ መስመር መስራቱንና አለመስራቱን ያረጋግጣል፤ልክ ካልሆነ ልክ አይደለም ይልና ያንን ኘላስተር ጭምድድ አድርጐ መሬት ይጥልና እንደገና ሌላ መስመር በፕላስተሩ ይሠራል። አሁንም ልክ አይደለም ይልና አጨማዶ ይጥላል። ሶስቴ አራቴ ደጋግሞ ሲሰራ አየሁና ኘላስተሩ ለብዙ ሥራ ይሆን ነበረ በዩ ተበሳጨሁ። ብስጭቴንም ለመግለጽ ለአባቱ ልጁ በኘላስተሩ እንዲህ እየተጫወተ ከሚያበላሸው በኘላስተሩ ፋንታ ክር ቢሰጠው ብዩ አሳቤን አቀረብኩ። አባቱ ግን የመለሰልኝ መልስ እስከዛሬ ድረስ ወደፊትም ትምህርት የሆነኝ ሆኖ አገኘሁት። አባቱ እንዲህ አለኝ "ዛሬ እንዲህ ዋጋ ተከፍሎ ካልተማረ ነገ ሀገርን የሚቀይስ ጥሩ መሐንዲስ ሊወጣው አይችልም" አለኝ እውነት ነው ዛሬ የሚከፍለውን ዋጋ ሁሉ ከፍለን ለልጆቻችን ነገ ለራሳቸውና ለሀገር የሚጠቅሙ ዜጐችን እናፍራ ዛሬ በየቢሮው በየሀገሩ በየስራ ቦታው የሚያለምጡ ፍትህን በማጣመም በአቋራጭ ንዋይ ለማካበት የሚጥሩት ሁሉ ትናንትና በቤተሰብ ሳይሰሩ ያመለጡ የትናንትና ማሙሾት ናቸው። ስለዚህ እያጠፉም ቢሆን እውቀት እንዲገበዩ ጤናማ የሆነ ሥነ ምግባርን ተምረው እንዲያድጉ ቤተሰቦች እንትጋ። ቤተሰብ የሀገር መሠረት ነውና።

"ኢትዮጵያ ብዙ ሀፃናትና በርካታ ወጣቶች ያሉባት ሀገር ናት። እነዚህን ወጣቶች የሚያሳድጉ ወላጆች፣ አካባቢዎች፣ ትምህርት ቤቶች፣ ፖሊሲ አውጪዎችና መሪዎች ባጠቃላይ ሥራ ፈጣሪዎችን የማብዛት ግዴታ አለባቸው። ልጆች ትልልቅ ራዕይና አላማ እንዲይዙ ብዙ ችሎታና ሙያ እንዲኖራቸው ከሁሉም በላይ ወላጆች ኃላፊነት አለባቸው። በሁሉም

መስፈርቶች እያደገ የሚሄድ የቤተሰብ ኃላፊ እንደሆኑ ሲረዱ፣ ውስጣቸውን እየመረመሩ የቤተሰባቸውን መልካም ምሳሌነት / Role Model/ መከተል ሲችሉ ልጆች ከወላጆቻቸው የበለጠ ባለራዕይ ይሆናሉ። ህይወት የተለያዩ አማራጮች እንዳሏት ልጆቻቸውን ሲያስተምሯቸው፣ በሂደት የእነሱ ህይወት ከእለት ወደ እለት ለውጥ እያመጣ ሲሄድ፣ በየቤተሰቡ ያለ አንድ ሁለት ሰው የራስ የሚለው ሥራ ሲፈጥር፣ ተነሳሽነት ያድጋል። ልምድ ያካበቱ ወላጆች ለልጆቻቸው ዩኒቨርስቲዎች ናቸውና።

አሁን እንደሚታየው ብዙ ወላጆች በጣም ውስን የሆነ ህልምና ራዕይ አላቸው። የሚያጋጥሙአቸውን ችግሮች ሁሉ ከቤተሰብ አባላትና ከልጆች መኖር አለመኖር ጋር የሚያይዙ አሉ። በመሠረቱ ህፃናት ወላጆቻቸውን አስገድደው የተወለዱ አይደሉም። ህፃናትን የምንወልዳቸው እኛ ነን። በየትኞቹም ኃላፊነቶች ባብዛኛው ተጠያቂዎቹ እኛ ወላጆች ነን። ከምንጠቀምበት በላይ ገቢ ለመፍጠር የምንንቀሳቀስ ወላጆች ስንበዛ፣ በየቤቱ ያለ ድህነት ቀስ በቀስ ይጠፋል። ኢትዮጵያ የምታድገው እያንዳንዱ ቤተሰብ የተሻለ ደረጃ ሲደርስ ነው።

በጥቂቶች የኢኮኖሚ ነፃ መውጣት ብዙ ሰው ጥሩ ኑሮ መኖር አይችልም። የአስተሳሰብ ድህነትን የሚያወርሱት ልጅ ባለፀጋ አይሆንም። ጥሩ ኑሮ የአዕምሮ፣ የዓይንና የጆሮ፣ የህያው ዓለም መመቸት ደስታና እርካታ ማግኘት ነው። ብዙ ወላጆች አስሮ የያዛቸው የአስተሳሰብ ድህነታቸው ነው። የተለወጠ አስተሳሰብ ይዘን ሥንሠራ ሩጫችንን የሚያዩ ልጆች ትምህርት ከቤታቸው ያገኛሉ። እልህ ወኔ፣ ጥረት የሚያዩ ልጆች ለትልቅ ውድድር ይነሳሳሉ። ትልቅ ችግር ቢፈጠርባቸው እንኳ በራስ የመፍታትን

ወኔ ይዘው ያድጋሉ። ስለዚህ የመጀመሪያው ለሥራ (Entrepreneurial) ጥሬ ኃብት ዕድገት ትልቁን ሚና የሚጫወተው ቤተሰብ ነው። በየትኛውም አቅጣጫ ባለው የህይወት ጉዞ ተነሳሽነት ሲያድግ ራሳቸውን የሚያሳድጉ፣ ለተሻለ እድገት የሚበቁ ሀገር ተረካቢ ዜጐችን ማፍራት ይቻላል።

እዚህ ላይ ሳይነሳ መታለፍ የሌለበት ጉዳይ፣ ብዙ ወላጆች የምንጨነቀው ትንሽን ገቢ በየወሩ እንዴት አብቃቅተን መኖር እንደምንችል ነው። የተሻለ ገቢ ለመፍጠር በመፍጨርጨር ፋንታ፣ በየወሩ የምናገኘውን ገንዘብ ለማብቃቃት እንደክማለን። ገንዘብን ለፍጆታ ለማብቃቃት የምናደረገው ጥረት ሕይወታችንን ብዙም አይቀይረውም። ያልታዩ የሥራና የዕድገት አጋጣሚዎችን ማፈላለግ ግድ ይሆናል። ይህ ካልሆነ አልሟላ ያለ ህይወት ለማሟላት አለመቻልና ተስፋ መቁረጥ ይከተላል። ያኔ ቤተሰብ ተስፋ የቆረጡ ልጆች የምናሳድግበት ባዶ ቤት ይሆናል።

ከዚህ ወጥተን ኢትዮጵያ ብዙ የሥራ ፈጠራ (Entrepreneurs) እንዲኖሯት ለማድረግ ቀደም ብሎ ለመጥቀስ እንደተሞከረው በእያንዳንዱ ቤተሰብ ቢያንስ አንድ የራሱ የሆነ የሥራ ችሎታ ያለው የቤተሰብ አባል ሊኖር ይገባል።[12]

አንድ ወቅት የጋብቻ አማካሪነት Marriage counseling ስልጠና ስንወስድ አንድ የዩኒቨርስቲ ሌክቸረር የቤተሰብን የሥራ ሁኔታ አስመልክተው ሲናገሩ "በኢትዮጵያ ውስጥ በአንድ ከሚኖሩ ቤት ስድስት ሰዎች ውስጥ ትጉ ሠራተኞች ሁለቱ

[12] ኢንተርፐረነርሺፕ በዶ/ር ወሮታው በዛብህ ገጽ 109-110 1998 ዓ.ም

ናቸው አራቱ ጡረተኖች እንደሆኑ በጥናት ታውቋል "ብለዋል ምክንያቱ ምንድን ነው፤ የቤተሰብ ኃላፊዎች አራቱን ሰዎች ለስራ አለማነሳሳታቸው ወይም ከልጅነት ጀምሮ በጥሩ የሥራ ባህል አለማደጋቸው ሊሆን ይችላል።አንዳንድ ጊዜ እንደምናየው ልጆች ለትምህርና ለሥራ ብዙ የማይጓጉት ደግሞ የአባዬና የእማዬ ኃብት ንብረት አለ እርሱን እንወርሳለን ምን አደከመን በሚል አጓጉል ተስፋ ተወርሰው ሊሆን ይችላል። ይህንንም አመለካከት ማስተካከል ያለበት ወላጅ ነው።፤በተጨማሪም ወላጅ ብቻ ሳይሆን መንግስትም ልጆች ሥራ እንዲወዱና እንዲለምዱ ገና ከልጅነታቸው ጀምሮ እንደየ ዕድሜአቸው በትምህርት ሚኒስቴር ካሪኩለም ውስጥ ስለ ሥራ ነድፎ ሊያስተምራቸው ይገባል። ደግሞ ሥራ እንዲጠሉ የሚያደርግ ገና በልጅነታቸው የሕፃናት የጉልበት ብዝበዛ ሲደርስባቸው አሁን ከሚያደርገው የበለጠ ጠበቃቸው ሆኖ ሊሟገትላቸው ይገባል።ህዝቡም የህጻናትን መብት ሊጠብቅ ይገባል።

"ስንቶቻችን ስለ ህጻናት መብቶች መሰረታዊ ግንዛቤ አለን? የህጻናት መብቶች ጉዳይ ሲነሳ ሁልጊዜ በቅድሚያ የሚታወሰው በኢትዮጵያ መንግስት ተገቢውን ትኩረት ተሰጥቶት ህዳር ወር 1984 ዓ.ም ጸድቆ በአዋጅ ቁጥር 10/1984 ዓ.ም የወጣውና የሕጻናት መብቶች ድንጋጌ ሰነድ ነው። ይህ ሰነድ የሕጻናት መብቶች ዙሪያ በርካታ ጉዳዮችን የያዘ ቢሆንም በዚሁ ክፍል ግን መሰረታዊና ዋና ዋናዎቹን ብቻ ለግንዛቤ ያህል ለመዳሰስ ተሞክሯል። ከዚህም በላይ የህጎች ሁሉ የበላይ ህግ በሆነው የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዶሞክራሲያዊ ሪፖብሊክ ሕገ መንግስት በአንቀጽ 36 ላይ የህጻናትን ሁለንተናዊ ዕድገት በሚያስጠብቅ መልኩ ተደንግጓል። በዚህም መሰረት በሕገመንግስቱ አንቀጽ 36

ንዑስ አንቀጽ 1 ስለ ህጻናት መብት እንዲህ ሲል ጠቅሶታል። ማንኛውን ሕጻን የሚከተሉት መብቶች አሉት፤

በህይወት የመኖር፣

ስምና ዜግነት የማግኘት፣

ወላጆቹን የማወቅ የእነርሱንም ጥበቃና እንክብካቤ የማግኘት፣

ጉልበቱን ከሚበዘብዙ ልማዶች የመጠበቅ፣ በትምህርቱ በጤናው

በደህንነቱ ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ስራዎችን እንዲሰራ ያለመገደድ ወይም ከመስት የመጠበቅ፣

በትምህርት ቤቶች በህፃናት ማሳደጊያ ተቋሞች ውስጥ በአካሉ

ከሚፈጸም ወይም ጭካኔያዊና ኢሰብአዊ ከሆነ ቅጣት ነጻ መሆንና የመጠበቅ መብት አሉት/አላት።

ስለሆነም ከላይ በቀረበው አንቀጽ መሠረት ሕፃናትን ለጉልበት ብዝበዛ መዳረግ ማለት በህገመንግስቱ ላይ የተቀመጠውን የሕፃናት መብት መጣስ መሆኑን መረዳት ይኖርብናል።[13]

ያን ጊዜ ጥሩ ሀገር ተረካቢ ዜጋ እናገኛለን፤ ታዲያ ነገ የኢትዮጵያችን የዳቦ ቅርጫ ውስጥ መግባቷ ቀ`ቶ የዳቦ ቅርጫት ሆና ትኖራለችም።

[13] ጉልበት እንደዋዛ በጎጻናት የጉልበት ብዝበዛ ዙሪያ ሕጻናትን ወላጆችንና ማህበረሰብን ለማስተማር የተዘጋጀ መመሪያ ገጽ 48 1997 ዓ.ም

በነገራችን ላይ ኢትዮጵያችን የዳቦ ቅርጫት እንዳትሆን እንቅፋት የሆነባት ወላጆች ልጆቻቸውን ለሥራ አለማነሳሳታቸው ብቻ ሳይሆን ቤተክርስቲያንም ምዕመናኗን ለሥራ አለማነሳሳቷ ጭምር ነው።ታዲያ ቤተክርስትያን ምዕመናኗን ለሥራ እንድታነሳሳ ምን እናድርግ?

ወንጌልን እንጂ ወንጀልን አትሥሩ !

ምዕራፍ ስምንት

ኢትዮጵያችን የዳቦ ቅርጫት የምትሆነው ቤተክርስቲያን ምዕመናኗን ለስራ ስታነሣሣ ነው

ሥራ መሥራት ክብር ነው። ዘፀአት 34:21 እንዲህ የሚል ትዕዛዝ ሥራን በተመለከተ እንደተሰጠ እናያለን። ስድስት ቀን ትሰራለህ በሰባተኛውም ቀን ታርፋለህ በምታርሥበትና በምታጭድበት ዘመን ታርፋለህ።

ከዚህ የምንገነዘበው በሳምንት አንድ ቀን ስለማረፍ ነው። ምክንያቱም ስድስት ቀን ትሰራለህ ይላልና ይህ ትዕዛዝ ነው። የምርጫ ጉዳይ አይደለም። እያንዳንዱ ሰው ቤተሰቡን ለኑሮ የሚያግዝ ሥራ መሥራት ይኖርበታል። በምሳሌ 6:6-8 እግዚአብሔር ጉንዳኖች ለሥራ ያላቸውን ታታሪነት ለምግብ አሰባሰብ የሚያደርጉትን እንድንመለከት ያዘናል። ስለሆነም ሥራ የሕይወት ጠቃሚ ከፍል አንዱ እንደሆነ ያስረዳናል።ለአይሁዳዊ ሥራ እጅግ ጠቃሚ ጉዳይ ነው። ሥራ የሕይወት ጠቃሚና አስፈላጊነት ያለው ተግባራዊ እንቅስቃሴ ነው። አይሁዶች አንድ አባባል አላቸው ሥራን አስመልክቶ፡- " ልጁን አንድ የሥራ መስክ የማያሳይና የማያስተምር ወላጅ በአንፃሩ ሥርቆትን ያስተምረዋል።" በአይሁድ መምህር /ራባይ/ የሆነ ሰው በኮሌጅ ትምህርት እንደሚሰጥ ኘሮፌሰር ይቆጠራል ሆኖም ለሚያስተምረው ትምህርት አንድ ሳንቲም እንኳን አይወስድም። እርሱ ራሱ የራሱን ኑሮ ለመደገፍ በእጆቹ ይሰራል። ስለሆነም ልብስ ሰፊዎች ጫማ ሰፊዎች /ሰሪዎች/

ፀጉር አስተካካዮች ዳቦ ጋጋሪዎች ሙዚቃ ወይም ቲያትር ሰራተኞች ነበሩ። ሥራ ለአይሁድ ሕይወት ነው።

አዲስ ኪዳን ስለ ሥራ የተብራራና ጥልቀት ያለው መግለጫ ባይሰጥም ሰዎች ያላለፉበት ከሆነ በላተኛነታቸውን ይኮንናል። እንዲያውም ጳውሎስ "ሊሰራ የማይወድ አይብላ" ሲል ነገሩን ጠበቅ አድርጉታል። ሰው ለመብላት የሚሆነውን መብት ያለሥጋት ሊጠቀምበት የሚችለው በአቅሙ ተፈላጊ ሥራ ያከናወነ እንደሆነ ብቻ ነው። በተሰሎንቄ የነበሩ አማኞች ስለምጽአት ከነበራቸው የተዛባ ግንዛቤ የተነሳ ክርስቶስ በቅጽበት ይመጣል የሚል እምነት ስለነበራቸው በሥራ ላይ ትኩረት አላደረጉም ነበር። ይሁን እንጂ የጠበቁት ጌታ እነርሱ በጠበቁት ጊዜ ባለመምጣቱ ረሃባቸውን ለማስታገስ ምግብ ያሰናዱ ሰዎች ቤተ እየገቡ ይመገቡ ስለነበር በአንደንዶች ዘንድ ውዝግብ ተነስቶ ነበር። ጳውሎስም ሳይሰሩ እየቀላወጡ ለመኖር የፈለጉትን ሰዎች አጥብቆ ለመኮነን በዚህች ከተማ ሲኖር ያሳየቸውን ምሳሌነት እንዲህ ሲል አስታወቀ....."1ኛተሰ 2:9 ድካማችንና ጥረታችን ትዝ ይላችኃልና ከእናንተ በአንዱ እንኳ እንዳንከብድበት ሌሊትና ቀን እየሰራን የእግዚአብሔርን ወንጌል ለእናንተ ሰበክን።" ጳውሎስም ሥራን በተመለከተ በሰጠው ትምህርት እያንዳንዱ ሰው በራሱ ላይ ብቻ ያነጣጠረ ስግብግብነት የሚነዳው በእኔነት ላይ ብቻ ያማከለ ልፋትን ኮንኖ ይልቁንም አማኝ የራሱን መሰረታዊ ፍላጐት ለማሟላት በገዛ እጁ መልፋት ይኖርበታል ሲል አስተማረ። ግሪካውያን ልፋት ያለበትን በእጅ የሚሰራ ሥራ በዘመኑ በባርነት ቀንበር ስር እያማቀቁ ለሌሎች በሎሌነት ለማደር የተሰጡ ሰዎች ሥራ ነው ብለው ያስቡ ስለነበር፤ ሰርቶ

ከመበላት ይልቅ በሌሎች ላይ ጥገኛ ሆነው መኖርን መርጠው ነበር።

ከዚህ ስርዓት አልባ ኑሯአቸው የተነሳ ሐዋርያው በገዛ እጃችሁ ሥሩ.... /1ኛ ተሰ 4:11/ የሚል ጠበቅ ያለ መመሪያ ሰጠ።

ስንፍናንና ጥገኝነትን የኑነነው ጳውሎስ አማኝ በራሱ ላይ ካማከለ ኑሮ ፀድቶ በሌላው ትከሻ ሸክም ከመሆን ራሱን መጠበቅ እንዳለበት ካስገነዘበ በኋላ የአማኙ የሥራ ትኩረት ለሌሎች ለማካፈል መትጋትን ይጨምራል ብሎአል። በኤፌ 4:28 "....ለተቸገሩት የሚያካፍለው እንዲኖረው በገዛ እጆቹ በጐ የሆነውን እየሰራ ለማግኘት ይድከም ከሚለው የጳውሎስ አገላለጽ እንደምንረዳው የአማኙ ለሥራ ያለው ግብ እኔ ለእኔ ብቻ ሳይሆን ከቻለና ከሆነለት ሌላውንም የሚጨምር መሆኑን ነው። ለክርስቶስ ራሳቸውን የሰጡ አማኞች ከመስመር የወጣ ስግብግብነትና ስስትን ከማስተናገድ ይልቅ እየሰሩ ለሌሎች መትረፍ አይነተኛ መለያቸው ነው። /የሐዋ 20/ በጳውሎስ አገልግሎት ይህንን ለማድረግ የሚያስችል የተለየ ትጋት ይስተዋል ነበር።

ጳውሎስ ለኤፌሶን አማኞች በሰጠው ምክር እንደምንመለከተው "..... ከሚቀበል ይልቅ የሚሰጥ ብፁዕ ነው እንዳለ የጌታን የኢየሱስ ክርስቶስ ቃል እንዲያስቡ....." /የሐዋ 20:35/ ከሌላው ከመጠበቅ ይልቅ ሌሎችን ለመርዳት መሰናዳት ከራስ የሚተርፍ ትጋትን እንዳደፋፈረ እንመለከታለን። ጳውሎስ ይህንን ሲናገር ጌታ ኢየሱስ በምድር የሰጠው አገልግሎት ወደ

ሕሊናው የመጣ ይመስላል። ጌታ ኢየሱስ በአናጢነት ሥራ ተሰማርቶ /ማቴ 13:55/ ወላጆቹን ይደግፍ እንደነበር ወንጌላት በተለያዩ ሥፍራዎች ይተርካሉ። ምንም እንኳ ትንሹን በማበርከት ተአምር የሚሰራ ጌታ ቢሆንም ሰርቶ መኖርን በተግባራዊ ሕይወቱ ስላሳየ የእርሱን ፈለግ ሊከተሉ የሚወዱ በሙሉ የሚጓዙበትን ጉዳና አመልክቷል።

ለዚህም ነው ከብዙ ዘመን በኋላ የራስ ምሳሌነትና ለሌላው የማካፈልን ጥበብ ከኢየሱስ መማሩን በመግለጽ በተግባር የሥራን ክቡርነት ለኤፎሶን አማኞች ያስገነዘበው። እንደ አገልጋይ ሌሎች እሱን የመደገፍ ኃላፊነት እንዳለባቸው ቢያውቅም የማንም ሸክም ሳይሆን ይልቁንም ለሚጐድላቸው በማካፈል አዲስ ኪዳናዊ መርህ አስተምሯል /የሐዋ 20:33-38/

ለቤተክርስቲያንና ለእግዚአብሔር ሥራ ጠቃሚ አስተዋጽኦ የደረጉት ስመ ጥሩዎች ባልና ሚስት አቂላና ጵርስቅላ ድንኳን በመስፋት ሥራ ላይ ተሰማርተው ራሳቸውንና የእግዚአብሔርን ሥራ ይደግፉ ነበር። በአዲስ ኪዳን ያየናቸውን የሚበዙ ትጉ ቅዱሳን ለሥራ የተጋ ማንነት ነበራቸው /የሐዋ 18:1-3/ በዚህ ዘመን የምንኖረው ጌታን እንወዳለን፣ ፈለጉን እንከተላለን የምንል ሁሉ አቋማችን ከእነርሱ የተለየ ሊሆን አይገባም። ለዚህም ነው ጳውሎስ "ለሥራ ከመትጋት አትለግሙ የሚል መመሪያን ለሮሜ አማንያን የሰጠው /ሮሜ 12:11/።

በአዲስ ኪዳን ውስጥ ሰዎች በየትኛውም መስመር ተሰማርተው የተሳካላቸው ሰራተኞች እንዲሆኑ የሚያደርጉትን ለጌታ እንደሚያደረጉት እንዲገነዘቡ ለሥራ ጥሩ አመለካከት

እንዲኖራቸው ያደፋፍራል። ጳውሎስ "የምታደርጉትን ሁሉ በትጋት አድርጉት የሚል ምክር ይመክራቸዋል። ቆላ 3፡13። የመከራቸው የቆላሲያስ አማኞች ለሌላው ሰው በሌሎች ያደሩ ነበሩ። አሠሪውም ሆነ ሰራተኛው ቅንነትና ንጽህና በተላበሰ መንገድ የዕለት ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ ጳውሎስ ጠንከር ያለ ማሳሰቢያ ይሰጣል።

ጴጥሮስም ከአሰሪዎቻቸው ጋር ችግር ለነበረባቸው በሎሌነት ሥራ ይተዳደሩ ለነበሩ ሰዎች ሥራ የሚመራበትን መንፈስና ክርስቲያናዊ አመለካከት ሲገልጽላቸው እንመለከታለን /1ኛ ጴጥ 2፡18/። መጽሐፍ ቅዱስን በስነ ጽሁፍና ታሪካዊው አውድ የማይተረጉሙት ሰዎች በተለይም የኮምኒዝም አቀንቃኞች ለዚህ የተለየ ትርጉም በመስጠት መጽሐፍ ቅዱስን ኮንነዋል። ይሁን እንጂ የክፍሉ መሰረታዊ መልዕክት ሥራችሁን በሰላማዊ መንገድ፣ በመታዘዝ መንፈስ አከናውኑ የሚል ነው። ያዕቆብ ግፈኝነትን በመኮነን ለልፋት ተመጣጣኝ ክፍያን በመጠየቅ በጭካኔ የሌሎችን ላብ የሰበሰቡትን ባለጠጎች ያስጠነቅቃል። ይህ ማስጠንቀቂያ ለጉልበት ተመጣጣኝ ክፍያ የሚያስገነዝብ ቢሆንም ያለአግባብ ሌላውን ማሰራት ያልተገባ መሆኑን ያስገነዝባል።

ጳውሎስ ለቲቶ በጻፈው መልዕክቱ በቀርጤስ ሰዎች የሥራ ፈትነት መንፈስ በአማኞች ላይ እንዳይገባ ጠንከር ያለ ማሳሰቢያ ሰጥቷል። በአዲሰ ኪዳን ውስጥ /1/ ሰርቶ መብላት /2/ ሰርቶ ራስን መቻል/3/ ሰርቶ ለቤተሰቦች ተገቢውን እንክብካቤ መስጠት /4/ ሰርቶ ለሌሎች ለሚጉድላቸው ማካፈል/5/ በሥራ ትጋት ማሳየት በተደጋጋሚ ተጠቅሰው የምናያቸው ክስተቶች

ናቸው።

በአዲስ ኪዳን ሥራ ለማንኛውም ሰው ተገቢ እንደሆነ ያመለክታል። በተጨማሪም ግለሰቡ ስለሥራ ስለሰሪው ሊኖረው ስለሚገባ የቀና አመለካከትም ይዘግባል። እንዲያውም ሥራ ብቻ ሳይሆን አንድ ሰራተኛ ሥራውን በሚገባ ስለመሥራቱም የሚያጠቃልል ነው። ከዚህ በታች ቁልፍ የሆኑ የአዲስ ኪዳንን የሥራ መርሆችን እንመልከት።

ትክክለኛ ፍትሐዊና ቅን አሰሪ ሁን !

ጳውሎስ አሰሪዎችን በተመለከተ እንዲህ ይመክራቸዋል፦

"ጌቶች ሆይ /አሰሪዎች ሆይ/ እናንተ ደግሞ በሰማይ ጌታ እንዳላችሁ ታውቃላችሁና ለባሪያዎቻችሁ በጽድቅና በቅንነት አድርጉላቸው"። /ቆላስ 4፡1/

አሰሪ ከሆንን እጅግ የከበደ ኃላፊነት አለብን። ይኸውም ከበታቻችን ለሚሰሩ ሰራተኞች ትክክለኛ /ፍትሐዊና ቅን ሰዎች ልንሆንላቸው ይገባል። የሚገባቸውን ደመወዝ በትክክለኛ ጊዜና በወቅቱ ልንከፍላቸው ይገባል። /ዘሌ 19፡13/ እነርሱን የሚያሳስብ ሁኔታ እኛንም ሊያሳስበን ይገባል። በየጊዜው መብታቸውን የሆነውን ደንቡ የሚፈቅድላቸውን ለማድረግ በተጠየቅን ጊዜ ወደ ኋላ ማለት አይኖርብንም።

ዛሬም በቤተክርስቲያን እንዲሁ ሊሆን ይገባል።በዓለም ላይ ተሰሚነትና ተቀባይነት ካላቸው ተቋማት ውስጥ ቤተክርስቲያን የመጀመሪያውን ደረጃ ትወስዳለች። ስለዚህ ሰዎችን ወደ በጐ የመመለስ በጐ የማሰብና የማድረግም ትምህርት እንዲያገኙ ማድረግ ከዚህ ቀደሙ በበለጠ ይጠበቅባታል። ሁልጊዜ ሰዎች

ሲፀልዩ " ላጡት አስብላቸው " የሚል ልማዳዊ ፀሎት ብቻ ከሚፀልዩ ላጡትም እንዲአስብላቸው እኔንም እርዳኝ ብለው ለሥራ ተነስተው ራሳቸውንም ሌሎችንም እንዲደግፉ ምዕመናኗን ለስራ ልታነሣሣ ይገባል።

በዓመት ውስጥ በየአብያተክርስቲያናቱ ቢያንስ ሁለት ወይም ሪስት ኮንፈረንስ ባብዛኛው ይኖራል፤ ግን አንድ ክፍለጊዜ እንኳን ስለ መልካም የሥራ የሥነ ምግባር ሳይሰበክ እንዲሁ በሌሎች ጉዳዮች ብቻ ጊዜው ያልቃል ለምን? ትኩረት ስላልተሰጠ።

ዓለምን እንድትለውጥ ቤተክርስቲያን ተጠርታለች። በዓለም ያለ ፍጥረት ሁሉ የሰውን ልጆች መገለጥ በጥብቅና በጉጉት ይጠብቃል በሮሜ 8:19 <u>"የፍጥረት ናፍቆት የእግዚአብሔርን ልጆች መገለጥ ይጠባበቃል።"</u>ሜዳው ሸንተረሩ የእግዚአብሔርን ልጆች መገለጥ እየተጠባበቀ ተገለጡና አሳምሩን ይላል። ለዚህ ደግሞ በኢትዮጲያም ሆነ በአፍሪካ ተወዳጅነትንና ተቀባይነትን ያገኘው የእግዚአብሔርን ቃል በማስተማርና በማስታጠቅ ለአገር ውስጥም ሆነ ለውጭ አገር አገልጋዮችን ያፈራው በአዲስ አበባ ሳር ቤት አካባቢ የሚገኘው **ኢቫንጀሊካል ቲዎሎጂካል ኮሌጅ / ኢቲሲ / ምስክር ነው**። አሁን የህንጻው ጣሪያ ሳይቀር በአከባቢው ለሚሰሩ ህንጻወች እንኳን ምሳሌ የሆነው መንፈሳዊ ኮሌጅ እንዲህ አምሮና ተውቦ ከመሰራቱ በፊት የቆሻሻ መጣያ እንደነበረ አውቃለሁ። ነገር ግን የእግዚአብሔር ልጆች ተገለጡበትና አሁን በውበቱም ሆነ በሥራው ዓለምን የሚስብ ሆኖ አረፈው።ስለዚህ ዛሬም ሰዎች ሁሉ ለስራ እንዲገለጡና አለምን እንዲያበጃጁ ከተፈለገ ቤተክርስትያን ምዕመናኖቿን ለስራ ማነሳሳት ይጠበቅባታል።

ስለ ሥራ ቁሱ ከምስባኩ መሰበክ ይኖርባቸዋል። ዘማሪዎቹ ስለ ሥራ መዝሙር ሊዘምሩ ይገባል። ያን ጊዜ የምዕመናን የሥራ አመለካከት እየሰፋ ይሄዳል።

"ቤተክርስቲያን ነጋዴ አይደለችም " የሚል ጽንፈኛ አመለካከት እንኳ ቢኖር፤ ሠርታ በማሳየት ይህን ከቃሉ የወጣ አመለካከት ማረቅ ትችላለች። ዛሬ አንዳንድ ቤተክርስቲያን በር ላይ ለቤተክርስቲያኒቱ ገቢ የሚያስገኙ ሥራዎች ተጀምረው እናያለን፣ ይህ ደግሞ መልካም ጅምር ነው ሌሎችም አብያተክርስቲያናት ሊከተሉት የሚገባ ነው እላለሁ። ምንም እንኳ ቤተክርስቲያን የንግድ ቤት አይደለችም የሚል አውድን ያልጠበቀ ወቀሳ እንኳ ከጽንፈኞች ቢገጥማትም ሰርታ በማሣየት በማስተማርና ሥራ አጥተው የተቸገሩትን በመርዳት ቤተክርስቲያን ከእውነት ጋር ፀንታ ልትቆም ይገባታል።በተጨማሪም መጽሐፍ ቅዱስ ሥራ የምንሰራው ለምን እንደ ሆነ እና አላማውም ምንድን እንደሆነ የሚያስተምረውን አጠንክራ ልታስተምር ይገባል።

"አንደኛው ሥራ የምንሠራው ለእኛም ሆነ ለሌሎች የሚያስፈልጋቸውን ነገር ለማግኘት ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውሰጥ ሥራ ተሞግሶ፣ ስንፍና ግን ተወግዞ የምናገኘው በዚህ ምክንያት ነው /ምሳ 28:19 ፣ 16:26/ በአዲሰ ኪዳን ጳውሎስ ብርቱ ምክር ለክርስቲያኖች ሰጥቶአል። <u>" .... ሠርተው የራሳቸውን ምግብ እንዲበሉ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ሰም እናዛቸዋለን፣ እናስጠነቅቃቸዋለንም</u> 2ተሰ 3:12 ሥራ የሚያስፈልገንን ነገር የምናገኝበት መንገድ በመሆኑ "ሥራ ፈትነት" በእጅጉ ተኮንኖአል። <u>"ያለ ሥራ መቀመጥ እንቅልፍን</u>

<u>ያስከትላል፣ ስለዚህ ሰነፍ ሰው ረኃብተኛ ይሆናል። "ትጉህ ገበሬ በቂ ምግብ ይኖረዋል፣ ጊዜን በከንቱ የሚያባክኑ ሰዎች ሁል ጊዜ እንደ ደኸዩ ይኖራሉ"</u> /ምሳ 19:15፣ 20:4፣ 20:13/። በእግዚአብሔር ዓለም ውስጥ ሥራ ፈት ሆኖ መኖር ፍጹም ነውር ነው። እያንዳንዱ ሰው በገዛ እጁ እየሠራ መብላት አለበት። የማንሠራ ከሆነ የጌታ ቃል እንደሚናገረው መብላት የለበንም።

ሁለተኛው ሥራ የምንሠራው የተፈጠርንበትን ዓላማ እውን ለማድረግ ነው። ለመንቀዋለል አልተፈጠርንም፤ ለመበዘንም አልተሠራንም። የተፈጠርነው በእግዚአብሔር አምሳል ነው። በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረ ሰው፣ እንደ እግዚአብሔር የሚሠራ ነው። በአምሳሉ ከፈጠረን በኋላ ሥሩ አለን /ዘፍ 1:28/ ልብ እንበል "የምንሰራው ለመኖር አይደለም፣ ይልቁንም የምንኖረው ለመሥራት ነው። እግዚአብሔር ሠራተኛ ፍጡር አድርጐ ስላበጀን፣ እኛም እንሠራለን፣ እንፈጥራለን። የፈጠራ ክህሎታችን ከየትም የመጣ አይደለም፣ ካተመብን አምሳሉ እንጂ። ሠራተኞች ከመሆን ይልቅ ቦዘኔዎች ከሆንን፣ ፈጣሪዎች ከመሆን ይልቅ አጥፊዎች ከሆንን የተፈጠርንበትን ዓላማ ስተናል። ሰው በፈጠራ ክህሎት የተካነ ፍጡር ነው። ማሰብና ማስላት ይችላል፣ መማርና መመራመር ይችላል። በመሆኑም ሥራ ለሰው ልጆች መልካም የሆነው እነርሱነታቸው የሚታወቅበት በመሆኑ ነው። ሰዎች ጎሊናውያን እንጂ እንደ እንስሳት ደመ ነፍሳውያን አይደሉም። ይልቁንም፣ "ለባውያን ወንቁሃን" ናቸው ማለትም ብልህና አስተዋይ ናቸው። እንስሳት ግን እንዲህ አይደሉም። እንደ እኛም "አምሳለ መለኮት" አይደሉም። ሠራተኝነት ሰዎች በእግዚአብሔር የተፈጠሩበትን

ዓላማ እውን ሲያደርግ፣ ሥራ ፈትነት ደግሞ ከዚያ ያጐድላቸዋል። ለሷልትና ለዋዛ ፈዛዛ አልተፈጠርንም። ሠራተኛ እንድንሆን ማለትም ሥራ አክባሪና በሥራ አዳሪ እንድንሆን ተፈጥረናል።

ሶስተኛው ሥራ የምንሠራው እርስ በእርስ ለመደጋገፍ ነው። በእግዚአብሔር ዓለም ውስጥ ህብረተሰባዊነት እንጂ፣ ግለሰባዊነት ስፍራ የለውም። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሰዎች አብረው እንዲኖሩ፣ እንዲሠሩ፣ እንዲተባበሩ ሲጠሩ ማየት የተለመደ ሥርዓት ነው። አንዱ ሲሠራ፣ ሲያበጅና ሲያሳምር ሌላው ይጠቀማል። የአንዱን ጉድለት ሌላው ይሞላል። አንድ ሰው ሁሉን መሆን ስለማይችል፣ ለሁላችንም የተለያየ ችሎታ ተሰጥቶናል። ሁላችንም በተሰጠን ችሎታ ስንሳተፍ አብረን ተደጋግፈን እናድጋለን። ለሥራችን ትርጉም ከሚሰጠው ነገር አንዱ ይህ "እርስ በርስ መደጋገፋችን፡ ነው። ልብ እንበል፡ እርስ በእርሳችን መደጋገፍ ተባለ እንጂ፣ ሽክም /ፖራሳይት/ እንሁን አልተባለም። ሥራ መተጋገዣና መረዳጃ መሆኑ ቀርቶ መበዝበዣና መጨቆኛ ከሆነ፣ "ራስ ወዳድነትን" እያራመድን ነው። አዲስ ኪዳን በገዛ እጃችን እየሠራን ራሳችንንም ሆነ ሌሎችን እንድንረዳ ይመክረናል/ኤፌ 4:28

በመጨረሻም ሥራ የምንሠራው ለፈጣሪያችንና ለአምላካችን ክብር እንዲሆን ነው። እግዚአብሔር ለፍጥረቱ ዓላማና ግብ ሰጥቶአል። ፍጥረቱ በተፈጠረበት ዓላማና ግብ ሲኖር እግዚአብሔር ይከብራል። እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ተባባሪ ሠራተኞች እንድንሆን አድርጐናል። ምድርን ሲፈጥር ምድር በራሷ ፍሬ እንድታፈራ አላደረገም። ሰዎች ምድርን እንዲገዙና

እንዲያለሙ አደረገ። ይህም ከሰዎች ጋር አብሮ ለመሥራት ምን ያህል ራሱን ትሑት እንዳደረገ በግልጽ ያሳየናል። እግዚአብሔር የሰዎችን "አብሮ ሠራተኝነት" ፈልጓል። በሌላ አነጋገር" "የሥራ ባልደረቦቹና አጋሮቹ" እንድንሆን ይሻል። እርሱ ዐፈርን፣ ዘሩን፣ ፀሐዩን፣ ዝናቡን፣ አዘጋጀ። እኛ ደግሞ እናርሳለን፣ እንዘራለን፣እናጭዳለን። እግዚአብሔር ፈጣሪ ነው፤ ሰዎች አልሚ ናቸው። እግዚአብሔር አስገኚ ነው፣ ሰዎች ከእግዚአብሔር የተገኘውን እርሱ በሚሰጣቸው ፀጋና ኃይል ተንከባካቢ ናቸው። እንግዲህ በፈጣሪና በፍጡር መካከል "ትብብር" አለ ማለት ነው። ስንሠራ እግዚአብሔርን እናከብራለን /ቆሮ 10:31፣ ቁላ 3:23-24/። ሥራ አምላካዊ በረከት፣ ፀጋና ጥሪ ነው። ስንሠራ በእግዚአብሔር የተፈጠርንበትን ዓላማ እንፈጽማለን፣ የእነርሱንም አምሳል እንገልጣለን።(ሥራ አምልኮ ነው) የሚባለው በዚህ ምክንያት ነው። **እግዚአብሔር ስላለ ሥራ ክቡር ነው**። እግዚአብሔር ሠርቶ ስላሳየ ሥራ የተመሰገነ ተግባር ነው። [14]

በዚሁ አጋጣሚ ሌላ መስተካከል አለበት የምለው ቤተክርስቲያን ደጃፍ ላይ ሙሉ አካል ያላቸው ሰዎች ለልመና ሲኮለኮሉ ቤተክርስቲያን ሰብሰባ ሥለ ሥራ በማስተማርና (brain wash) በማድረግ ለሥራ ልታነሣሣ ይገባል የሚል ነው። መስራት የሚችሉትና መስራት የማይችሉት ተለይተው ሊታወቁ ይገባል፤ እንጂ መስራት የሚችሉትን ሁሉ እየመፀወተች ሠርተው ሊያገኙት ካለው በረከት ልታስቀራቸው አይገባም እላለሁ። ቤተክርስቲያን ማድረግ ያለባት ዋና ነገር ህዝቧን ለስራ ማነሳሳትና ከመንግስትም ጋር ተባብሮም

[14] ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር ሚኒሊክ አስፋው ገጽ 53-54

እንዲሠሩ ማድረግ ነው።ከመንግስት ጋር በመተባበርና ህዝቧን በማስተባበር በነቂስ ህዝቧን አውጥታ አካባቢዋን ልታፀዳ ደኖችን ልትተክል ከመንግስት ጐን ልትቆም ይገባታል።

በተጨማሪም ትጉ የሆኑ ክርስቲያን ነጋዴዎችን በህዝብ ፊት በመሸለም ሰነፎችና ወስላታ ነጋዴዎችን ለመልካም ሥራ ልታነሣሣ ይገባል። በትንሽ ብትጀምሩም ታድጋላችሁ ልትል ይገባል ምክንያቱም ዛሬ ዓለምን ሁሉ የሞላው ወርልድ ቪዥን የተጀመረው በኮሪያ ሀገር በ5 ዶላር ብቻ እንደነበረ የወርልድ ቪዥን አነሳስ ታሪክ ይናገራል። አለበለዚያ ቤተክርስቲያን የሰነፎች፣ የግብዞችና እና የወንበዴዎች ዋሻ ነው የምትሆነው።

በቅርቡ አንድ ወጣት እንዲህ የሚል ደብዳቤ ፃፈልኝ እኔ ክርስቲያን ነኝ። ግን ምንም የገቢ ምንጭ የሌለኝ ድኃ ሰው ነኝ ። ታዲያ አንዲት በጣም የምወዳት ልጅ አፍቅሮ አለችኝ ለጥሎሽና ለሠርግ የሚሆን ገንዘብ ስለሌለኝ ጠልፌ ባገባ ኃጢያት ይሆንብኛል ወይ? እርሷም እንደኔው የገቢ ምንጭ /ሥራ/ የላትምና በእምነት መጋባት አንችልም ወይ? የሚል ነው። ይህንን ዓይነት ጥያቄ የሚያነሣው ሰው ቤተክርስቲያን ውስጥ ነው ያለው ገና ጠለፋ ኃጢያት እንደሆነ አያውቅም ገና ሥራ ሳይኖረው ሚስት ብሎም ወደፊት ልጅ እንዲኖረው የሚፈልግ ሰው ነው።ለምንድነው ይህ ወጣት እንደዚህ አይነት ውስብስብ ችግር ውስጥ ራሱን ለማጠላለፍ የሚፈልገው ? ምክንያቱስ ምን ሊሆን ይችላል ?.ብዙ ምክንያቶች ቢኖሩም ምናልባት አንዱ፤ግሩም የሆነ የሥራ ስነ-ምግባር ትምህርት በቤተክርስቲያኑ አለመማሩ ቢሆንስ። ቢማር ኖሮ አፍቅሮ ፈልጐ ከማግባቱ በፊት ሥራ መፈለጉን ያስቀድም ነበር። ልክ እንደዚህ

ወጣት አይነት ጥያቄ ሌሎች ሁለት እጮኛሞችም ጠይቀውናል።

"ሁለታችንም ሥራ የለንም ግን በእምነት ብንጋባ ምን ችግር አለው ?" የሚል። እኔንም መልሼ እንዲህ ስል ጠየኩአቸው፤ "ምን ትበላላችሁ?" እነርሱም አሰብ አድርገው "ፍቅር እንበላለን" አሉኝ ፍቅር ያለ እንጀራና ውኃ እስከመቼ ይበላል! እነዚህ ወጣቶች እንደምናያቸው ቤተክርስቲያን ይሁን ብላ ብትለቃቸው ምናልባት ከወር በኋላ እርስ በርሳቸው ሲበላሉ ታገኛቸዋለች ትዳርም ይፈርሳል። ስለዚህ ቤተክርስቲያን አሁን ከምታደርገወው በተጨማሪ ለልጆቿ ጤናማ የሆነ የሥራ ስነምግባር በማስተማር ለበጐ ሥራ ሁሉ ህዝቧን ልታነሳሳ ይገባል። ያን ጊዜ የኢትዮጵያ ድኅነት ተረት ይሆናል። ድኅነትን የምታሸንፈው ቤተክርስቲያን ነች። ....<u>*በመካከላቸው አንድስ እንኳ ችግረኛ አልነበረም ይላልና ቃሉ*</u>/ ሐዋ.ሥራ 4:34/


ያኔ ኢትዮጵያችን ከዳቦ ቅርጫነት ወጥታ የዳቦ ቅርጫት ትሆናለች ::ያኔ በዓለም ላይ በድኅነት ትታወቅ የነበረች ኢትዮጵያ በታታሪ ሠራተኝነት ትታወቃለች።

ሥራ እርግማን ሳይሆን የእግዚአብሔር ስጦታ ነው። ሥራን እርግማን አድርገው የሚያዩ ሰዎች ያገኙትን ሥራ ሰርተው ራሳቸውን ለመለወጥ ይልቅ በልመና፣ በአቋራጭ መንገዶች፣ በሙስና ሥራን በመሥራት መክበር ይፈልጋሉ። ይህ ደግሞ በጋራ የኋላ ኋላ ራሳቸውንም አገርንም ይጎዳል።

አውሮፓና አሜሪካ የ1ኛው ዓለም ሰዎች እንዲባሉ ያደረጋቸው ዋና ምሥጢር የፕሮቴስታንት የሥራ ሥነ ምግባር (Protestant work ethics) የተባለው ነው። ይህ የሥራ መርህ ሥራ ለእግዚአብሔር የተሰጠ ስጦታ እንደሆነና ሰዎችን የሚጎዳ እስካልሆነ ድረስ ሰው የማይሰራው ሥራ እንደሌለ ያምናል።

ሥራን በተክክለኛው አስተሳሰብ እስካየነው ድረስ ሥራ ለሰው ሳይሆን ለእግዚአብሔር እንደምናደርገው አድርገን በትጋት እንድንሰራው የእግዚአብሔር ቃል ያዘናል። ቆላ 3፤23

አገራችን በማንኛውም መንገድ ካደጉት አገሮች ተርታ ለማሰለፍ እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር አመቻችቶልናል። ቁልፉ በእጃችን ነው፣ ሰርተን ማደግ፣ ሰርተን መክበር፣ ሰርተን እራሳችንን መለወጥ እንችላለን። ወ/ሮ ደመወዝ ቁጭት የሚያሲዝ መጽሐፍ በዚህ በሥራ ሥነምግባር ላይ በመጻፉ ላመሰግነው እፈልጋለሁ። ዛሬ ይህን መጽሐፍ በቡድን ጥናትና በመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤቶች እና በሌሎችም መድረኮች ሁሉ ትምህርት የሚሰጥበት መጽሐፍ አድርገን እንድንወስደው አበረታታለሁ።



መጋቢ ስለሺ ከበደ (ዶ/ር)

በነገራችን ላይ አገራችን የዳቦ ቅርጫት እንዳትሆን ጋሬጣ የሆነው ቤተክርስቲያን ህዝቧን ለሥራ አለማነሳሳቷ ብቻ ሳይሆን መንግስትም ሠራተኞቹን ለበለጠ ሥራ በበለጠ ሁኔታ አለማነሳሳቱ ነው። ታዲያ መንግስት ሰራተኛውን በበለጠ ሁኔታ ለሥራ ለማበረታታት ምን ማድረግ ይጠበቅበታል ?.

የሰው ልጅ

'ሀ' ብሎ በሳር

'ዋ' ብሎ በአሳር

ይማራል !

ሉሬት ጸጋዬ ገ/መድኅን

ምዕራፍ ዘጠኝ

ኢትዮጵያችን የዳቦ ቅርጫት የምትሆነው መንግስት ሠራተኞችን ለበለጠ ሥራ ማበረታት ሲችል ነው::

መንግስት አሁን እያደረገ ያለው ጉዳይ ይበርታ ይደግ ይመንደግ የሚያሰኝ ነው:: አልፎ አልፎ ትጉና ታታሪ ሠራተኛ ገበሬዎች ሲሸለሙ አይተናልና:: ሆኖም ይህ የሚያበቃ አይደለም:: የምድሪቱን ሠራተኞች የበለጠ እንዲሰሩ ለማበረታታት ከተፈለገ በየቤቱ መልካም አስተዳደር እንዲነግስ የቅርብ ክትትል ማድረግ:: በየዘርፉ ያሉ ሰርተው የሚያሰሩ መሪዎችን በየድርጅቱ ጠቅላላ ሰራተኞች ፊት መሸለም:: በቴሌቪዥንና በሬዲዮ ሰለ ስራ ፈጠራ የሚያስተምር ኘሮግራም ሰፊ ሽፋን ተሰጥቶ ዜጐችን ለስራ እንዲያነሳሳ ቢደረግ ለዚህ የሚሆን የሬዲዮ ወይም የቴሌቪዥን ኘሮግራም ቢመደብ::የሚዲያ መጨናነቅ ካለ እንደ እኔ አስተያየት ከተቻለ ለውጭ ሀገር የስፖርት ትንታኔ ከምንሰጠው ሰፊ ፕሮግራም ላይ ቀነስ ብናደርግ መልካም ነው:: የበለጠ የሚጠቅመን ይኼኛው ነውና:: አርቲስቶች ደግሞ ስለሥራ የሚያወሳና የሚያስተምር ዝማሬ ቢያቀርቡ ግሩም ነው:: ለምሳሌ እንደ "ሁሉም ቢተባበር የት ይደረስ ነበር ዓይነት" አሁንም በግሌ አስተያየት አይንሽ ጥርስሽ የሚለው ዘፈን ኢትዮጵያውያንን ከድህነት ብዙ ፈቅ የሚያደርገን አይመስለኝምና:: የሁላችንም ራዕይ ድህነትን ከምድራችን ላይ ለማጥፋት መሆን አለበት:: ስለዚህ መንግስት ቤተክርስቲያን እና ህዝቡ አንድ ግብና አንድ ራዕይ ሊኖረን ይገባል::ያለ ግብና ያለራዕይ የሚንቀሳቀስ ሰው የት እንደሚደርስ

አያውቅምና::

አንድ የምንወዳቸውና የምናከብራቸው በራዕይ መንቀሳቀስን የሚወዱ የቤተክርስቲያናችን ሰው ራዕይን አስመልክቶ እንዲህ ብለዋል::

ራዕይ የሌለው:-

- ዝናብ የሌለው ደመና
- እህል የሌለው ቀፎ
- ክር የሌለው መርፌ
- ድንጋይ የሌለው ባትሪ
- ጋዝ የሌለው ኩራዝ
- ጥይት የሌለው ጠመንጃ
- ሞተር የሌለው መኪና
- ጨው የሌለው ምግብ
- ቅጠል የሌለው ዛፍ
- ጥርስ የሌለው አንበሳ
- ወጥ የሌለው እንጀራ
- ክንፍ የሌለው አሞራ
- ክዳን የሌለው ፔርሙስ
- ከንፈር የሌለው ጥርስ

- አጥር የሌለው ቤት
- መንገድ የሌለው መንደር
- ፊልም የሌለው ካሜራ
- አምፖል የሌለው ኤሌክትሪክ
- አውራ የሌለው ንብ
- መህልቅ የሌለው መርከብ
- አስኳል የሌለው እንቁላል
- መስኮት የሌለው ቤት ነው ብለዋል።

አቶ አየለ ቀልቦሬ/

ከአቃቂ ቃለ ሕይወት ቤተክርስቲያን /2000 ዓ.ም/

እዚህ ላይ የምንማረው ምንድን ነው፤ ያለ ራዕይ መጓዝ ከንቱ ነው የሚለውን ነው። ሆኖም ደግሞ መንግስት ራዕይም ኖሮት ራዕዩን በሙሉ ልብ ይዞ ከግብ የሚያደርስ ንቁና ታታሪ ሰራተኛ ከሌለ ከንቱ ነውና ለሰራተኞች የምለው አለኝ። ይኸውም፦ሥራ አላሰራ ከሚል ለራዕያችን እንቅፋት ከሚሆን ክፉ ኃሳብ ጋር እንጂ ከሥራው ከራሱ ጋር አንጣላ የሚል ነው።

ዮሴፍ ከጲጥፋራ ሚስት ክፉ ሀሳብ ጋር እንጂ የተጣላው ከሥራው ከራሱ ጋር አልነበረምና መጽሐፍ ቅዱስ ሥራውን ሊሠራ ገባ ይለናል።በዘፍ 39፡11 <u>"እንዲህም ሆነ በዚያን ጊዜ ሥራውን እንዲሠራ ወደ ቤቱ ገባ..."</u> አንዳንድ ሠራተኞች የመስሪያ ቤቱ አካሄድ አላምራቸው ሲል ከአለቃቸው ጋር

ሳይስማሙ ሲቀሩ ፊት ለፊት ተነጋግረው ለነገሮች መፍትሄ ከመስጠት ይልቅ ከሥራ ጋር በመጣላት፤ ሶኬት ሳይነቅሉ ይሄዳሉ። መብራት ሳያጠፉ ይሄዳሉ፤ የቧንቧ ውኃ ከፍተው ይሄዳሉ፤ ወይም ማሽን ይሰብራሉ ባጠቃላይ ለድርጅቱ ኪሣራ የሚያመጡ ተግባሮችን ይፈጽማሉ። ይህ ግን አሳዛኝ ነው። አገርን የሚየሳድግ ሳይሆን የሚያቆረቁዝ ነውና ራሳችንን እናርም።መልካም የሆነውንም ሥራ ከመስራት አንታክት፤ አንለግም፤ አንሰልችም።አንድ ነገር ልጨምርና ልጨርስ

በዓለም ላይ ምንም ቢደረግ የማይሰለች ጉዳይ ምንድነው ተብሎ ቢጠየቅ ብዙ መልስ እንናገር ይሆናል። ግን ትክክለኛው መልስ በዓለም ላይ ከጥንት ጀምሮ እስከዛሬ ድረስ የሰው ልጅ ቢያደርገው ቢያደርገው ያልሰለቸው ወደፊትም የማይሰለቸው ጉዳይ ቢኖር **"ልብስ መልበስና ማውለቅ ነው"** እስቲ ተመልከቱ አንድ ሰው ዛሬስ መልበስ ሰለቸኝ ብሎ ራቁቱን ለመዋል አስቦ ከቤት ቢወጣ የሚፈጠረውን ገምቱ። ሥራ መስራትም እንደልብስ መልበስና ማውለቅ የማይሰለቸን የማይታክተን ሊሆን ይገባል።ያን ጊዜ ኢትዮጵያችን ከዳቦ ቅርጫ ወጥታ የዳቦ ቅርጫት ትሆናለች።

በነገራችን ላይ ኢትዮጵያችን ከዳቦ ቅርጫ ወጥታ
የዳቦ ቅርጫት እንዳትሆን መሰናክል የሆነባት ነገር
መንግስት ሠራተኛውን ከዚህ በበለጠ ለሥራ
ለማነሣሣት አለመቻሉ ብቻ ሳይሆን የቁጠባ ባህላችንም
አለመዳበሩም ነው። ታዲያ የቁጠባ ባሕላችን
እንዲዳብር ምን እናድርግ?

በፈሊጥ ካልገባህ
በፍልጥ ይገባኃል።

ምዕራፍ አስር

ኢትዮጵያችን የዳቦ ቅርጫት የምትሆነው የቁጠባ ባህላችን ሲዳብር ነው?

በእኔ ትርጉም መቆጠብ ማለት ለነገ ማስቀመጥ ማለት ነው። መቆጠብ በእግዚአብሔር ላይ እምነት ማጣት አይደለም። ዛሬ የቆጠብነውን ነገ እንደምናገኘው በእግዚአብሔር መታመናችን ነው እንጂ። <u>*ነገ ለራሱ ይጨነቃልና ለነገ አትጨነቁ*</u> /ማቲ 6፡33/ ተብሏል፤ በማለት ለነገ የማያስቀምጡ እንዲሁም ባንክ ገንዘባቸውን የማያስገቡ ሰዎች አሉ። ነገር ግን ይህ ቃል ፈጽሞ ለነገ አትቆጥቡ የሚል ዕሳቤ የለውም። ቁጠባ እንዲያውም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው። በዘፍ 41:25-36 ላይ ዮሴፍ የግብጽን ንጉስ ፈርኦንን ሕልም ከፈታ በኃላ በመጀመሪያ ሰባት የጥጋብ ዓመታት እህል ይከማች ይህም የሚቆጠበው እህል ቀጥሎ ለሚመጣው ሰባት የረኃብ ዓመታት ይሆናል ሲል እናነባለን። መቆጠብ አለማመን ሳይሆን ብልህነት ነው። ለክፉ ቀን ብለን የምናስቀምጠው ክፋ ቀን ያሳልፋል እንጂ ክፉ ቀን አይጠራምና። ቁጠባ ዛሬንም እንደዛሬ ነገንም እንደነገ መኖርን የሚያስተምር ነው። ቁጠባ ጊዜንና ዘመኑን ማወቅና ብሎም መዋጀት ነው። በምሳሌ መጽሐፍ ምዕራፍ 6 ላይ ጉንዳን ዘመኑን በመለየት እንደምትቆጥብ እንመለከታን <u>*" መብልዋን በበጋ ታሰናዳለች መኖዋንም በመከር ትሰበስባለች።"*</u>

ጉንዳን በጋና መከርን ለይታ ትሰራለች ይኸውም በመከር አዝመራ እርሻ ላይ የሚገኝበት ወቅት ነው።መኖዋን ትሰበስባለች

እንጂ አታሰናዳም። ለምን ገበሬው እህሉን ከእርሻ ላይ ሳያነሳባት ቶሎ ቶሎ ትሻማለች። በበጋ ግን አዝመራ በእርሻ ላይ የማይገኝበት የፀሐይ ወቅት ነው። መብልዋን ታሰናዳለች። ታሰናዳለች ማለት ሁሉንም የሰበሰበችውን በየክፍሉ በየክፍሉ ዋሻዋ ውስጥ ታስቀምጣለች ማለት ነው። ጉንዳን በመከር ትሰበስባለች በበጋ ታሰናዳለች በክረምት ደግሞ የቆጠበችውን እየበላች የክረምቱ ውኃ ጠራርጐ እንዳይወስዳት አቅሟን ስለምታውቅ ክረምት እስከሚያልፍ በደህና ወቅት ዘመኑን ለይታ ያጠራቀመችውን እየበላች ዋሻዋ ውስጥ ትቀመጣለች።

በቃሉ ላይ እንዲህ አድርጐ ስለ ጉንዳን የተቀመጠው፡- እግዚአብሔር ለጉንዳን ገዶት ሳይሆን የሰው ልጅ ትምህርት ያገኝበት ዘንድ ነውና እስቲ ከዚህ እንማር። ከጉንዳን ብዙ ነገር እንማራለን።ቁጣዩን እንመልከት፡ ጉንዳኖች፡-

- ተስፋ አይቆርጡም /ከክብደታቸው የበለጠ ሸክም ተሸክመው ይሄዳሉ/
- ታታሪ ሠራተኞች ናቸው /አለቃ የላቸውም ሁሉም በስራ የተጠመዱ የራሳቸው አለቆች ናቸው/
- በመተባበር ይሠራሉ /በመካከላቸው አልምጥ የለም/

ፈጣኖች ናቸው /አንዴ በእግር ከገቡ ጭንቅላት ላይ ወዲያው ይወጡና ልብስ ያስወልቃሉ።

ባጠቃላይ እግዚአብሔር ከጉንዳን ኮሌጅ የሚያስተምረን ቁጠባን ብቻ ሳይሆን ተስፋ አለመቁረጥን ታታሪ ሠራተኛ

መሆንን በመተባበር መስራትን ለሥራችን ፈጣኖች መሆንን ሁሉ ነው።

ለእኛ ለኢትዮጵያውያን ቁጠባ እጅጉን ያስፈልገናል። ለድኅነታችን ጥልቀት አስተዋጽኦ ያደረገው የገቢ ምንጫችን አናሳ መሆኑ ብቻ ሳይሆን ያገኘነውንም በአግባቡ ሳንጠቀም ማድፋፋታችንም ነው። ለዚህ እንደመረጃ የማነሣው የዓመት በዓል ወቅትን ነው። በዚህ ጊዜ በጉም፣ ዶሮውም፣ ቅርጫውም መጠጡም አዲስ ልብስ መግዛቱም አዲስ የቤት ዕቃ መግዛቱም ወይም መቀየሩም ሁሉም አንድ ላይ እንዲሆን የምንፈልግበትና የምናደርግበት ወቅት ነው። ለአመትና ለስድስት ወር እየቆጠብን መብላት የምንችለውን ኃብት በአንድ ሳምንት ወይም ወር ውስጥ ተደፋፍቶ ይቀራል። ለምን በግ ከተገዛ ቅርጫውና ዶሮው ቢቀርስ ወይም ዶሮ ከታረደ በጉና ቅርጫው ቢቀርስ፤እንደ እኔ የግል አስተያየት ብናውቅበት እኮ በቁጠባና ራስን በመግዛት ሁሌ ኑሮአችንን ሁልግዜ ዓመት በዓል ማድረግ እንችላለን።

ደስታ እኮ አንድ ቀን ብቻ ይለቅ ከተባለ ወደ ለቅሶም ሊቀየር ይችላል። እስቲ ወደ ቁጠባ ባህል እንመለስ። አንዳንድ ሰው ደመወዙን በተቀበለ ሰሞን ፈሽታ ያደርጋል። ከበር መልስ ጓደኞቹን ሁሉ ይጋብዝና በ15ኛው ቀን ኪሱ ባዶ ቤቱ ባዶ ሲሆንበት፡ አራራ መታኝ ይላል። አራራ የመታው ወይም ያስመታው ማነው? ራሱ ሰውየው አይደለምን?

የቁጠባ ባህላችን እንዲያድግ እዚህን ሁለት ነገሮች ብናደርግ መልካም ይሆናል።

- ቤተሰብ ምሳሌ በመሆን ልጆቻቸውን ስለቁጠባ ማስተማር

ያስፈልጋቸዋል።

መንግስት ሕዝቡን በተለያዩ መንገዶች ተጠቅሞ ስለቁጠባ ማስተማር አለበት።

የኪነ ጥበበ ሰዎችም ስለቁጠባ በማይረሳና በሚያስደስት መንገድ ማስተማር አለባቸው እንጂ "**መገን ያራዳ ልጅ አይፈራም ኪሣራ፤ ፖውንዱን መንዝሮ ገባ ሠንጋ ተራ**" የሚለው አካሄድ ብዙ አላዋጣንም፡ የአራዳ ልጅ ከሆነ ኪሣራን ሊፈራ ቁጠባን ሊያፈራ ይገባልና። እስቲ እኔና ባለቤቴ ደመወዛችንን ተቀብለን ስንመጣ ምን እንደምናደርግ ልንገራችሁ፤የእኛ ቤት 10,20,70 በሚለው የቁጠባ መመሪያ ያምናልና።ምን ማለት ነው አስር፤ሃያ፤ሰባ ማለት። 10 ማለት ከአሥር አንድ የእግዚአብሔር ነው። /ከሁለታችንም ደመወዝ ከአስር አንድ ለፈጣሪያችን አስራት እንሰጣለን።/ 20 ማለት ደግሞ ከመቶው ሃያ ፐርሰንት ለወደፊት ይሆነን ዘንድ እንቆጥባለን ማለት ነው። በሁለታችንም ስም ለዚህ የባንክ ደብተር አለን።/ 70 ማለት ከመቶ ሰባ ፐርሰንት ለቀለባችን እናደርጋለን ማለት ነው።በአጭሩ ከአስር አንድ ለጌታ እንሰጣለን፣ ሃያውን እንቆጥባለን፣ሰባውን እንቆረጥማለን ማለት ነው።ይህ መመሪያ በጣም ጠቅሞናልና እስቲ እናንተም ራሳችሁን በመግዛት ይህንን መመሪያ ተጠቀሙበት አትራፊ እንጂ አክሳሪ አትሆኑምና።በቁጠባና በእቅድ የሚመራ ሰው የሕይወት ወከባ የለበትም።**አሥር ሃያ ሰባ የለበት ወከባ!!**

እስቲ አሁን ደግሞ ወደ ጆንዊስሊ የቁጠባ መመሪያ ልውሰዳችሁ፤ ጆንዊስሊ መልካም ክርስቲያናዊ የሥራ ሥነ

ምግባር የነበራቸው የተከበሩ የእግዚአብሔር ሰው እንደነበሩ የፃፏቸውን መጽሐፍት የሚያነቡ ሰዎች ሁሉ ይመሰክሩላቸዋል። ታዲያ እኚህ የተከበሩ የእግዚአብሔር ሰው ሥራንና ቁጠባን አስመልክቶ የሚከተለው መመሪያ ወይም መፈክር ነበራቸው፦

የምትችለውን ያህል ሥራ


የመትችለውን ያህል ስጥ

የምትችለውን ያህል ቆጥብ

እነዚህ ሶስት ከቃሉ ጋር የማይጣረሱ ሀሳቦች ለምድራችን ለኢትዮጵያም ያስፈልጓታል። ያን ጊዜ ኢትዮጵያችን ከዳቦ ቅርጫት ወጥታ የዳቦ ቅጫት ውስጥ ልተገባ ትችል ይሆናልና።

ያልሰራ አይብላ ማለት የሰራ ይብላ ማለት ነው። ስለዚህም ሰው ሥራ ሳያማርጥ ከሰራ በዚህ ምድር ላይ የተዋጣለትና ደስ የሚል ኑሮ ሊኖር ይችላል። የዓለማችን የታወቁ ኃብታሞች በጣም ብዙ ሥራዎችን ሳያማርጡ በመስራታቸው በአንዱ ሥራ ላይ ውጤታማ ሆነዋል።በመሆኑም በሀገራችን ኢትዮጵያ ድህነትን ልንቀንስ የምንችለው ማንም ሰው ይህንን ወይም ያንን ሥራ አልሰራም ሳይል በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ያገኘውን ሥራ ቢሰራ ስኬታማ ሊሆን ይችላል። የዛሬ አስራ አምስት ዓመት አንድ ወንድም ``ቢዚ በግዱ አለኝ ለምን መሰላችሁ ሁልግዜ በተለያዩ ሥራዎች ላይ ተጠምጄ ስለሚያዩኝ ነበር። እኔ ግን በግድ ሳይሆን ደስ እያለኝ ነገዬን አስቤ ነበር የምሰራው። ሥራ ሳላማርጥ ያለመታከት በመስራቴም ከጌታዬ ጋር አሁን ላለሁበት መልካም ኑሮ በቅቻለሁ።

ወንድማችን ወ/ዊ ደመወዝም በዚህ መጽሐፍ ላይ የሚመክረን፤ ሥራ ሳናማርጥና ሳንንቅ ብንሰራ በግልም ሆነ በጋራ ከድኅነት እንወጣለን፤ አገራችንም ኢትዮጵያ ከዳቦ ቅርጫ ወጥታ የዳቦ ቅርጫት ውስጥ ትገባለች ይለናል።እኔም ኢትዮጵያዊያን ሁሉ ይህንን መጽሐፍ እንድናነብና ለተግባራዊነቱም በነቂስ እንድንወጣ ስጋብዝ በታላቅ በደስታ ነው።



አቶ ጌታቸው ታዬ

የኢ.ወ.ቤ.ክ.መ.ኢ. የምሥራች ድምፅ

የመርካቶ መጻሕፍት መደብር አስተባባሪ

በነገራችን ላይ ኢትዮጵያችን የዳቦ ቅርጫት እንዳትሆን ማነቆ የሆነባት ጥሩ የሆነ የቁጠባ ባህል አለመኖሩ ብቻ ሳይሆን በአንድ ሥራ ብቻ ረክተንም መቀመጣችንም ጭምር ነው። ታዲያ በአንድ ሥራ ብቻ ረክተን እንዳንቀመጥ ምን እናድርግ?

አገርህ በሰማይ ቢሆንም የቀበሌ መታወቂያ ግን በኪስህ እንዳለ አትርሳ !

ምዕራፍ አስራ አንድ

ኢትዮጵያችን የዳቦ ቅርጫት የምትሆነው በአንድ ሥራ ረክተን መቀመጣችንን ሥናቆም ነው።

ምንም እንኳን አገራችን ሶስት አራት ሥራ የሚሠራበት አገር ባትሆንም ወደፊት መምጣቱ አይቀርምና ሁለት ሶስት ከዚያም በላይ ሙያ ይዞ መጠበቅ ግን ብልህነት ነው። ሌላው ዓለም ከአንድ በላይ ሥራ እንደሚሠሩ እንሰማለን። እኛስ ሥራ የለ ሆኖ ወይስ ሙያ ጠፍቶ ወይስ ዕድል የለ ሆኖ እስቲ ልባችንን በጌታ ላይ አሳርፈን <u>አዕምሮአችንን ግን ለሥራ እናቁነጥንጥ፤</u> እዚህ ላይ ለአንባቢዎቼ ግልጽ ማድረግ የምፈልገው፤ አንድ ስራ መስራት ጥሩ አይደልም፤ አያሳድግም ማለት ፈልጌ ሳይሆን ተጨማሪ ሌሎች ሙያዎችም ይኑሩን ለማለት ፈልጌ ነው።አዳዲስ የሥራ ፈጠራወችንም እናዳብር ለማለት አስቤ ነው።

ብዙ ክርስትያኖች ሥራ መሥራትን ከመንፈሳዊ ነገር የመውጣትን ያህል ይፈሩታል። ሁለትና ሶስት ዓይነት ሥራ ያለው ክርስቲያን ካለማ ለሥጋው እንደሚሮጥ አድርገው ይቆጥሩታል። ብልህ ሰው እንቁላሎቹን ሁሉ በአንድ ቅርጫት አያስቀምጥም። አንድ ችግር ቢፈጠርና ቅርጫቱ ላይ አደጋ ቢደርስ እንቁላሎቹ ሁሉ ይሰባበራሉና። አማራጩ እንግዲህ እንቁላሎቹን በተለያዩ ቅርጫቶች ማስቀመጥ ይሆናል። በአንድ ላይ አደጋ ቢደርስ ሌላኛው ቅርጫት ያመልጣል። ስለዚህ ጦም አይታደርም። ሌላው "ፍልፈልን እንመልከት። በቆፈረው በአንድ

ቀዳዳ ብቻ አይተማመንም። ይልቁንም አንዱ ቢደፈንበት በሌላኛው ያመልጥ ዘንድ ሌላ ቀዳዳ ያበጃል።ሁለት ቀዳዳ ያላት አይጥ አትሞትም እንደተባለው ማለት ነው። ስለዚህ አንድ ሰው ከአንድ በላይ ሥራዎች ሊኖሩት ከቻለ ጠቀሜታው የጉላ ነው ማለት ነው። ለዚህም ይረዳን ዘንድ ራስንና አገርን ለማበልጸግ የሚረዳውን የሥራ ፈጠራ (Entrepreneurship) /ማለት የሰው ኃይል፤ መሬት፤ ኢኮኖሚን ሁሉ በማገናዘብ ማለት ነው።/ "አሥር እንቁላል ለአንዲት ዶሮ አስታቅፎ በ21ኛው ቀን አሥር ጫጩቶችን ማግኘት ተፈጥሮአዊ ሂደት ነው። ይህንን ተፈጥሮአዊ ሁኔታ መነሻ ተደርጉ አሳቡ በጥናት ዳብሮ እንቁላሉን የሚያስፈልገው ሙቀትና የተለያዩ ነገሮችን በመስጠት ሁኔታዎች እንዲሟሉ ተደርጉ በአንድ ጊዜ በርካታ ጫጩቶችን ማግኘት የተቻለበት ሂደት ጥሩ የፈጠራ ምሳሌ ነው። ልክ እንደ እንቁላል አሳብም ኢንኩቤት ይደረጋል።

ብልጭ የሚል አሳብ በማብላላት እንቅፋት የሆኑን አስተሳሰብና ፍርሃታችንን አስወገደን ከ "ሣጥኑ" ለመውጣት ከደፈርን ልንሠራ የምንችለውና ገቢ ሊያስገኝልን የሚችል የአዲስ ፈጠራ ባለቤት መሆን እንችላለን።

ለሥራ ፈጠራ ጽንሰ ሐሳብ መስፋፋት ትልቅ አስተዋጽኦ ያደረገው አስትሪያዊው ኢኮኖሚስት ጆሴፍ ሹምፔተር እንደሚለው አንድ ፈጠራ ተፈጠረ የሚባለው ከዚህ ቀደም ያልነበረ አዲስ አሳብ ወደ ተግባር በመለወጥ ብቻ ሳይሆን የነበረውንም በአዲስ መልክና አገላለጽ የአሰራር ዘዴ ማቅረብንም ይጨምራል ይላል። በዚሁ ምሁር አገላለጽ መሠረት አንድ አዲስ

የፈጠራ ውጤት በመጣ ቁጥር የቀድሞው እየጠፋ እየተተካ ይሔዳል።

በእኛ አገር ባህልና የተለያዩ ምክንያቶች የፈጠራ ወይም የአንድ አዲስ አሳብ ባለቤት ሆኖ ቀድሞ ለመታየት ብዙ ተነሳሽነት የለንም፤ እንጂ በአገራችን አዳዲስ ሪከርዶች ሊመዘገብላቸው የሚችሉ ብዙ የሚፈጠሩ ነገሮች አሉ። በዚህ እድል ለመጠቀም ዛሬ የተሻለ ዘመን ነው። ከሌሎች ጋር ሳይሆን ከራሳቸው ጋር እየተወዳደሩ አዳዲስ ታሪኮችን እያስመዘገቡ እራሳቸውን ቤተሰባቸውን፣ሕዝብና አገራቸውን በመጥቀም ኢንተርኔሪነሮችም በሚሰጡን ፍሬ አገራችን በቅርቡ ከኋላ ቀር አገሮች ጋር ከተመዘገበችበት መዝገብ ሥሟን አውጥተን በትልቅ ቦታ እናደርሳታለን የሚል ተሰፋ አለኝ!!! "

ሽለምጥማጥ የምትባል አውሬ በአብዛኛው ምርጥ ምግቧ ማር ነው። ታዲያ ይህንን ምግቧን ለማግኘት እግዚአብሔር በተፈጥሮ የሰጣት ልዩ ችሎታ አላት። እንደሚታወቀው ማር በሁለት ቦታ ይገኛል አንደኛው ከምድር በላይ /በቀፎ ዛፍ ላይ ተሰቅሎ/ 2ኛ ከምድር ውስጥ /ጣዝማ ማር ይባላል/ ታዲያ ይህች አውሬ ይህንን ምግቧን ለማግኘት ወደ ጫካ ትወጣና እየሄደች በመንገዷ ላይ በአንደኛው ጆሮዋ ምድር ውስጥ በሌላኛው ጆሮዋ ዛፍ ላይ ያለውን አየሰማች ትሄዳለች።ሹሹሹ የሚል የንብ ድምጽ ትሰማለች ቆፍራም ማር ታገኛለች። እግዚአብሔር ልክ እንደዚሁ ለሰው ልጆች ሁሉ ስጦታና ችሎታ ሰጥቷልና እስቲ በተሰጠን ችሎታና ስጦታ ተጠቅመን ከአንድ ሥራ በላይ ለመስራት እንሞክር። ፍሬውም እጅግ ጣፋጭ ይሆናል። ፈረስ ሲሞት ለጅብ እንደሚሰጥ ነበር ከዚህ ቀደም የማውቀው፡ አሁን

ግን ሳይሞት ታርዶ ሥጋው እንደሚጠቅም ሰምቼ ደስ አለኝ። ሥጋው ለአዞ እርባታ /ለአዞ ምግብ/ ቆዳው ደግሞ ወደ ውጭ አንደሚላክ። ለካ ቁጭ ብለው ካሰቡበት የማይጠቅም ነገር የለም። ሌላም ልጨምርላችሁ።

አንድ ቀን በመንገድ ዳር ላይ በሁለት እጁ የውሻ ቡችሎች ለመሸጥ የያዘ ወጣት ልጅ አየሁና መኪናዬን ወደ እርሱ አስጠግቼ በማቆም ስንት ስንት እንደሆነ የሚሸጠው ጠየኩት ከየት እንዳመጣቸውም ጭምር፡- እርሱ በጉዳና የሚኖር ልጅ እንደሆነና በእርሱ አጠገብ ደግሞ ውሾች እንዳሉ አንድ ቀን በጣም ሲርበው ለምን እነዚህን ቡችሎች የሚገዛኝ ካገኘሁ አልሸጣቸው በሉ እንዳሰበና ለእነዚህም ቡችሎች ለወንዱ ቡችላ 60 ብር ለሴቷቡችላ 30 ብር እንደተመነ አጫወተኝ። እኔም አሳቡን አድንቄለት አበረታትቼውም ወንዱን ቡችላ በ60 ብር ገዝቼ ወደ ቤቴ ገባሁ። ሁሌ በዚያ መንገድ ሳልፍ ያን ወጣት የተለያዩ መልክ ያላቸውን ቡችሎች እንደተለመደው በቀኝና በግራ እጁ ይዞ ሲሸጥ አየዋለሁ። ጉበዝ ይህ ወጣት ከተሳካለት እኮ በአይነቱ ልዩ የሆነ የውሻ ባዛር ሳያዘጋጅ የሚቀር ይመስላችኃል። እስቲ አካባቢያችንን ዘወር ዘወር ብለን በመቃኘት የማይሠሩ ሥራዎች እናስብና ለመስራት እንነሣ እንጂ በአንዲት ሥራ ብቻ ረክተን አንቀመጥ።እስቲ በዚህች ስራችን ላይ ተጨማሪ ሙያወችን እንደራርብባት።

አንዳንድ ሐኪሞችና አስተማሪዎችን አውቃለሁ። ቀን በመንግስት መስሪያ ቤት ይሠራሉ ማታ በትርፍ ጊዜያቸው ደግሞ ሌላ ሥራ ይሠራሉ። ሐኪሙ ያክማል አስተማሪውም ያስተምራል። አንዳንድ ሐኪሞችንና አስተማሪዎችን ደግሞ

አውቃለሁ :: ሰውንም ገንዘብንም የሚያተርፍ አዕምሮ ተሰጥቷቸው፡ ከመደበኛው ሥራ ውጪ የማይሠሩና ትርፍ ጊዜያቸውን ዝም ብሎ በዋልፈሰስ በመጠጥ ቤትና በዳንኪራ ቤት በእንቶ ፈንቶ የሚያሳልፉ አሁን ከሚኖሩት ኑሮ የበለጠ ማደግና ሀገራቸውንም ማሳደግ ሊችሉ ግን በአንድ ሥራ ብቻ ረክተው የተቀመጡ:: እስቲ ሥራ ፈጥረን የተለያዩ ሥራዎችን እንስራ የሰው ኃይል እኮ ዕምቅ ነው:: ሌሊት በጥበቃ / በዘበኝነት/ የሚሠራ ሰው ቀን ግማሽ ቀን ከተኛ በኋላ ግማሽ ቀን የሚሠራው ሥራ ሊኖረው ይገባል:: ሙሉ ቀን ተኝቶ መዋል የለበትም:: በእኔ አመለካከት ግማሹን ቀን ሱቅ በደረቴ መስራት አለበት ወይም ሌላ ሊያገኘው የሚችለው ሥራ / ሱቅ በደረቴን ሥራ የመረጥኩት እስከአሁን የንግድ ፈቃድ የማይጠየቅበት ሥራ ስለሆነ ነው/::

ከአንድ በላይ ሥራ ለመስራት ሥራን መፍጠር ያስፈልጋል:: አንድ ወቅት ላይ አዲስ አበባ ብሔራዊ ትያትር አካባቢ ያሉ ሊስትሮዎች ያደረጉትን የሥራ ፈጠራ ሰምቼ በጣም ተደነኩ:: ጉዳዩ እንዲህ ነው:- በሐይለኛ የክረምት ወቅት እዚያ አካባቢ ያሉ የአስፋልት መንገዶች በውኃ ይጥለቀለቃሉ ታዲያ የቱ ቀጥ ያለ መንገድ ይሁን የቱ ጉድጓድ ተለይቶ ሰለማይታወቅ ሰዎች ገብተው ለመሻገርና ታክሲ ይዘው ወደ ቤታቸው ለመሄድ ይቸገራሉ:: በዚህ ጊዜ እዚያ አካባቢ ያሉ ሊስትሮዎች ለአንድ ሰው 50 ሳንቲም በማስከፈል አዝለው አስፋልቱን ያሻግራሉ:: ታዲያ አንዱ ሊስትሮ አንድ ወፍራም ሴት ተሸክሞ መሀል እንደደረሰ እንዲህ አለ፤ እማማ በጣም ስለከበዱኝ በ50 ሳንቲም አላሻግረዎትምና አንድ ብር ያደርጋሉ አላቸው:: እሳቸውም

አማራጭ የላቸውምና በተጨመረው ጊዜያዊ ጭማሪ ተሰማምተው ተሻገሩ:: አንዳንድ ጊዜ ሁኔታዎች ራሳቸው ካስተዋልን ሥራ እኮ ይፈጥራሉ እስቲ በአካባቢያችን የአየሩ ሁኔታ ፤የፖለቲካው ሁኔታ አጠቃላይ የጊዜው ሁኔታ የፈጠራቸውን አጋጣሚዎች አስተውለን ጊዜው ሳያልፍ ዕድሎቹን ሁሉ በአግባቡ እንጠቀምባቸው::

አንድ የምወደውና የማከብረው ጓደኛ አለኝ ::የበርካታ ሙያዎች ባለቤት ነው:: መካኒክ ነው፤ ኤለክትሪሽያን ነው፤ የቧንቧ ሠራተኛ ነው፣ አናፂ ነው ፣ መሐንዲስ ነው ካቦ ነው ወንጌል አስተማሪ ነው:: የዕድር ዳኛ ነው / የሀገር መሪነትንም ቦታ ቢያገኝ የሚለቅ አይመስለኝም/ አማካሪ ነው፤ ሾፌር ነው፤ባጠቃላይ ብዙ ሙያ ያለው ሰው ነው::እንደርሱ ዓይነት ሰዎች ቢበዙ ለምድራችን ችግር መፍትሔ ይሆናሉ:: ይህ ሰው ታዲያ በምንም አይነት አንድም ስከንድ ይሁን ጊዜውን በከንቱ አያሳልፍም::በጣም ደስ ከሚለኝ ባህሪው ደግሞ የዚህ ሁሉ ሙያ ባለቤት ነኝ ብሎ አለመኩራቱና ያለውን እውቀት ወይም ሙያ ለሌሎች ለማካፈል መጣሩ ነው:: ይህ ደግሞ ከአንድ ከበሰለና ለአገር ከሚቆረቆር ዜጋ የሚጠበቅ ነው:: እንዳንዶች ብዙ ዘመን እውቀት እና ልምድ ሳያካፍሉ በራሳቸው እንደኮሩ ድብቅ አድርገው ወደመቃብር ይወርዳሉ፡ ይህ አይነት አስተሳሰብ አገርን አያሳድግምና ሊታረም ይገባዋል:: ሙያችንን በሕይወት እያለን ለሌሎች ወገኖቻችን ልናወርስ እርስ በእርሳችንም ስለ ሥራ ፈጠራ ልንመካከር ይገባል:: ምክንቱም ዛሬ እንደዚህ የምናደርጋቸው ነገሮች ሁሉ ወደፊት በምድራችን ላይ ስኬትን ሊያጎናጽፉን ይችላሉና::

"ሁልጊዜ ከእናንተ የተሻለ ከሚያውቁ ሰዎች ጋር ለመዋል ሞክሩ" የሚል አንድ የቆየ አባባል አለ። በእርግጥ ይህን ማድረግ ቀላል ነው። ምክንያቱም የሚከብደው በአንድ ነገር ላይ ከእኛ የተሻለ ዕውቀት ከሌለው ሰው ጋር መዋል ነው።መንገድ ላይ የመኪና ጐማ ስቀይር ከአንድ ጐዳና ተዳዳሪ የሰማኋቸው የህይወት አስገራሚ እውነታዎችን ሁሌም አልረሳቸውም። ከዚህ ሌላ በአንድ ወቅት ከከተማ ወጣ ብሎ በሚገኝ አካባቢ ስጓዝ ያገኘሁት የፖሊስ አባል ብዙ የማላውቃቸውን ቁም ነገሮች አስጨብጠኖል። አዎን፣ በየጊዜው እንዲህ ያሉ ጠቃሚ መረጃዎች ብዙም ከማንጠብቃቸው ሰዎች እንቃርማለን።

ከጥቂት ዓመታት ቀደም ብሎ አንድ ፋብሪካ አዲስ የመስታወት መስኮት ለገበያ አቅርቦ ነበር። ባለቤቱ ሲናገሩ አሳቡን ያገኙት ከአንድ የታክሲ ሾፌር ነበር ይላሉ። ከአስር ዓመት በፊት አንድ የተለያዩ መሳሪያዎችንና ማሽኖችን የሚያመርት ፋብሪካ ከአንድ የተለየ ማሽን ከፍተኛ ገቢ ሲያገኝ ቆይቷል። የሚገርመው የዚህ ማሽን ፈጣሪ የሆነው መሐንዲስ በመጀመሪያ አሳቡን ያገኘው በአንድ ወቅት የባህር ጉዞ ሲያደርግ ከጀልባው ባለቤት ነበር።አንድን ሰው አንዲሁ በማየት በጭንቀላቱ ውስጥ ያለውን አሳብ ማወቅ አይቻልም። ብዙ ዝቅ ተደርገው የሚገመቱ ሰዎች በጭንቀላታቸው ውስጥ ትላልቅ ሀሳቦች ይኖሩዋቸዋል ። ዛሬ ዝቅተኛ ቦታ ላይ የተቀመጠና ተራ ኑሮ የሚኖር ግለሰብ ነገ የተሻለ ስፍራ ላይ የማይደርስበት ምንም ምክንያት የለም። በህይወታችን ውስጥ ለሰው ልጆች ሁሉ ሀብታምም ሆነ ድሃ፣ የተማረም ሆነ ያልተማረ፣ የተሳካለትም ሆነ የልተሳካለት በእኩልነት መቅረብና ማስተናገድ ይገባናል። ይህ መልካም ነገር በመሆኑ ብቻ ሳይሆን ለእኛም ጠቀሜታ

ስለሚኖረው ነው። የብዙዎቻችን ችግር አንዲት ሙያ ካለችን ራሳችንን በዛች መስመር ገድበን መኖራችን ነው። በአንድ ሙያ ውስጥ ሆነን የተወሰነ ውጤት ካየን፣ በዚች ምድር ላይ ከእኛ ስራ ወይም ንግድ ውጭ ሌላ ነገር ያለ መሰሉ አይታየንም። ይሄ ደግሞ የግል የንግድ ተቋም ሰናንቀሳቅስም ሆነ በደመወዝ ተቀጥረን ስንሰራ የሚያጋጥመን ነገር ነው።

በእርግጥ አንድ ሰው ስራውን ወይም ንግዱን ሊወድ ይገባል። ግን ሌሎች ሰዎችም የተሻለ ንግድ እያንቀሳቀሱ እንደሆነ ወይም ጥሩ ሥራ እንዳላቸው እውነታውን ሊቀበል ይገባል። ከእነዚህ ሰዎች ብዙ የምንማረው ነገር ይኖራል። ከማንም ጋር መገባባትና አሳብ መለዋወጥ ልምዳችንን ያዳብርልናል፤ የአስተሳሰብ አድማሳችንንም ያሰፋዋል። ዘወትር ሥራችንን የሙጥኝ ብንል የማናገኛቸውን አዳዲስ አሳቦች እናገኛለን። ከዚህ ሌላ አዳዲስ ባልንጀሮችንም ለማፍራት ይረዳናል። እነዚህ ሰዎች ደግሞ አንድ ቀን ሊረዱን ይችላሉ። በመጀመሪያ ደረጃ ዓለማችን ራሷ የሰው ልጆች እንጂ የነገሮች መኖሪያ እንዳልሆነች ልብ ልንል ይገባል። በእርግጥ የተለያዩ ጠቃሚ ነገሮችን ይዛለች። ሆኖም እነዚህ ነገሮች የሰው ልጆች የፈጠራ ውጤቶች መሆናቸውን መዘንጋት የለብንም። ችሎታችን፣ ሙያችን፣ ተሞክሮአችን በሰዎች አማካኝነት እንጂ በሌላ በምንም መንገድ ወደተፈለገበት አላማ ሊደረስ አይችልም። ስለዚህ ከተለያዩ ሰዎች ጋር በተግባባንና ብዙ ነገሮችን እያወቅን በሄድን ቁጥር ለስኬታችን መንገድ እንጠርጋለን።

በየትኛውም የሙያ መስክ ቢሆን የወደፊት ስኬታችን ቀድሞ ስናከናውነው በቆየነው እና አሁን በምናከናውነው ተግባር

ሥራ ... ሥራ ... በአገርህም ኩራ!

ላይ የተመሰረተ ነው። አሁን እያከናወናቸው ያሉ ሰራዎች ወደ ስኬት እንዲያሻግሩን ለማድረግ የሚከተሉትን ዘዴዎች መጠቀም እንችላለን። ለዚህም ለራሳችን የሚከተሉትን ጥያቄዎች እናቅርብ፦

1. ይህ ስራ አሁን ምን ያስገኝልኛል?

2. ወደፊትስ ከዚህ ስራ የማገኘው ጥቅም ምንድነው?

በእርግጥ አንድን ስራ ወይም ንግድ በአጭር ጊዜ የሚያስገኝልኝን ጥቅም ወይም ትርፍ ከግምት ውስጥ ማስገባት ጠቃሚ ነው። ሆኖም ይህ ወደፊት ልናገኝ የምንችለውን ጥቅም ሊጋርደው አይገባውም። ብዙ ሰዎች በተለይ ደግሞ ወጣቶች አዲስ ስራ ሲያገኙ የመጀመሪያ ትኩረታቸው ደመወዙ ላይ ነው። ይሁንና አዲስ ስራ ስታገኙ ሶስት ነገሮችን መመልከት ተገቢ ነው፦

1. ለአሁን በቂ ገንዘብ የምታገኙበት መሆኑን፣

2. ወደፊት ሊጠቅማችሁ የሚችል ስልጠና፣ ልምድ እንዲሁም ሌሎች ዕድሎችን የምታገኙበት መሆኑን፣

ወደፊት ሊጠቅሟችሁ ከሚችሉ ሰዎች ጋር ለመተዋወቅ በር የሚከፍት እንደሆነ።

አንዳንድ ስራ ደመወዙ የተሻለ ስለሆነ ብቻ የምትገቡበት ከሆነ ስህተት ላይ ልትወድቁ ትችላላችሁ። ምክንያቱም ይህ ሥራ ወደፊት ትምህርትና ልምድ እንድትቀስሙ ዕድል የማይፈጥርላችሁ ሊሆን ይችላል። በተጨማሪም በተለያየ መልኩ ሊረዱዋችሁ ከሚችሉ ሰዎች ጋር የመተዋወቅ ዕድሉን

ላታገኙ ትችላላችሁ፡

የራሳችሁን እንዲሁም ሌሎች የምታውቋቸውን ሰዎች የስራ ህይወት ለለፍታ ለመቃኘት ሞክሩ። እነዚህ ሰዎች ዛሬ ያሉበት ደረጃ ለመድረስ በፊት ከነበሩበት ተቋም የቀሰሙት ልምድ ወይም ያፈሯቸው ጓደኞቻቸው የራሳቸው የሆነ ድርሻ ይኖራቸዋል።ልትገቡበት የምታስቡበት ስራ ወደፊት የማደግና የመሻሻል ራዕያችሁን ዕውን የሚያደርግ መሆን አለመሆኑን ራሳችሁን ጠይቁ። ይህንን ካሰተዋላችሁ፣ ለወደፊት ህይወታችሁ ፅኑ መሰረት ታኖራላችሁ።" ይሽ ሁሉ እንግዲህ ምንድን ነው በአንድ ሥራ ብቻ ረክተን መቀመጥ የለብንም ለማለት ነው። ይህንን ከላይ ያነሳሁትን አሳብ የሚያጠናክር አንድ ነገር እንደሚከተለው ላካፍላችሁ።

ከቻይናዎቹ ጋር አብሮ መስራት የሚፈልግ አንድ ሰው ነበር።መሐንዲስ ነው አና የመሐንዲስ ባለሙያ ፈልገው የሥራ ማስታወቂያ ሲያጡ አንብቦ ሄደ ተፈትኖ ለምን እንደወደቀ እየቆጨው እንዲህ ሲል አጫወተኝ። በየተራ እየገባን ቃለመጠይቅ ተደረገልን። የትምህርት መረጃዎቻችንን ፊት ለፊት አስቀምጠው አንድ በዕድሜ ጠና ያሉ ቻይናዊ ከአንድ ኢትዮጵያዊ ጋር ሆነው ከሥራ ጋር የተያያዙ ብዙ ጥያቄዎችን በትርጉም እንዲህ እያሉ ጠየቁኝ፦

ምን ምን ሥራ ትችላላህ? መሐንዲስ ነኝ ሳይት ላይ መስራት እችላለሁ አልኳቸው። ሌላስ አሉኝ ሌላ አልችልም አልኳቸው

ዶዘር ላይ መስራት ትችላለህ ? አልችልም

- መንጃ ፈቃድ አለህ? የለኝም

- ግንበኝነት ትችላለህ? አልችልም /እኔ እኮ መሐንዲስ ነኝ አልኩኝ/ ባጠቃላይ መልሴ ሁሉ ስላላጠገባቸው "እኛ የምንፈልገው ሁለገብ ሠራተኛ ነው። ሁሉንም መስራት የሚችል፤ አንተ አንድ ሙያ ብቻ ነው ያለህና ላወጣነው ሥራ በቂ አይደለህምና ይቅርታ አድርግልን›› ብለው ሸኙኝ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በውስጤ ብዙ ነገር ተጫረብኝ። እኔ አንድ ሙያ ብቻ ይዤ እስከመቼ ብዬ እስቲ መንጃ ፈቃዱን እንኳ ልጀምር ብዬ ጀመርኩ ተሳክቶልኝ አወጣሁ። ሌሎችንም ሙያዎች ለመማር ወደፊት ራሴን እያዘጋጀሁ ነኝ ብሎ አጫወተኝ።አም ጤናና እድሜ ፈጣሪ ከሰጠን አዕምሮአችንን ዝግ አድርገን መቀመጥ የለብንም ።በዕውቀት ላይ እውቀት፤ በሥራ ላይ ሥራ እየጨመርን ልንተጋ ይገባናል። ያን ጊዜ ነው አገራችን ኢትዮጵያ የዳቦ ቅርጫት የምትሆነው።

በነገራችን ላይ ኢትዮጵያችን የዳቦ ቅርጫት እንዳትሆን እንቅፋት የሆነባት በአንድ ሥራ ብቻ ረክቶ መቀመጥ ሳይሆን። ያለንን ጥሬ ኃብታችንንም በትክክል አለመጠቀማችን ነው። ታዲያ ጥሬ ኃብታችንን ለመጠቀም ምን እናድርግ?

አሥራ አንድ ድኃ ወንድሞች ያሉት ኃብታም ሰው ትንሽ ቆይቶ አሥራ ሁለተኛ ድኃ ይሆናል

ምዕራፍ አስራ ሁለት

ኢትዮጵያችን የዳቦ ቅርጫት የምትሆነው ጥሬ ኃብታችንን በትክክል መጠቀም ስንችል ነው።

አገራችን ኢትዮጵያ ብዙዎችን የሚያስጎመጅ ገና ያልተነካ ጥሬ ኃብት ያላት ሀገር መሆኗን እንኳን ወዳጆቿ ጠላቶቿም ይመሰክሩለታል። በዓለም ላይ ካሉ 200 አገሮች ውስጥ የ13 ወር ፀጋ የለበሰች ሀገር ብትኖር ኢትዮጵያችን ነች።አየሩ ተስማሚ አፈሯ ለም ነው። በውስጧ ያለው ማዕድንና የከበረ ድንጋይ ተዝቆ የሚያልቅ አይመስለኝም ። **የበሬ ግምባር የምታህል መሬት ይዘው ሌሎች አገሮች ሊበልጡን አይገባም።** ወንዙ ሸንተረሩ ግሩም ነው ሀገሩ። ታዲያ እኛ ህዝቦቿ በዚህ ጥሬ ኃብት እየተጠቀምን ነው ወይስ በጥሬ ኃብታችን ላይ ቁጭ ብለን እጃችንን አጣምረን እያጉረመረምን ነው? የጥያቄውን ምላሽ ለእያንዳንዳችን እየተውኩ እኔ ግን ወደፊት ማድረግ የሚገባንን ነገር ልጠቁም እወዳለሁ።

1. የአሥራ ሦስት ወር ፀጋ እያሉ መዘመር ብቻውን በቂ አይደለምና በዚህ በተሰጠን ፀጋ ተጠቅመን አገራችንን ለማልማት እንነሣ። በአሜሪካ ሀገር ሰዎች በሙቀት እንደሚሞቱ በሚዲያ /በዜና/ ሰምቻለሁ ።በእኛ ሀገር በሙቀት ሞተ የተባለ ሰው የለም /ሰምቼ አላውቅም/መቼ የሚገለው ሙቀት ተሰጠንና።

2. በውጭ ሀገርም ያሉ ኢትዮጵያዊያን ሁሉ የሀገራቸው ኃብት ገና ለትውልድ ሁሉ ይተርፋልና በዚህ የ13 ወር ፀጋ

ተጠቅመው ምድራቸውን እንዲያለሙ በሀገራቸው ጥሬ ኃብት ሀገራቸው ላይ ኢንቬስት እንዲያደርጉ በዜግነቴ ጥሪዬን አቀርባለሁ። አብዛኞቹ ማዕድን የሚያወጡልን ሰዎች የውጭ አገር ዜጎች ናቸውና እስቲ እኛም እንበርታ፡

• ጫካውን ለግብርና እርሻና ለከሰል በማለት ከማቃጠልና ከመመንጠር ታቅበን ሌሎች ደኖችና ጫካዎች እንዲበዙ ኢትዮጵያችን ለምለም አረንጓዴ ለብሳ እንድትኖር መንግስት በቀየሰልን አንድ ሰው ሁለት ዛፍ በሚለው ግሩም ራዕይ እንሳተፍ ።ለተከልነውም ችግኝ አድጐ ጥላ እስኪሆነን ድረስ እንከባከብ። ደን ከሌለ ዝናብ የለም። ዝናብ ከሌለ የሚጠጣ ውኃ የለም ። **ውኃ ከሌለ ደግሞ ኤለክትሪክም የለም** ። ስለዚህ የጨለማ ጉዞ እንዳይሆንብን እንንቃ።

አባይ ሞላልሽ ብሎ ማዜም ብቻ እንደማያዋጣ አውቀን፤ የሞላውን አባይ እንዴት ለአገር ጥቅም እናውለው የሚለውን ልናስብበት ይገባናል። አዋሽ የኢትዮጵያን አፈር ጠራርጐ ይዞ ሳይወጣ እዚሁ ኢትዮጵያ ውስጥ የአፋር ምድር አሸዋ ውስጥ ገብቶ ይቀራል። በአሁኑ ጊዜ ራሱ መንግስት በአዋሽ ወንዝ ላይ እየሰራ ያለው ሥራ የሚያበረታታ እና እሰየው የሚየሰኝ ነው። ነገር ግን የምድራችንን አፈር ጠራርጎ ሳይራራልን ለግብጽ ቸርነት ለማድረግ ሌት ተቀን የሚገስግሰውን የአባይንም ጉዳይ ከጎረቤታችን ከግብጽ ጋር በማያጣላ ሁኔታ አብረን እናስብበት እላለሁ። የዝናብን ወቅት ብቻ እየጠበቅን ከምንገላታ፡ ወንዞቻችንን በትክክል ተጠቅመን የመስኖን ስራ ብናዳብር የአገራችን አየር የማይቀበለው የእህል ዘር የለምና አትራፊዎች እንሆናል።

በአገራችን አየሩ የማይቀበለው አፈሩ የማያበቅለው የእህል ዘር እምብዛም የለም። ለዚህ እንደ አብነት ይሆነን ዘንድ ሶስት

የሰው አገር ዘሮች አቀርባለሁ።

"ባህር ዛፍ" ከስሙ እንደምንረዳው ባህር ዛፍ ኢትዮጵያዊ አይደለም። ከባህር ማዶ ነው የመጣው። ግን በእንግድነት መጥቶ ይኸውና ዛሬ ባለቤት ባለ ሀገር ሆኖ ጆሮውንም ቢቆርጡት ወደ አውስትራሊያ መልሱኝ ቤተሰቦቼ ናፍቀውኛል የሚልም አልሆነም። ለምን? አየሩና አፈሩ ተስማምተውታላ። ከሰውም ጋር ተስማምቶና ምልክት ሆኖ ይኖራል፤ ባህር ዛፍ ባለበት ሁሉ ሰው አለና።

"ባርማሽላ" ይህም የእህል ዘር አንደ ባህር ዛፍ እንግዳ የውጪ ሀገር እህል ነበር ነገር ግን የኢትዮጵያ አየርና አፈር የማይቀበለው የለምና ይኸውና አልምዶት ዛሬ ቤተኛ ሆኖ ተፈላሶ ማሳ ሞልቶ ይኖራል።

"አፕል" ይህም ኢትዮጵያዊ አይደለም ከውጪ ከSIM ፈረንጆች ጋር መጥቶ እዚሁ አየሩና አፈሩ ተስማምቶት እየተስፋፋ እንደሆነ የጨንታ ገበሬዎች ይመሰክራሉ። እነዚህን ሶስት ዘሮች ያነሣሁት፤የሀገራችን አየርና አፈር የማይቀበለው የለም የሚለውን አሳብ ለማስገንዘብ ነው። እግዚአብሔርም ጥሩ አገር ሰቶናል ለማለት ነው። ታዲያ እኛ እዚህች ለሁሉም ተስማሚ የሆነች አገር ላይ ቁጭ ብለን ድኃ ነኝ ብለን ማውጅ የለበንም።

ድኃ ማለት አዕምሮውን ያጣ እንጂ ኃብት ንብረት ያጣ አይደለም። እንኪን ሙሉ አካል ይዘን አካላችን እንኪ ቢጉድል አዕምሮአችን ብሩህ እስከሆነ ድረስ መስራት እንችላለንና።

ጃኒ ኢሬክሰን የተባለች ሴት ውኃ ዋና ስትዋኝ በደረሰባት አደጋ ሁለቱን እጆቿን ጨምሮ ከወገቧ በታች የማትንቀሳቀስ ፓራላይዝድ ሆናለች። ሆኖም በዓለም ላይ የታወቀች ሰዓሊና

የወንጌል ሰባኪ ነች። የምትስለው ታዲያ በአፏ ነው ።የጃኒ ስዕሎች በዓለም ላይ እጅግ ውድ ዋጋ ያወጣሉ። እንግዲህ እግዚአብሔር የሰጠንን አካልና የተፈጥሮ ፀጋ ተጠቅመን እንሰራ እንጂ ላለመስራት ምንም ምክንያት የለንም። የኢትዮጵያ ተስፋዋ እግዚአብሔር፤ ህዝቧና፤መሬቷ ናቸውና። እስቲ ሁላችንም ፈሪሃ እግዚአብሔርን ተላብሰን ለሥራ በመታጠቅ ቸሩ ፈጣሪ የሰጠንን ጥሬ ኃብት ተጠቅመን አገራችንንና አራሳችንን ለማሳደግ እንጨክን።

አንድ ቀን የቀለበት መንገድ ሲሰራ ትልልቅ መኪናዎች ድንጋይ እያመጡ በወረፋ ሆነው ሲዘረግፉ አየሁ። ከየት ነው የሚያመጡት ብዬ ሳይ ከመንደሩ ማዶ ካለው ለዘመናት የአካባቢው ሰው የአድባር ደም ከሚያፈስበት ተራራ ስር ነው እየቆፈሩ የሚያመጡት ለካ፤ ይገርማል እኛ አጠገቡ ሆነን ስንሳለመው ስናጥንለት ኖርን ቻይናወቹ ግን ከውጪ መጥተው የእኛኑ ጥሬ ኃብት በመጠቀም መንገድ ሰሩልን። ምንድነው ልዩነቱ ? ጥያቄውን አንባቢ ይመልስ፤ ሆኖም ቻይናዎቹ መንገድ የሚሰራበትን ጥሬ ኃብት የሆነውን ድንጋይ አፈር አሸዋ እንጨት ውኃ አሌክትሪክ ሌላም ሌላም ከውጪ አላመጡም። እዚሁ እኛው ጋር ያለውን ነው የተጠቀሙት። እኛ ለሥራ እንጨክን እንጂ ብዙ ገና ያልተነካ ጥሬ ኃብት አለን አዕምሮአችንንና ጉልበታችንን ተጠቅመን ስንነሳ ውጤታችን ያማረና የሰመረ ይሆናል። አገራችን ከዳቦ ቅርጫ ወጥታ የዳቦ ቅርጫት ትሆናልች።

ኢትዮጵያ የምትለወጠውና የምትበለጽገው በሥራ ነው:: ኢትዮጵያዊ የሆነ ሁሉ ክቡር ለሆነው ሥራ ጊዜውን፣ ዕውቀቱንና ጉልበቱን ቢሰዋ አገሩን ከዳቦ ቅርጫነት ወደ ዳቦ ቅርጫትነት ይለውጣታል! የዚህ መጽሐፍም ዐብይ የትኩረት አቅጣጫ ነው::

የሰባኪው ምሳሌና ሁለት ጉልቻ የተሰኙትን መጽሐፍት ለእንባቢያን ያቀረበው ወንጌላዊ ደመወዝ አበበ ሥራ ሥራ በሚል ርዕስ ይህን መጽሐፍ ደግሞ ለንባብ አብቅቶአል:: በእግዚአብሔር ቃል ላይ የተመሰረተ፣ በብዙ ምሳሌዎችና ገጠመኞች ጣፍጦ ውብ በሆነ አጻጻፍ የቀረበ ተነባቢ መጽሐፍ ነው:: ስራ ካልሰራን ለእግዚአብሔርም ሆነ ለሰው እንደማንመች፣ እግዚአብሔር ስንፍናን የሚጠላ አምላክ እንደሆነ የቤተ ክርስቲያንና የመንግስት ድርሻም መሆን እንዳለበት መጽሐፉ ቅልብጭ አድርጎ ያሳያል::

ይህንን መጽሐፍ በእጁ ያስገባ ሰው ካነበበው በኋላ ስለ ሥራ ያለው አመለካከት ሙሉ በሙሉ እንደሚለወጥ እርግጠኛ ነኝ:: ስለዚህ መጽሐፍ ደራሲውን ከሁሉም በላይ መገለጥን የሰጠውን እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ::



አቶ ደረሰ ብሩ

የኢ.ወ.ቤ.ክ.መ.ኢ. የምሥራች ድምፅ የመገናኛ ዘዴዎች

አገልግሎት ጎትመት መገናኛ ዘዴ ክፍል ኃላፊ

በነገራችን ላይ ኢትዮጵያችን የዳቦ ቅርጫት እንዳትሆን እንቅፋት የሆነባት ጉዳይ ጥሬ ኃብታችንን በትክክል አለመጠቀማችን ብቻ አይደለም:: አላስፈላጊ ጦርነቶች ውስጥም መግባት ጭምር እንጂ:: ታዲያ አላስፈላጊ ጦርነቶች ውስጥ እንዳንገባ ምን እናድርግ?

ቀና ቀና ያለ ማሸላ
ወይ ለወፍ
ወይ ለወንጭፍ
ይሆናል።

ምዕራፍ አስራ ሦስት

ኢትዮጵያችን የዳቦ ቅርጫት የምትሆነው አላስፈላጊ ጦርነቶች ውስጥ መግባትን ስናቆም ነው።

ከአፍሪካ አህጉር ውስጥ ኢትዮጵያና ላይቤሪያ የሚታወቁት በቅኝ ግዛት አለመያዛቸው ነው። ይህ ደግሞ በተለይ ለእኛ ለኢትዮጵያውያን ኩራት ነው። ሆኖም ብዙ ዘመን ኢትዮጵያ በጦርነት አሳልፋለች። ከግብፅ፣ ከእንግሊዝ፣ ከጣሊያኖች ኦርስ በኦርስ ከሶማሊያ እንዲሁም ከኤርትራ ጋር። ታዲያ እነዚህ ሁሉ የሰው ኃይል የገንዘብ ኃይል እና ጊዜን አጥፍተውብናል።አንዳንዶቹ ጦርነቶች አስፈላጊ ናቸው። አንዳንዶቹ አስፈላጊ አይደሉም።በእኔ አስተሳሰብ አስፈላጊ ጦርነት የምለው አገርን ለመውረርና ለማጥፋት የሚመጣውን ኃይል እምቢ አላስገባም አገሬን ለሰው አልሰጥም ብሎ በታላቅ ወኔ መከላከልን ነው።ምክንያቱም ሁሉም አገር ፈጣሪ በወሰነለት ድንበርና ክልል መኖር ስለበት።ቃሉም *በሐዋርያት ሥራ 17:27* *<u>...የተወሰኑትንም ዘመኖችና ለሚኖሩበት ስፍራና ዳርቻ መደበላቸው ይላልና ::</u>* በአሁኑ የልማት አካሄድ ኢትዮጵያ ከላይ በጠቀስኳቸውና በሌሎችም ጦርነቶች ባታልፍ ኖሮ እስከዛሬ የኢኮኖሚ እድገቷ ፈጣንና አመርቂ ይሆን ነበረ። አሁንም ተስፋ በእጃችን አለ። በዚህ ርዕስ ሥር ብዙ የምናገረው ባይኖረኝም ላለማደጋችን አንዱ ምክንያት ጦርነት መሆኑን አሳይቼ ወደፊት ይህ ችግር እንዳይደግመን መንግሰት ከጉረቤት ሀገሮች ጋር መልካም የሆነ የዲኘሎማሲ ግንኙነት /Diplomacy/ እንዲያደርግ በአክብሮት አሳስባለሁ። ያን ጊዜ ብቸኛው ጠላታችን ድኅነት ብቻ

ሥራ ... ሥራ ... በአገርህም ኩራ!

ይሆናል።ብቻውን ደግሞ ድኅነት ሊያሸንፈን አይችልምና ድሉ የእኛ መሆኑ አያጣራጥርም። ያን ጊዜ ኢትዮጵያችን የዳቦ ቅርጫ መሆኗ ቀርቶ የዳቦ ቅርጫት ትሆናለች።

በነገራችን ላይ ኢትዮጵያችን የዳቦ ቅርጫት እንዳትሆን ያደረጋት በብዙ ጦርነቶች ውስጥ ማለፏ ብቻ አይደለም ።ነገር ግን ዜጎች ወደ ውጭ ለመሄድ ልባቸው መሸፈቱም ጭምር እንጂ።ታዲያ ዜጐች ልባቸው ወደ ውጪ እንዳይሸፍት ምን እናድርግ?

በአንድ አህያ ከሚመሩ መቶ አንበሶች ይልቅ ፤ በአንድ አንበሳ የሚመሩ መቶ አህዮች ያስፈሩኛል።

ምዕራፍ አስራ አራት

ኢትዮጵያችን የዳቦ ቅርጫት የምትሆነው ውጭ አገር በመሔድ ብቻ ሳይሆን በአገራችንም ጌታ እንደሚባርከን ስናምን ነው።

የድሮ አባቶቻችን እና እናቶቻችን ለተወለዱባት እናት አገራቸው ያላቸውን እውነተኛ ፍቅር ለመግለፅ የሚጠቀሙባቸው አንጀት የሚበሉ አንዳንድ ቃላቶች ወይም አባባሎች አሏቸው ። ለምሳሌ፦ "እትብቴ የተቆረጠባት አገሬ" "የአገሬ አፈር ይብላኝ" "ሁሉም በአገር ያምራል" ሌሎችም ሌሎችም። አንድ ሰው ራሱ ህግ የሚጥስ ሥራ የሚሰራ ከሆነ ሌለው ሰው በህግ አምላክ ወይም በባንዲራው አምላክ ይለዋል ። እነዚህ ሁሉ ኢትዮጵዊነትን ያሳያሉ። ዛሬ ግን በዚህ ዘመን ባለን ትውልዶች ብዙ አይሰማምና ለምን ይሆን ብዬ ራሴን እጠይቃለሁ? ትዝ ይለኛል ትምህርት ቤታችን ጠዋት ወደ ክፍል ገብተን ትምህርት ከመጀመራችን በፊት የኢትየጵያ ህዝብ መዝሙር ዘምረን ባንዲራችንን እንሰቅል ነበር ።ታዲያ ባንዲራ እየተሰቀለ እና መዝሙሩ እየተዘመረ ሁሉም ሰው ባለበት ይቆማል እንጂ የሚንቀሳቀስ የለም። ዛሬስ? ለመሆኑ የዛሬዎቹ ተማሪዎች / የእኛ ልጆች/ የኢትዮጵያን ህዝብ መዝሙር ምንም ሳይሳሳቱ ከጫፍ እስከ ጫፍ ይዘልቁታል? እኛስ አዋቂዎቹ ይህንን ፈተና እናልፍ ይሆን?። ለማንኛውም ኢትዮጵያ አገራችን ባንዲራው ምልክታችን መዝሙሩ የአቋም መግለጫችን ነውና፤ የኢትዮጲያ ዜጎች ለሥራ እና ለፍቅር በእጅጉ የሚያነሳሳውን የኢትዮጵያን ህዝብ መዝሙር ማወቅ ያስፈልገናልና

ለሁላችሁም እንደሚከተለው አቅርቤላችኋለሁ።

የዜግነት ክብር በኢትዮጵያችን ጸንቶ

ታዬ ሕዝባዊነት ዳር አስከዳር በርቶ

ለሰላም ለፍትህ ለሕዝቦች ነጻነት

በእኩልነት በፍቅር ቆመናል በአንድነት

መሰረተ ጽኑ ሰብዕናን ያልሻርን

ሕዝቦች ነን ለሥራ በሥራ የኖርን

ድንቅ የባህል መድረክ የአኩሪ ቅርስ ባለቤት

የተፈጥሮ ጸጋ የጀግና ሕዝብ እናት

እንጠብቅሻለን አለብን አደራ

ኢትዮጵያች ኩሪ እኛም በአንቺ እንኩራ።

ውጪ አገር ከመሄድና በኢትዮጵያ ከመኖር የትኛው ይሻልሀል ብላችሁ ሰዎችን ብትጠይቁ ካልተሳሳትኩ ጥቂት ያልሆነ ቁጥር ያለው ህዝብ ውጪሀገር ብሄድ ይሻለኛል ነው የሚላችሁ፡ እንዳውም አብዛኛው ሰው እድሉን ቢያገኝ መውጣት ይፈልጋል። እኔ አትውጡ ከአገር እያልኩ አይደለም ግን ወጥታችሁ አትቅሩ / አትጥፉ/ እያልኩ ነው እንጂ።ጠንክረን ከሠራን እግዚአብሔር በኢትዮጵያም ይባርከናል እያልኩ ነው እንጂ። አንዳንዳንድ ሰው ደግሞ ወይ አይሄድ ወይ እዚሁ አይሰራ ሁሌ መንገደኛ ሆኖ የሚሰሩትን ልብ እያደከመ ውጪን ተስፋ እያደረገ ያለ ሥራ ይኖራል።

አንዳንድ ውጪ አገር ደርሰው የሚመለሱ ሰዎች ደግሞ የሚነግሩን ነገር ሁሉ ኢትዮጵያን በዚያው ጀምበር አስለቅቆ ወድያው ወደ ውጪ ሂዱ ሂዱ የሚያሰኝ ነው እስቲ እባካችሁ ከውጪ የምትመጡ ወገኖቻችን እኛ በአገር ቤት ያለነውን የአገር ፍቅር የበለጠ እንዲያድርብን አድርጉ እንጂ በማይደረስበት የተስፋ ዳቦ አትሙሉን።እናንተም ወደ እናት አገራችሁ ኑና አብረን እንስራ (አገር ቀሚስ ናትና)። ስለ ውጪው አገር ከነገራችሁንም በግሩም የስራ ስነምግባራቸው እንዴት ድህነትን አሸንፈው እራሳቸውንና አገራቸውን እንዳሳደጉ የሚያሳየንን ጠቃሚ ነገር የሚጠቅመውን ጎን ብትነግሩን።

በጣም የምወደውና የማከብረው ወንድሜ ምህረቱ ጴጥሮስ እንደሚያደርገው ማለት ነው። ምህረቱ በአሁኑ ጊዜ በአሜሪካን አገር በትምህርት ላይ ይገኛል። ሆኖም ምህረቱ ስለ አሜሪካ በጽሑፍም ሆነ በቃል ሲናገር ብትሰሙት አንድ ነገር ላይ ነው የሚያተኩረው "የአሜሪካ እድገት ሚስጥር ትጋት ነውና እኛም ከተጋን የማናድግበት አንዳችም ምክንያት አይኖርም" የሚለው ላይ። እንድያውም አንድ ወቅት በብርሃን መጽሔት ቁጥር 58፣2000 ላይ "ምን እንማር ይሆን?" በሚል ርዕስ ያቀረበውን ጽሑፍ በዚህ መጽሐፌ ላይ እንዳካትት ፈቅዶልኛልና እንደሚከተለው አቅርቤላችኋለሁ። ምህረቱንም ከልቤ አመሰግናለሁ።

ምን እንማር ይሆን?

በእግዚአብሔር ፈቃድና ጊዜ ከአገሬ ኢትዮጵያ ወደ ምድረ አሜሪካ ከመጣሁኝ ጊዜ አንስቶ ራሴን እየጠየቅሁ ያለሁትን

ጥየቄ ለሌሎች አንባቢያን ላጋራ የሚል ውሳኔ ላይ በመድረሴ ሳቢያ ይህን አጠር ያለ መጣጥፍ ልጽፍ የግድ ሆነ፡ "ለመሆኑ ሊያነሳ የፈለገው ጉዳይ ምን ይሆን?" የሚል ጥያቄ በዚህ መጣጥፍ አንባቢ አእምሮ መነሳቱ አይቀርም። ነገሩ እንዲህ ነው፣ ከእኔ አስቀድሞ ወደ አሜሪካን አገር መጥተው ብዙ ዓመት የኖሩ ሰዎች አሉ፣ እኔም ወደዚህ አገር ከመምጣቴ በፊት ስለምድሪቱ ገና ኢትዮጵያ ውስጥ እያለሁ አበው "ያላዩት አገር አይናፍቅም" እንዲሉ በጆሮዬ የሰማሁትን፣ በዓይኔ ያላየሁትን አገር ዕድገት፣ "ከልኩ አያልፍም" በሚለው ቀላል ዓረፍተ ነገር ዘግቼው ነበር። አሁን ግን ያለኝ መረዳት ከዚህ በእጅጉ ተለይቷል። እርግጥ መስማት ጥሩ ነው። ማንበብ ጠቃሚ ነው፡ በዓይን ማየት ደግሞ ከሁለቱም ይልቃል። ራሴን ጨምሮ "ሰው ወደ አሜሪካን አገር ለመሄድ የሚጋደለው ለምን ይሆን? የሚል ልብ አንጠልጣይ ጥያቄ፣ "የዕድሜዬን ግማሽ" ሙሉ ሲያሰጨንቀኝ ከርሟል። ይሁን እንጂ ዛሬ እንዳስተዋልኩት የአሜሪካን አገር ዕድገት ገና በማደግ ላይ ካሉ አገራት ጋር ላነፃፀረ ሰው። በእርግጥ ለአንዱ ነግቶ ለሌላው ደግሞ ገና በጨለማ ላይ እንዳለ እንዲታሰብ ያደርጋል።

ምግብ ጠግቦ መብላት ብርቅ የሆነበት አገር እንዳለ ሁሉ የምግብ ነገር ምን አልባት ፈጽሞ ከጥያቄ ውስጥ የማይገባበት ሀገር ደግሞ አለ። ደንበኛ የሚበላ ነገር ይዞ እስኪሰለቸው ድረስ እንዲበላ፣ "የመብላትን መጥኔ ይስጥህ፣ የቻልከውን ያህል ሞክር" ተብሎ ሜዳውም ፈረሱም ይኸው የሚባልበት አገር ደግሞ አለ። አሜሪካ!! ሰው ይሥራ እንጂ ያገኛል። ያልም እንጂ ይደርሳል፣ይትጋ እንጂ ይካሳል። ለምድራዊ ኑሮ አሜሪካ ጥሩ

ነገር አለው። ይህ ሁሉ ቢሆንም አሜሪካ ሁሉ ነገር ደግ እና፣ ተግዳሮት አልባ አገር ግን አይደለም፣ ብዙ ጥሩ ነገሮች እንዳሉት ሁሉ የመጥፎ ነገሮችም መፍለቂያ እንደሆነ ማውሳቱ እውነትን መካድ አይደለም። መጥፎውን ለጊዜው ገታ እናድርግና ስለ ደግ ደጉ እናውራ።

አሜሪካ ሰውን በእኩይ ምግባሯ ከምትጠልፈው በላቀ ሁኔታ በአገሪቱ በመኖር በምታስገኘው ጥቅም አኪያ የብዙዎችን ቀልብ ስባለች። ይህን እውነት ስለ ምድረ አሜሪካ የሰማ ሕዝብ ከዓለም ዙሪያ ሲተም ይስተዋላል። አሜሪካ አገር ያድርስ እንጂ ሰው ቢዋሽ ያለውን ንብረትና ጥሪቱን ሸጦ ዕድሉን ቢያገኝ፣ በአሥርና በአሥራ አምስት ሰዎች ቤተክርስቲያን ከፍቶ መጋቢ እከሌ ቢባል፣ ሌላም ሌላም ነገር ቢሰራ ምን ገዶት። ከዚህ የተነሳ ይመስላል ገንዘብ ለማግኘት ሲባል በውሸት ጋብቻ "ተጣምሮ" ወደዚያ ምድር ቢሻገርና። በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉትን ኤምባሲዎች ብናይ በዲቪ አመልካች ብዛት በመጨናነቅ የአሜሪካን ኤምባሲን ግንባር ቀደም ሆኖ እናየዋለን። ግን ለምን የዚህን ጥያቄ ምላሽ ለማግኘት አንባቢ ያለመሰልቸት ይህን መጣጥፍ አንብቦ መጨረስ ይኖርበታል።

በሰው ደረጃ ሲታይ በምድር ላይ ምድረ አሜሪካ ያልበለፀገችበት አቅጣጫ አለ ለማለት አያስደፍርም፣ ትምህርት፣ ቴክኖሎጂ ገንዘብ የተማረ የሰው፣ኃይል የጦር ሰራዊት ጥንካሬ ወዘተ... አሜሪካ ለራሷ ያደገች ሀገር የሚፈልሱትን ሁሉ በፍጥነት የመቀየር ኃይል አላት። በአብዛኛዎቹ ደሃ ከሚባሉ ሀገራት የመጡትን መኪና መንዳት ይቅርና ሊሳፈሩበት የሚመኙትን ሰዎች ባለ መኪና

ታደርጋለች። ባለቤት ታደርጋለች። ሌላም ሌላም ብዙ ነገሮችን ሰፈላጊ ታቀርባለች። ታዲያ በብዙዎች በአእምሮ የተሳለችዋ የሕልም አሜሪካ ግን አይደለችም። ይህን ስል አሜሪካ ገንዘብ ከመንገድ ዳር የሚዛቅባት ሀገር አለመሆኗን ልብ ማለት ያሻል። ነገር ግን ለተጋ ሰው የማትሰጠው የሽልማት ዓይነት የለም ለማለት ያስደፍራል።

በአሁኑ ወቅት በአሜሪካን ሀገር ትልቅና በዋናነት አነጋጋሪ የሆነው ጉዳይ የሕገ ወጥ ነዋሪዎች ጉዳይ ነው። በግምት ከ11 ሚሊዩን በላይ የሚሆኑ ሕገ ወጥ ነዋሪዎች በዚህች ሀገር ውስጥ ይገኛሉ። የአሜሪካ መንግስት እነዚህን ሕገ ወጥ ነዋሪ ናቸው ያላቸውን ሰዎች አገር ይልቀቁና ወደ የመጡበት ይመለሱ እያለ ሲሆን፤ ሕገ ወጥ ነዋሪዎቹ ደግሞ "ይህቺን ሀገር ከምንለቅ ሞታችንን እዚሁ ያድርገው" በማለት ላይ ሲሆኑ ከሀገር አታስወጡን በማለትም ሰላማዊ ሰልፎችን እያካሄዱ ናቸው። "ሕገ ወጥ እንኳ ብንሆን ኃጢያታችንን ይቅር ብላችሁ ሕጋዊ ዕውቅናን ስጡን፣ እኛ አሜሪካውያን ነን፣ ሌላ መሄጃ የለንም" በማለት ላይ ይገኛሉ። "ሰርተን ማግኘት እንፈልጋለን ደሃ ቤተሰቦቻችንን እንደግፋቸዋለን ተውን እናንተ አሜሪካውያን" እያሉ ናቸው። በአንድ ወቅት በአሜሪካን አገር በአንድ የሬድዩ ጣቢያ ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸው ኘሬዝዳንት ቡሽ ስለ አሜሪካ ሲናገሩ ያሉትን ላንሳ፣ "አብዛኛው ሰው በዓለማችን አሜሪካንን ለመኖሪያነት ይመርጣታል፤ እኛም የተራቡትን እንመግባለን፣ እኛ አሜሪካውያን ለሌሎች ሰዎች መልካም ነን" ታዲያ አሜሪካንን ካልመረጡ ማንን ሊመርጡ ይችላሉ?

በዚህ ሥፍራ ስለ አማሪካን አነሳን እንጂ፣ ዛሬ አደጉ የተባሉ

አገራት ሁሉ ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ በማደግ የታወቁ ሳይሆኑ ከዜሮ ደረጃ ጀምሮው አሁን ወዳሉበት ደረጃ የደረሱ ናቸው። እነዚህ አገራት በአንድ ወቅት በማጣት ትግል ውስጥ ያለፉና የድህነትን ኩርኩም የቀመሱ ናቸው። ለመሆኑ ዛሬ ምን ይሆን እንዲህ የለወጣቸው? እስቲ የዚህን ነጥብ እውነትነት ለማሳየት ይረዳኝ ዘንድ በቅርቡ ያገኘሁትን እና ከዛሬ አንድ መቶ ዓመት በፊት የነበረውን የአሜሪካንን የኑሮ ደረጃ ሁኔታ የሚያሳይ መረጃ ላስቀምጥ።

- የሕይወት ጣራ 47 ዓመት ነበር።
- 14% ያህል ቤቶች ብቻ መታጠቢያ ነበራቸው።
- 8% ቤቶች ብቻ የስልክ ተጠቃሚ ሲሆኑ ከዴንቨር ወደ ኒውዮርክ የሶስት ደቂቃ ጥሪ ለማድረግ አስራ አንድ ዶላር ይከፈላል።
- በመላው አገሪቱ 8000 መኪናዎች ብቻ ሲኖሩ በአስፋልት የተሸፈኑ መንገዶች ደግሞ ከ144 ማየልስ አይበልጡም።
- ትልቁ የፍጥነት ወሰን በሰዓት ከአሥር ማየልስ አይዘልም።
- አላባማ ሚስስፒ፣ አይዋሃ እና ቴናሲ እያንዳንዳቸው ከካሊፎርኒያ በላይ የሰው ብዛት ነበራቸው።
- የካሊፎርኒያ ግዛት 1.4 ማሊዮን ሕዝብ በመያዝ በሃያ አንደኛ ደረጃ ላይ ነበረች።
- አንድ ፖውንድ ስኳር በአራት ሳንቲም ይሸመታል።
- አንድ ደርዘን እንቁላል አሥራ አራት ሳንቲም ያወጣል።
- አንድ ፖውንድ ቡና አሥራ አምስት ሳንቲም ይሸጣል።

- አብዛኛዎቹ ሴቶች ፀጉራቸውን በወር አንዴ የሚታጠቡ ሲሆን የእንቁላል አስኳል ደግሞ እንደ ሻንፑ ጥቅም ላይ ውሏል።
- ካናዳ ድሆች በምንም ምክንያት ወደ ግዛቷ እንዳይገቡ የሚያግድ ሕግ አላልፋ ባታላች።
- አምስቱ ግምባር ቀደም የሞት ምክንያቶች፣ ኒሞኒያና ጉንፋን፣ የሳንባ ነቀርሳ፣ ተቅማጥ፣ የልብ በሽታና የደም ግፊት ነበሩ።
- የአሜሪካ ባንዲራ አርባ አምስት ከዋክብት ነበሩት።
- ደመወዝ በአማካይ በሰዓት ሃያ ሁለት ሳንቲም ይደርሳል።
- በአማካይ የአመት ደመወዝ ሁለት መቶ ዶላር እና አራት መቶ ዶላር ነበር
- ጉብዝ የሂሳብ ሰራተኛ በዓመት እስከ ሁለት ሺ ዶላር የጥርስ ሐኪም ሁለት ሺህ አምስት መቶ የእንስሳት ሐኪም አንድ ሺህ አምስት መቶ እና አራት ሺ ዶላር ኢንጅነር እስከ አምስት ሺ ዶላር ያገኙ ነበር።
- ከ95% በላይ ሴቶች ቤት ውስጥ ነው ልጆቻቸውን የሚወልዱት።
- 90% የአሜሪካ ዶክተሮች የኮሌጅ ትምህርት አልነበራቸውም።
- አሪዞና፣ አክላሆማ፣ ኒው ሜክሲኮ ሃዋይ እና አላስካ የአሜሪካ ጎብረት አካል አልነበሩም።
- <u>የላስ ቬጋስ፣ የኔቫዳ ሕዝብ ከሰላሳ አይበልጥም።</u>

- ከአሥር አሜሪካዊ ጉልማሳ ሁለቱ ማንበብ ወይም መፃፍ አይችሉም።
- 6% አሜሪካውያን ብቻ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት አጠናቀዋል።
- 18% የአሜሪካ ቤተሰቦች ቢያንስ አንድ የሙሉ ጊዜ ሰራተኛ ወይም የቤት እርዳታ ነበራቸው።

በመላ አሜሪካ 230 የግድያ ወንጀሎች ብቻ ተመዝግበዋል።

ዛሬ አሜሪካንን በወሬና በንባብ በቻ ሳይሆን በዓይኑ ላያት ዕድገቷ የመቶ አመት ሳይሆን የበርካታ ምዕተ ዓመታት ውጤት ይመስላል። ሰው ሳይሆን መላዕክት ከሰማይ ወርደው ያበለፀጓት ይመስላል። እንግዲህ በመቶ ዓመት እነኚህ ተግዳሮቶች ሁሉ ተወግደው ምድረ አሜሪካ ዛሬ ዓለምን በውዴታም ይሁን በግዴታ እገዛለሁ አቅም አለኝ እስክትል ያበቃት ምስጢሩ ምን ይሆን? እንዲያውም እግረ መንገዴን ላንሳና በጣት የሚቆጠሩ ዓመታት ውስጥ ራሳቸውን አበልጽገው ምድረ አሜሪካንን ካልተቆጣጠርን እያሉ ያሉትስ ቻይናና ሕንድ እንዴት አቅም ሊያገኙ ይችላሉ? አስተዋይ ልቦና ያለው ሊያስብበት የሚገባ ይመስላል።

በርግጥ አሜሪካንን ሳይሆን ስለ አሜሪካ የሚያውቅ ሰው ነገሬ ብዙም ላይጥመው ወይም ላይጥማት ይችል ይሆናል። ነገር ግን አማሪካንን በዓይኑ ያየ ሰው የምድረ አሜሪካንን ብልጽግና ዕድገት በቃላት ሊያስቀምጥ ሳያስችግረው አይቀርም ብዬ እገምታለሁ። በመጣጥፌ ውስጥ እስከ አሁን ድረስ ስለ አሜሪካ

ብቻ ማውራቴ አንዳንዶችን በብዙ ዓይነት መልኩ ሊያስቆጣቸው ይችል ይሆናል። ቁም ነገሩ ግን እንደ አስተዋይና ባለ አዕምሮ ሊያስተምረን ከማይችል መማር እንደሆነ መግለጽ እወዳለሁ። እኔ እስከገባኝ ድረስ የምድረ አሜሪካ ዕድገት ተግቶ መሥራት፣ ጊዜን በአግባቡ መጠቀም፣ አቅምን አውቆ መኖር፣ ይሉኝታን ማስወገድ ሥራን አለመናቅ፣ ከልክ ባለፈ ማህበራዊ ኑሮ ውስጥ አለመተብተብ እና ሌሎችም መሰል ጉዳዩች ናቸው። አንድ ቀን ባለቤቴን "ለመሆኑ የአሜሪካ ሕዝብ መቼ ነው የሚያርፈው? ስል ጠየኳት። ምላሿ ይህን ይመስላል። "አሜሪካ ውስጥ በሳምንት ውስጥ የሃያ አራት ሰዓት ጊዜ ሰባት ይሰራል። ይህ አባባል ሰዓት ሰባቱንም ቀን ይሰራል የሚል አንደምታ አለው። እራሴ በካሊፎርኒያ ያየሁትን ነገር ላስቀምጥ። በቀንም ይሁን በሌሊት ሱቆችና ሬስቶራንቶች ይሰራሉ። መንገዶች ልክ ጠዋት በሥራ መግቢያ ሰዓት በመኪና እንደሚጨናነቁ የተጨናነቁ ናቸው። ሰው በአጭሩ ይሰራል። ከልቡ ይሰራል፣ ሌት ተቀን ይሰራል።

ስለ ሥራ ሲነሳ አብረው መነሳት ያለባቸው በርካታ ነገሮች ይኖራሉ የአገር ስላም አንድነት ሙስናና የተለያዩ ቢሮክራሲያዊ አሰራሮች ሊሎችም ይኖራሉ በመጀመሪያ አንድ ሰው ራሱንና አመለካከቱን ነው መለወጥ ያለበት የአመለካከት ለውጥ ከሌለ ሌሎች እንቅፋቶች ስለተወገዱ ብቻ ሰው ጠንካራ የሥራ ባሕልን ያዳብራል ማለት አንችልም። አሜሪካን በመሰለ አገር እንኳ ሰርተው ከማግኘት ይልቅ የሚዘርፉና በልመና የተሰማሩ ሰዎችን አይቻለሁ። እውነቱን እንነጋገር ከተባለ እኛም በአገራችን ጠንካራ የሆነ የስራ ስነ ምግባር የለንም። ለማደግ ከፈለግን ደግሞ በፀሎት እያሳበብንና ስራ እያማረጥን እራሳችንን

ከመጉዳት ሰርተው ያደጉት አገራትን ተሞክሮ በመውሰድ እራሳችንን ልንለውጥ ይገባል። እድገት ብዙ ከማውራትና ከመመኘት አይመጣም። ተግባራዊ እርምጃዎችን ካልወሰድን የምንመግብ ሳይሆን ተመጋቢዎች፣ የምንለግስ ሳይሆን ተለጋሾች፣ የምናስተዳድር ሳይሆን ተዳዳሪዎች እንሆናለን። መመሪያው አንድ ነው። ሰርተን ለማግኘት መስራት ብቻ ነው ያለብን። በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ብዙ ግራ የሚያጋቡ መንፈሳዊ መልዕክቶችን እንሰማለን "ኢትዮጵያ የተስፋ ምድር ናት አንድ ቀን ትጐበኛለች ነፃ ትወጣለች፣ ብዙ ብዙ እንሰማለን ይህ ሁሉ እውነትም ይሁን አይሁን ዋናው ቁም ነገር ግን አሁን ህዝባችን ካለበት የኑሮ አዘቅት ውስጥ ይወጣ ዘንድ ዘላቂ መፍትሔ የሥራ ስነ ምግባርን እንደሚገባ ማሳደግ ይመስለኛል። የሥራ ስነ ምግባርን ለማሳደግ የሚከተሉትን መፍትሔዎች ለማስቀመጥ እወዳለሁ።

- ሥራን አለመናቅ
- ሥራን እንደሽክም/ እርግማን አለመቁጠር
- ጊዜን በስራ ላይ ማዋል
- ቤተክርስቲያን ውስጥ ሥራ መንፈሳዊ ግዴታ መሆኑን መስበክ
- ማህበራዊ ኑሮ ሚዛኑን የጠበቀ ማድረግ
- ኑሮን በእቅድ መምራት
- እራስን ለማስቻል ማቀድና ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግ ተግቶ መሥራት

ከሌሎች ትጉህ አገራትና ግለሰቦች ምክርና ልምድ መቅሰም

የእግዚአብሔርን እርዳታ በፀሎት መጠየቅ የእግዚአብሔርን ቃል በሚገባ ማጥናት /ሥራን በተመለከተ/

በመጨረሻም የዚህ መጣጥፍ ትልቁ መልዕክት የአሜሪካ እድገት ሚስጥር ትጋት ነውና እኛም ከተጋን የማናድግበት አንዳችም ምክንያት አይኖርም። የሚል ሲሆን ይህም እውን እንዲሆን የመንግስት፣ የዜጐች፣ የአብያተ ክርስቲያናትና የተለያዩ የሃይማኖት ተቋማት የእርስ በእርስ ህብረት እጅግ አስፈላጊ ይሆናል።[15]

አንድ ወጣት ልጅ በአንድ ኮንፍረንስ ላይ ስለጋብቻ አስተምሬ ስወጣ ወደ እኔ መጥቶ በትንሽ ወረቀት የፃፉትን የፀሎት ርዕስ ስጠኝ ማረፊያ ክፍሌ ሄጀ ሳነባት የሚገርም አሳብ ይዛለች " የውጭ አገር ዜጋ /ፈረንጅ/ ማግባት እፈልጋለሁና ፀልዩልኝ" ትላለች ብቻዬን ፈገግ አልኩኝና፣ ይህ ወጣት ልጅ ፈረንጅ ማግባት የፈለገው ለምን እንደሆነ መጠየቅ አለብኝ ብዬ ከሰዓት በኋላ ባለው ኮንፍረንስ ላይ "ጠዋት የፀሎት ርዕስ የሰጠኸኝ ወጣት ልጅ ይህ ኮንፍረንስ እንዳለቀ እንድታገኘኝ" ብዬ ማስታወቂያ ተናገርኩኝ። ከእርሱም ጋር ከሰዓት በኋላ ተገናኘንና የሚከተሉትን ጥያቄዎች እያከታተልኩ ጠየኩት፡

ፈረንጅ ለማግባት የፈለከው ለምንድነው?

ኢትዮጵያ ድኃ ስለሆነች ከችግር ለማምለጥ ነው?

እግዚአብሔር ለፈረንጆቹ ሚሽነሪ ትሆናለህ ብሎ ነግሮህ ይሆን?

ስንተኛ ክፍልስ ነህ? ለሁሉም ጥያቄዎች የሰጠኝ መልስ የሚያጠግብ አልነበረም። ባጠቃላይ ፈረንጅ የሚያገባው ጥቁር ሴት ስለማይወድና ውጭ አገር መሄድ ስለሚፈልግ ብቻ እንደሆነ በግልፅነት አጫወተኝ። እኔም የራሱን ፈቃድ ሳይሆን

[15] ብርሃን መጽሔት ቁ.58 2000 ዓ.ም በምሕረቱ ጴ.ጉታ

የጌታውን ፈቃድ እንዲከተል ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ ውጪ አገር ለመሄድ እንዳይነሣ በዚሁ በአገሩ እግዚአብሔር የወደደውን ሊያደርግለት እንደሚችል ውጪም መሄድ ከፈለገ በጊዜውና በወቅቱ ጌታ በር ሊከፍትለት እንደሚችል ምንም ሳላስቀር መከርኩት ጸለይኩለትም።

ለመሆኑ ልባችን ከልጅነት ጀምሮ ወደ ውጪ የሚሸፍተው ለምንድነው? ይህ ወጣት 8ኛ ክፍል ላይ ሆኖ ውጪ አገር መሄድና ፈረንጅ ማግባት ምን አስመኘው ትምህርቴን ጨርሼ ከዩኒቨርስቲ ድግሪዬን ይዤ በአገሬ ውስጥ ለውጥ የሚያመጣ ሥራ እሰራለሁ የሚል የጋለ ምኞት ያላደረበት ለምንድ ነው? የምንባረከው ኃብታም የምንሆነው ውጪ አገር ስንሄድ ብቻ ነው የሚል አስተሳሰብ በውስጣችን የሚያድገው ለምንድነው? መልሱን በጋራ እንመልስ እኔ ግን አንድ ነገር እርግጠኛ የማደርግላችሁ ልባችንንና አሳባችንን ስብስበን በእውነትና በቅንነት ከሠራን እዚሁ አገራችን ምድራችን ላይም ይባርከናል የሚለውን አሳቤንና ምኞቴን ነው። እኔን በአገሬ ባርኩኝ ለምስክርነትም እንድሆን አቁሞኝ አይቻለሁና።

አንዳንድ ጊዜ በአረብ ሀገር የሄዱት እህቶቼ ላይ ሙቅ ውኃ ደፋባቸው ከፎቅ ወረወሯቸው በሰው ልጅ ላይ የማይሰራ ግፍ ሠሩባቸው የሚል ስሰማ ልቤ እጅግ ያዝናል ያንገበግበኛልም። ያልፍልኛል ኑሮን አሸንፋለሁ ቤተሰቦቼን እረዳለሁ ብለው ሄደው እስከወዲያኛው በሞት ተሸንፈው ሲቀሩ ሁላችንንም ያሳዝነናል። ለሥራ ያላቸውን መነሳሳት ሳይ ደስ ይለኛል ፤ግን በአገሬ ሠርቼ ያልፍልኛል የሚለው አሳብ ሲቀንስ ሳይ ደግሞ ይከፋኛል።ምናልባት እዚህ ጥሩ ክፍያ ያለው ሥራ ጠፍቶ

ይሆናል።ቢሆንም የማያውቁት አገር ሄዶ ከመሰቃየትና ከመሞት በአገር መሰንበት ይሻላል።

የዲቪ ፎርም በሚሞላበት ጊዜ የወረፋውን እርዝማኔ ሳይ ሰው የቀረ አይመስልም። እዚህ ላይ አንድ ነገር ተናግሬ ልጨርስ ፡ መፅሐፍ ቅዱስን ሳነብ የተረዳሁት አንድ እውነት፤ይህ ነው። የእኛ ልብ ከእግዚአብሔር ካልራቀ የእርሱ ባርኮት ከእኛ አይርቅም። ፈጣሪ እኛን ለመባረክ ቦታ አይወስነውም። ለእግዚአብሔር አሜሪካም አፍሪካም አንድ ነው አትላንታም ወላይታም ካሊፎርኒያም አዲስ አበባም አንድ ነው።

"ሥራ የመፈለግና የማጣት ችግር በብዙዎች ዘንድ የሚታይ ነው። በአሁኑ የአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ የተነሳ ሰዎች ሥራ ለመሥራት ፈቃደኛ ይሆናሉ። ከጥገኝነት ለመላቀቅ ጉጉት ያድርባቸዋል። ሆኖም ግን ካላቸው የትምህርት ደረጃና ሙያ አንፃር ሥራ ቢፈልጉም ቢያፈላልጉም ያጣሉ። እነዚህ ሰዎች ተሰፋ በመቁረጥና በማማረር ሕይወት ውስጥ ሲገቡ ይታየሉ። ሥራ አጥ መሆናቸው በጥገኝነት እንዲኖሩ ያስገድዳቸዋል። ጥገኛ መሆናቸው ደግሞ በራሱ ራስ ምታት ይሆንባቸዋል። በዚህም ምክንያት በራሳቸው ላይ በሚፈጠረው ሥነ ልቦናዊ ቀውስ ምክንያት እምነታቸውን የሚጥሉ፤ በብስጭት ራሳቸውን የሚገሉ፤ በሐሰትና በተጭበረበረ መረጃ ወደ ውጭ አገር ለመውጣት የሚታገሉ፤ በተለያዩ ሱሶች የሚጠመዱና ለስርቆትና ለሌሎች ወንጀሎች የሚታገሉ፤በዙዎች ናቸው። ይህ ሁኔታ ሥራ አጥነት ምን ያህል ሥር የሰደደ ችግር መሆኑን መፍትሔ እንድንፈልግ የሚገፋፋ ሲሆን በዚህ ረገድ ከእያንዳንዳቸው ብዙ ይጠበቃል።ሥራ ደግሞ የሚፈጠር ነገር

መሆኑንም መረዳት ያስፈልጋል።

አንድ ሰው እንዲህ አለ። "ሰዎች በሶስት ክፍሎች ይከፈላሉ ይባላል። ጥቂቶቹ ነገሮች እንዲሆኑ እንዲፈጠሩ ያደርጋሉ። ብዙዎቹ ደግሞ ነገሮች ሲከናወኑ ያያሉ። እጅግ በጣም ብዙዎች ግን የሆነውን ነገር እንኳን አያውቁም"። ሰለዚህ ነገሮች እንዲሆኑ ከሚያደርጉት ጥቂት ሰዎች መካከል ነን? ወይስ ተመልካቾች፣ ወይስ ደግሞ የነገሮችን አካሄድ ምንም የማናውቅ ሰዎች? ብዙዎቻችን ሥራን በመፈለግ ዕድሜአችንን ፈጅተን ይሆናል። እስቲ እግዚአብሔርንና ራሳችንን ቆም ብለን ለመመልከት እንሞክር። እግዚአብሔር በእያንዳንዳችን ውስጥ ያስቀመጠው ችሎታ (potential) አለ። ይህ ችሎታ እንዲገለጥ መነሳትና መጣር የእኛ ድርሻ ነው። ሌላ ቀስቃሽ እንዲኖረን አያስፈልግም። አንድ አባባል" ላሚቱን ከሰጡህ አንተ ማሰሪያውን ማቅረብ አለብህ" ይላል። እግዚአብሔርን ላሚቱንም ገመዱንም አምጣ አንበለው። ላሚቱን ከሰጠን ገመዱን እኛ እንፈልግ። በእግዚአብሔር የሚሰጠው ጥበብና ማስተዋል ሥራን እንድንፈጥር አብዝቶ ይረዳናል። ጥበብና እውቀት ባለበት ቦታ በዚያ ሥራ አለ። እውቀትና ጥበብ በሌለበት ሥፍራ ደግሞ ሥራ የለም።ዘጸ31:2-5 "የኡሪ ልጅ ባስልኤልን በስሙ ጠርቼዋለሁ። በሥራ ሁሉ ብልሃት በጥበብም በማስተዋልም በእውቀትም የእግዚአብሔርን መንፈስ ሞላሁበት፣ የጥበብን ሥራ ያስተውል ዘንድ በወርቅና በብር በናስም ይሰራ ዘንድ ለፈርጥ የሚሆነውን የዕንቁ ድንጋይ ይቀርጽ ዘንድ እንጨቱንም ይጠርብ ዘንድ ሥራውንም ሁሉ ይሰራ ዘንድ።" መክ 10:10 ደግሞ " ጥበብ ግን ሥራውን ለማከናወን ትጠቅመዋለች።"

ይላል። ወደ አዲስ ኪዳንም ስንመጣ "ስለዚህም ምክንያት ትጋትን ሁሉ እያሳያችሁ በእምነታችሁ በጐነትን ጨምሩ፣ በበጐነትም እውቀትን፣ በእውቀትም እራስን መግዛት፣ ራስንም በመግዛት መጽናናትን፣ በመጽናናትም እግዚአብሔርን መምሰል፣ እግዚአብሔርንም በመምሰል የወንድማማችን መዋደድ፣ በወንድማማችም መዋደድ ፍቅርን ጨምሩ። እነዚህ ነገሮች ለእናንተ ሆነው ቢበዙ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አውቀት ሥራ ፈቶችና ፍሬ ቢሶች እንዳትሆኑ ያደርጓችኋልና" ይላል /2ኛ ጴጥ 1:5-8/። በእርግጥ ይህ በመንፈሳዊ በኩል ስላለው ሥራ የሚያመለክት ቢሆንም ከላይ የተዘረዘሩት ነገሮች ትጋትን ካሳየን ሥራን በመፍጠር ወይም በተፈጠረ መስክ ውስጥ ገብተን መሥራት የምንችልበትን መንገድ እናገኛለን።"

እስቲ ወደ አገራችን

ይመለስ ልባችን


ይሁን መክበሪያችን

ይሁን ፍፃሜያችን

ፈጣሪም ይባርክ ኢትዮጵያ አገራችን።

ወገኖቼ በምድራችን ላይ ተረጋግተን እየሠራን ጌታን እንጠብቀው። አንዲህ የሚለውን የተስፋ ቃል የሰጠን ጌታ እኮ ታማኝ ነው። " ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች...." ቃሉን ካላዘዋወርነው በስተቀር እንጂ ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ አሜሪካ ትዘረጋለች አይልምና። እስቲ እንደተባለልን በአምላካችን እንታመን። ያን ጊዜ ኢትዮጵያችን የዳቦ ቅርጫት ትሆናለች። አሜን !

ዕድገት ብዙ ከማውራትና ከመመኘት አይመጣም። ተግባራዊ እርምጃዎችን ካልወሰድን የምንመግብ ሳይሆን ተመጋቢዎች የምንለግስ ሳይሆን ተለጋሾች የምናስተዳድር ሳይሆን ተዳዳሪዎች እንሆናለን።



ምሕረቱ ጴ.ጉታ

በነገራችን ላይ ኢትዮጵያችን የዳቦ ቅርጫት እንዳትሆን እንትፋት የሆነባት ጉዳይ ሰዎች አገር ጥለው ለመሄድ ማሰባቸው ብቻ አይደለም። ጊዜአችንንም በአግባቡ አለመጠቀማችንም ጭምር እንጂ። ታዲያ ጊዜአችንን በአግባቡ ለመጠቀም ምን እናድርግ?

በመርፌ ቀዳዳ ያልሾለከ ክር ልብስ መስፋት አይችልም::

ምዕራፍ አስራ አምስት

ኢትዮጵያችን የዳቦ ቅርጫት የምትሆነው ጊዜያችንን በአግባቡ መጠቀም ስንችል ነው::

ይህንን መፅሐፍ ለመፃፍ የገባሁበት የእንግዳ ማረፊያ ቤት Guest House/ አጠገብ ሌሉቱን ሁሉ ሲጨፈርበት የሚታደርበትቤት አለ:: እኔም ያወኩት እዚያ ገስት ሀውስ ሥራዬንለመስራትበመጣሁ ጊዜ ነው:: ጩኸቱ ከማታ አራት ሰዓት ይጀምራልየተለያዩ ዘፋኞች ካሴት ይከፈታል በየመካከሉ የሰዎች ጩኸት አለየሙዚቃው ድምፅ ከፍተኛ ነው:: ከተኛሁ በኋላም እንኳ 7 ሰዓትብንን ብል ሙዚቃው አለ ዘጠኝ ሰዓት አስር ሰዓት አሁንም ጭፈራው ቀጥሏል እነዚህ ሰወች በዚች ድህንነት ዘውድ ጭኖ በነገሰባት አገር የራሳቸውንም የሌሎችንም ሰዎችን ጊዜ እየበሉ እንደሆነ ለመሆኑ ያውቁ ይሆን ? ለራሳቸውም በከፍተኛ ችግር ውስጥ እንዳሉስ ያውቁ ይሆን ? ብዬ ራሴን ጠየኩ:: በእርግጥም ከፍተኛ ችግር ውስጥ ነው ያሉት::እስቲ ቀጥሎ የእነዚህ ሰዎች አካሄድ ከሚያስከትሉአቸው ችግሮች ጥቂቶቹን ላሳያችሁ::

- ሰውነታቸው ማረፍ ያለበትን ጊዜ አባክነውበታል አድክመውታል::
- በቀጣዩ ቀን በነቃ አዕምሮ ሥራቸውን ማከናወን አይችሉም
- ታመው ወይም ደክመው ከሥራ ሊቀሩ ይችላሉ
- ገንዘባቸውን ለጊዜያዊ ደስታ ይጨርሳሉ
- ቤተሰቦቻቸው እነርሱን በመጠበቅ ሳይተኙ /ሲጨነቁ/

ያድራሉ

- ለኤች አይቪ ኤድስ በቀላሉ የተጋለጡ ይሆናሉ
- ረጅም ዕድሜ መኖር አይችሉምና በአጭሩ ይቀጫሉ
- የሌሎችን ዜጐች የእንቅልፍ ጊዜ በረብሻ ያባክናሉ::
- ለተለያዩ ሱሶች ተገዢዎች ይሆናሉ::
- ጊዜያቸውን በትክክል መጠቀም አልቻሉምና ይቸገራሉ::

እንድህ አይነት ሁኔታ በዋና ዋና ከተሞቻችን ይታያልና እኔም እነዚህ ዜጎች ራሳቸውን መርምረው ሁሉን ነገር ሚዛናዊ በማድረግ ሕይወታቸውን በመልካም ሥነ ምግባር እንዲመሩ እመክራለሁ::ምክንያቱም እንደ እነዚህ አይነት ዜጐች እየበዙ ከሄዱ የአገር ኢኮኖሚ እየወደቀ ይሄዳል:: ኢትዮጵያችንም የዳቦ ቅርጫት መሆኗ ቀርቶ የዳቦ ቅርጫ ውስጥ እንደገባች ትቀራለች:: ስለዚህ ይህ እንዳይሆን ምን እናድርግ፤ ጊዜያችንን አንድም ሰከንድ እንኳ ሳይባክን በአግባቡ እንጠቀምበት:: **የአንድ ሰከንድ ጥቅም ለማወቅ ከፈለግን ደግሞ የምንወዳቸውን ሯጮቻችንን እነ ኃይሌ**

ገ/ስላሴን እንጠይቅ::

በአንድ ሰከንድ ሳይሆን በማይክሮ ሰከንድ ብዙ ልዩነት እንደሚፈጠር በሩጫው አለም እነርሱ በደንብ ያውቃሉና:: እኛም ኢትዮጵያውያን በደንብ አድርገን እናውቃለን::

በሰከንድ ልዩነት ባንዲራ ከፍ ብሎ ይውለበለባል ወይም ሳይውለበለብ ይቀራል

በሰከንድ ልዩነት ማሸነፍና ጉሮ ወሸባዬ አለ ወይም በመሸነፍ አንገት መድፋት አለ

በሰከንድ ልዩነት ብዙ ገንዘብ ሽልማት አግኝቶ ፎቅ መስራትና አገርን ማሳደግ አለ ወይም ለአገር ሸክም ሆኖ ምንም ሳያገኙ ያለውን የአገርን ኃብት ብቻ ማጫረስ አለ::

በሰከንድ ልዩነት ኢትዮጵያ አገራችንን በዓለም ሁሉ ላይ ማስተዋወቅ አለ ወይም የዚህ ተቃራኒ አለ :: ታዲያ እንግዲህ የሰከንድ ልዩነት በሩጫው አለም አንዲህ ከሆነ በእኛስ በሥራችን ዙሪያ እንዴት ነው ? አንድ ሰው እንድህ ሲል ሰምቻለሁ

"ለአንድ ሰከንድና ለአንድ ሳንቲም ብዙ አልጨነቅም::" አብዛኛው ሰው ለአንድ ሰከንድና ለአንድ ሳንቲም ብዙ አይጨነቅም ግን እነርሱ ተደምረው ነው እኮ ብዙ ደረጃ የሚደረሰው :: አንዳንድ ሰው አንድ ሰከንድ ሳይሆን አንድ ሰዓት አርፍዶ ለቀጠሮው ይመጣል:: የሚጠብቀውም ሰው ለጊዜ ግድ ስለሌለውና ጊዜ ስለተረፈው ይመስላል አንድ ሰዓት ያህል ይጠብቃል:: ለዚህ ነው " የአበሻ ቀጠሮ " የሚል ስም የወጣልን:: ይህ ግን ሊታረም ይገባል አሳፋሪ መታወቂያ ነውና::

አንድ ወቅት ከአንድ ፈረንጅ ጋር ለሥራ ጉዳይ ቀጠሮ ስንለዋወጥ መጨረሻ ላይ ያለኝን አረሳውም:: ልንለያይ ስንል " ለቀጠሮ የያዝነው ሰዓት በአበሻ ነው በፈረንጅ " አለኝ ምን ማለቱ መሳልችሁ ታረፍዳለህ ወይስ እንደ ፈረንጅ ልክ በሰዓቱ ትመጣለህ ማለቱ ነው:: እስከመቼ እንደዚህ እየተባልን እንዘልቃለን ብዬ እውነቴን ነው የምላችሁ ትንሽ ተሰማኝ ::

ፈጣሪ ለነጮቹም ለጥቁሮቹም የሰጠው ጊዜ እኩል 24 ሰዓት ነው። ታዲያ እኛ 48 ሰዓት ያለው ቀን የተሰጠን ይመስል ዳተኛ መሆናችን ምነው ጃል! እስቲ ጊዜአችንን በማክበር ጊዜአችንን እንጠቀም። እዚህ እኛ አገር ሁለት በጣም የሚከበሩ ቀጠሮዎች እንዳሉ አውቂአለሁ። የመጀመሪይው የፍርድ ቤት ቀጠሮ ነው። ለረጅም ጊዜ ቢቀጠርም እረስቶ የሚቀር ወይም አርፍዶ ፍርድ ቤት የሚመጣ ሰው ብዙ የለም። ለምን? ሁለተኛው ቀጠሮ ደግሞ የእጮኛ ቀጠሮ ነው። አንዱ እጮኛውን 11:00 ሰዓት ላይ አዲስ አበባ ዋቢ ሸበሌ ሆቴል ቀጥሮ ቢሆን፣ ከ 9:00 ሰዓት ጀምሮ በሸበሌ ሆቴል አካባቢ ተረኛ ሮንድ ጠባቂ ይመስል ሲሽከረከር ይታያል። ለምን? ልክ እንደ እነዚህ ቀጠሮዎች ጊዜያችንን ለሌሎች የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴዎችም ሁሉ በአግባቡ ብንጠቀም እድገታችን አዝጋሚ መሆኑ ቀርቶ ፈጣን ይሆናል።

"ሥራንና ጊዜን ሳያነጣጥሉ በአንድነት ማንሳት ተገቢ ነው። ምክንያቱም የጊዜ አጠቃቀም መቆራኘት ያለበት ከድርጊት ጋር ወይም ከሥራ አፈጻጸምና አከናወን ጋር ነውና። ስለ መልካም የሥራ ስነ ምግባር ስንነጋገር ውጤታማ ካልሆነ የጊዜ አጠቃቀም ተነስተን ማየት የማይቻል ነው። ስለዚህ ነው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋው ወራት በምድር ላይ ሰላሳ ሶስት ዓመት ያህል ብቻ እንደሚኖር ተረድቶ *"ቀን ሳለ የላከኝን ሥራ መሥራት አለብኝ፣ ማንም ሊሰራ የማይችልበት ሌሊት ይመጣልና"* ያለው። /ዮሐ 9:4 ይህ እውነት የሚያሳየን ማንኛውም ሥራ በጊዜ የተገደበና በተገደበው ጊዜ በዓላማው ላይ አተኩረን ካልሰራን ዕድሉ ተመልሶ የማይመጣ መሆኑን ነው። ስለዚህ ዋናው ቁም ነገሩ ሥራ መሥራቱ ብቻ ሳይሆን ሥራው

ከተመደበለት ጊዜ ጋር ያለው ጥምረት ለስኬታማነት ወሳኝ ነው ማለት ነው። ስለ ውጤታማ የጊዜ አጠቃቀም ስናወሳ ደግሞ አንድን ሥራ ሰርተን በውጤቱ ተጠቅመንና አድገንበት እግዚአብሔርንም አስከብረን ለመኖር ስለምንወስደው ብርቱ አርምጃ መናገራችን ነው።"

ጊዜን በተመለከተ ሌሎች መስተካከል ያለባቸው ነጥቦች አሉ ይህም ብዙ ሰዓት ለእረፍትና ለመዝናናት መስጠት ነው። ይህንን ለማሳየት 24 ሰዓቱ ለምሳሌ ያህል ከፋፍለን እንመልከት። ከ24 ሰዓት ውስጥ 8:00 ሰዓት ስራችንን ብንሰራ 16 ሰዓት ይተርፈናል ይህ እንግዲህ ለመዝናናት፣ ለመኝታ እና ሌሎች ጉዳዩች ለመከወን የቀረ ነው። 6:00 ሰዓት ሌሎችን ነገሮች ብናከናውንበት 10:00 ይተርፋል ይህንን ሁሉ ሰዓት ደግሞ መተኛት ያስቸግራል ስለዚህ 7:00 ሰዓት ያህል ከተኛ በኃላ ሰው 3:00 ሰዓቱን የሚያሳልፍበት ሲያጣ አብዛኛው ሰው ሥናልባት ልጅ ለመውለድ የሚያውልበት ጊዜ ያደርገው ይሆን?። ስለዚህ በእኔ ፍልስፍና ብዙ ልጆች የምንወልደውና ብዙ የሕዝብ ቁጥራችን እየበዛ የሄደው ብዙ ሰዓት ስለምንተኛ ነውና እስቲ የእንቅልፍ ጊዜአችን ከመደበኛው ሰዓት አናሳልፈው። ብዙ እንቅልፍ ድህነትን ያመጣልና ምሳሌ 6:9-11 "አንተ ታካች እስከመቼ ትተኛለህ? ከእንቅልፍህስ መቼ ትነሳለህ? ጥቂት ትተኛለህ ጥቂት ታንቀላፋለህ ትተኛም ዘንድ ጥቂት እጅህን ታጥፋለህ እንግዲህ ድህነትህ እንደወንበዴ ችጋርህም ሰይፍ እንደታጠቀ ሰው የመጣብኃል" ይላል። <u>ድህነትህና ችጋርህ</u> የሚሉትን ቃላት ልብ ይበሉ የግልን ጉዳይ እንጂ የጋራን አያመለክቱም። ድህነት የግል ነው ችጋር የግል ነው። እያንዳንዱ

ሰው በስንፍናው ተኝቶና በመዝናናት ብቻ በግሉም ሆነ በአገሩ ላይ የሚያመጣው የራሱ የግሉ ነው። እንዲህ ከሆነ አገር የጋራ ነው ድኅነት የግል ነው ማለት ነው።ነገር ግን የግል ችግር የጋራ እንደሚሆን ቆይቶ መዘንጋት የለብንም። ጊዜ እንደ ታክሲ ቆሞ አይጠብቅምና በተሰጠን ጊዜ እንጠቀምበት። ስለዚህ ትርፍ ጊዜ አለን እንኳ የምንለው ቢኖር የተለያዩ መጽሐፍትን በማንበብ የንባብ ባህላችንን ማሳደግ አለብን ከአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ብንነሳ የንባብ ባህላችን አናሳ ነው ።አባቶቻችን እና እናቶቻችንም አብዛኞቹ የዱሮ ቤተሰቦቻችን ሞራና ስኒ ሲያነቡ ነው የኖሩት ይህ ደግሞ አገራችንን እንዳሳሳደገ ለሁላችንም ግልጽ ነው። ዛሬ አልፎ እነርሱንም እኛንም ይጸጽተናል። የእኛም ዘመን ሳያልፍ በትኩስ ጉልበታችን እንስራ። ሳይጠቀሙበት እንደሚያልፍ ጊዜ የሚጸጽት ነገር የለምና።

"መሥራት እየቻለ - በትኩስ ጉልበቱ
ባፍላነቱ ዘመን - በወጣትነቱ፤
ሐይል ችሎታውን - አባክኖና አሽንፎ
በጁ ያለን ጊዜ - በዋዛ አሳልፎ፤
ትናንት ያልሠራውን - ሰው በራሱ ለግሞ
ዛሬን እየሸሸ - ሲቀጥር ለከርሞ፤
ከጅ ካመለጠ - ከመዳፍ ከወጣ
ጊዜ ላይመለስ - የሔደ ላይመጣ፤
አካል እየዛለ - ፊት እየገረጣ

ሥራ ... ሥራ ... በአገርህም ኩራ!

ሰውነት ሲደክም - እርጅና ሲመጣ፤
ከመሸ በኋላ - ወራቱ ካለፈ
በህሊና ፀፀት - እየተገረፈ፤
'ወይኔ'ን እያዜመ - በነበር አባዜ
አሻግሮ ያየዋል - ያን የጠፋ ጊዜ።[16]

"ጊዜ ወርቅ ነው" ሲባል ሁሌ እንሰማለን። የጊዜ ወርቅነት ሊገባው የሚችል ሰው አጠቃቀሙን የሚያውቅ ይሆናል። ለንባብ ባሕል መከናወን ቁልፍ የሆነ ነገር ቢኖር ጊዜን በአግባቡ መጠቀም መቻል ነው። ሌሎች ጉዳዮችን ለመፈፀም ጊዜ እንደሚኖረን ሁሉ፤ ለንባብ ደግሞ ጊዜ መመደብ ይኖርብናልና። በአብዛኛው ሰዎች የጊዜ አጠቃቀምን ቢያውቁት ኖሮ አውቶብስ እየጠበቁ የሚያሳልፉትን ሰዓት ለንባብ ሊያውሉት ይችላሉ፤ ካፍቴሪያ ውስጥ ሊያነቡ ይችላሉ። ሌሎችም በርካታ አጋጣሚዎች አሉ። የጊዜን አጠቃቀም ማወቅ ደግሞ ኘሮግራሞቻችንን መልክ ባለው መንገድ እንድናስኬዳቸው ወሳኝ ሚና የሚጫወት ክህሎት ነው። እዚህ ላይ የጊዜን አጠቃቀም በተመለከተ ተግባራዊ በሆነ ዕቅድ ማውጫ መንገዶችን ማወቅ ይኖርብናል። ይህ ማለት በቀን ውስጥ፤ በሳምንት ውስጥ፤ በወር ውስጥ በዓመት ውስጥ ምን ማድረግ እንደሚኖርብን ለራሳችን ዕቅድ ማውጣት ይኖርብናል።

እንግዲህ የንባብ ባህላችን እንዲያድግ ጊዜን በአግባቡ መጠቀም ተገቢ ብቻም ሳይሆን ወሳኝ ነው። ጊዜን በሥርዓት መጠቀም መቻል በብዙ አቅጣጫ የተዝረከረከ ሕይወት እንዳይኖረን

[16] የብልጽግና ቁልፍ ገጽ 115


ያደርጋል። ከዕቅዳችንም ውስጥ አንዱ ለንባብ የምንሰጠው ጊዜ ይሆናል። " ጊዜ የለንምና አናነብም " የሚሉ ሰዎች ያጋጥሙኛል። እውነቱ ግን ጊዜው ሳይኖራቸው ቀርቶ ሳይሆን፣ ጊዜ የለንም የሚሉት የማቀድ ባህል ስሌለላቸው ነው ። ጊዜ አግባብነት ባለው መንገድ ሥራ ላይ ከዋለ ለሌላ ነገር የሚሰጠውን ሰዓት ለንባብም መስጠት ስለሚቻል ባህሉን ማሳደግ የሚቻል ይሆናል። [17]

ስለዚህ ስራ ለነገ ማሳደር ብዙ ማውራትን ማንቀላፋትን እና ቅጥ ያጣ መዝናናትን ትተን ለሥራ ታጥቀን፤ ቆርጠንና ቆፍጥነን እንነሳ ያን ጊዜ ሰይፉን ታጥቆ የመጣብን ድኅነት በሰይፋችን ተወግቶ ይመለሳል። ያን ጊዜ ኢትዮጵያችን የዳቦ ቅርጫት ትሆናለች።

[17] የንባብ ባህል በምሕረቱ ጴጥታ ገጽ 147

በዘመናት ታሪክ የዳበረውን የመቻቻል ባህላችንን በማሳደግ፣ ስራ ወዳድና አክባሪ ዜጎች በመሆን፣ እጅ ለእጅ ተያይዘን አገሪን የሚያለማውን ራዕይ ሰንቀን ሁላችንም በየተሰማራንበት የግል ፣የመንግስትና ፣ የድርጅት ስራ ቦታዎችን ፀረ ሙስና አቋም በመያዝ ጎጂ ልማዳዊ ልምዶቻችን ቀይረን በአንድ ሐሳብ ለአንዲት ኢትዮጵያ እንስራ። ድህነት የጋራ ጠላታችን ስለሆነ ቤተሰብ ቤተክርስቲያንና መንግስት በጋራ ተባብረው ቢዋጉት በአጭር ጊዜ ውስጥ የጋራ ድል ይቀዳጃሉ።

ወንጌላዊ ደመወዝም እግዚአብሔር ይባርከው። ሥራ ሥራ የሚለውን አንገብጋቢና ወቅታዊ ርዕሰ ጉዳይ በአገር አቀፍ ደረጃ ከስካሁኑ የሥነ ጽሁፍ ድርሳናት አንጻር ሲታይ በመጽሔቶች በመንፈሳዊ፣ ጋዜጦች፣ በስልጠናዎችና በአጫጭር አውደ ጥናቶች ደረጃ እንጂ በዚህ መልክ በጥልቀትና በስፋት ተጠንቶ የማህበረሰባችንን ከሥራ ጋር በተያያዘ ሁኔታ የሚታየውን ሁለንተናዊ ጉድለቶቻችንን በዝርዝር የሚዳስስ መጽሐፍ አልተዘጋጀም። ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ እመርታው ከፍተኛ ስለሆነ ሁሉም የማህበረሰብ ክፍሎች ቢያነቡት ጠቀሜታው የጎላ ይሆናል። ስለሆነም ይህን የመሰረታዊ ለውጥ አካል የሆነውን ኢትዮጵያዊያን ሁሉ ገዝተው ቢያነቡት አገራዊና ቤተሰባዊ ትርፋማነታቸው የላቀ ይሆናል ብዬ እገምታለሁ።



ማርቆስ ዳንኤል (ወ/ዊ)

በነገራችን ላይ ኢትዮጵያችን የዳቦ ቅርጫት እንዳትሆን መሰናክል የሆነባት ነገር ጊዜን በአግባቡ አለመጠቀም ብቻ ሳይሆን፤ በልመና ኑሮን ለመግፋት ማሰብም ጭምር ነው። ታዲያ ከልመና አስተሳሰብ እንዴት መውጣት ይቻላል?

አይሮፕላን ያለ አብራሪው በሰማይ ላይ ያለ ውድ የሬሳ ሳጥን ነው ::

ምዕራፍ አስራ ስድስት

ኢትዮጵያችን የዳቦ ቅርጫት የምትሆነው በልመና ለመኖር ማሰባችንን ስናቆም ነው።

እንደዚያ ቀን አፍሬ አላውቅም። እኔና ፈረንጁ ለሥራ ጉዳይ ወደ አንድ ቦታ በእግራችን እየሄድን እያለ በየመንገዱ ሳያቋርጥ ከልጆቹ አፍ የሚሰማ አንድ ድምጽ አለ "ፈረንጅ ፈረንጅ መኒ" በተደጋጋሚ ፈረንጁን እየተከተሉ የዚያ አካባቢ ልጆች "ፈረንጅ ፈረንጅ መኒ" ተሳስተው እንኳን ከእኔ ጋር ስላለ "ፈረንጁና አበሻው መኒ" አይሉም። በልጅነት አዕምሮአቸው ማን እንዳስተማራቸው ወይም ይህንን ፍልስፍና ከየት እንዳገኙት አላውቅም " ፈረንጅ ገንዘብ አለው አበሻ የለውም የሚለውን የተሳሳተ አመለካከት "ፈረንጅ ፈረንጅ መኒ" በጣም አፈርኩ ፈረንጁ "ኖ መኒ ኖ መኒ" እያለ በወፍራም ፈገግታ ለልጆቹ ሁሉ መልስ ይሰጣል።

የሚገርም ነው ይህንን ከልጅነት ጀምሮ በልመና የተያዘውን አዕምሮና ልብ ማን ሊያስጥለው ይችላል? ከእግዚአብሔር ጋር መንግስት ቤተክርስቲያንና ወላጆች በመተባበር ሊያስቀሩት እንደሚችሉ አምናለሁ። ልመና ባህል ሊሆን አይገባም ከሆነም አሳዛኝ ነው፤ መቅረት ያለበትም ክፉ ባህል ነው።

ዛሬ የልመናው ዓይነት ዘዴውና መራቀቁ ይለያይ እንጂ፤ ልመና ዙፋኑን ዘርግቶ በአገራችን ላይ አለ። እንዴት ከዙፋኑ ላይ አውርደን ሥልጣኑን እስከወዲያኛው መቀማት እንችላለን?

አንዱ እና ዋናው መፍትሔ ሰዎች ከልመና ወጥተው በእጃቸው ሰርተው እንዲኖሩ የአዕምሮና የልብ ለውጥ እንዲያገኙ ስልጠናና ትምህርት መስጠት ነው። እርዳታ ሲለመድ የመሥራት ፍላጐት እየቀነሰ ይሄድና ይጠፋል። ለዚህም ይመስላል ባለፉት ዓመታት "ካናዳ ይዝነብ እንጂ ችግር የለም" የሚሉ በእርዳታ መኖርን የተለማመዱ ሰዎች በኢትዮጵያ ምድር የበቀሉት።ታዲያ እንደ እነዚህ ዓይነቶችን ሰዎች አካፋና ዶማ አስይዞ ማሰራት አስቸጋሪ ይሆናል።ሆኖም ተስፋ ሳይቆርጡ ማስተማር ነው።

ሁለተኛው መፍትሔ ደግሞ፤ሰፈኪው ክፍል ለማኙን በማጥናት መስጠትና አለመስጠት ነው። ጤነኛ ለሆነ ሰው ሁሉ " ስለቤዛዊት ዓለም " ሰላለ ብቻ መስጠት አይገባም። ብዙ ሰው የሚለምነኝ ሰው ካጠገቤ ይሂድልኝ በማለት ይመስላል የለማኙ ሀኔታ ግድ ሳይለውና ትንሽ እንኳን ሳያጣራ ያለውን ይሰጣል። ይህ ግን ልክ አይደለም።ጤናማ ከሆኑ መስራት እንዲችሉ መምከርና መገሰጽ አለብን እንጂ።

አዲስ አበባ ውስጥ ፒያሣ አካባቢ አንድ የደርግ ወታደር የነበረ ሰው የኮረኔል መንግስቱ ኃ/ማርያምን ፎቶ በትልቁ አሳጥቦና በፎቶ ፍሬም ማስቀመጫ ይዞ በእንገቱ በክር አንጠልጥሎ በደረቱ ላይ ፎቶውን እያሳየ እንዲህ እያለ ይለምናል።

" ስለ ቆራጡ መሪያችን "

"ስለ ሞት አይፈሬ" ይህንን የሰማና የሚያየው ሰው ሁሉ እየሰጠው ፈገግ እያለ ያልፋል ። ገረመኝ እኔ ለዚህ ሰው ገንዘብ ሳይሆን ነገም ሊያኖረው የሚችልበት አሳብ /idea/ ልሰጠው ጠጋ አልኩና "ይቅርታ የኔ ወንድም አንተ ሙሉ አካል ያለህ ጤነኛ

ሰው ነህ እንዲህ በአደባባይ እየለመንክ የሰው ፊት ከሚገርፍህ ለምን ትንሽም ሥራ ቢሆን ፈልገህ አትሠራም ? " ብለው ከላይ እስከታች በዓይኑ ገላመጠኝና "የእርጉ ዝንብ ዝም ብለህ አትሄድም" ብሎ ለማሳሳቻ በያዘው ከዘራ ሊገርልጠኝ ሲል ነው በቶሎ ያመለጥኩት። ይህ ሰው ይህንን የልመና ዘዴ ከየት አገኘው ወይስ እንደ እነዚያ ልጆች እሱም ከልጅነቱ ጀምሮ "ፈረንጅ መኒ መኒ" እያለ ያደገ ይሆን ?

ልመና ክፋ ነው

ልመና ጥገኛ ያደርጋል

ልመና ሌሎች አማራጮችን አያሳይም

ልመና ከሰው በታች ያደርጋል

ልመና የህሊና ወቀሳና ጠባሳ ያስከትላል

ልመና መቼም አያላድግም

ልመና ማንነትን ያሳጣል

ልመና ለአገር ዕድገት እንቀፋት ነው። ስለዚህ ልመናን እናስወግድ።

በልመና ብቻ መኖሪያ አድርገው ሌላ ሥራ ሳይሠሩ የሚኖሩ ብዙ ሰዎች አሉ። እንዲህ እያሉም የተለያዩ የልመና ዘዴዎችን ይጠቀማሉ፦

አሥር ሺህ ብር ከአገሬ ይዤ ወጥቼ ሌቦች ቀሙኝና የአቶቢስ መሣፈሪያ አጣሁና እንደወጣሁ ቀረሁ /10ሺህ ብር ከአገሩ ይዞ መውጣቱን እግዚአብሔር ይወቅ/

የቤት ኪራይ የምከፍለው አጥቼ ዕቃዬን ሜዳ ሊበትኑብኝ ነው

ሚስቴ ወልዳ ከሆስፒታል የማወጣበት ገንዘብ አጣሁ

ለዚህ ቤተክርስቲያን ማሰሪያ ያላችሁን ጣልጣል አድርጉ/ ለቤተክርስቲያኑ ይሆን ወይ ለግለሰቡ ጌታ ይወቅ/

የኤች አይ ቪ ታማሚ ነኝ መድኃኒቱን ለመጀመር ገንዘብ አጣሁ። /መድኃኒቱ እኮ በነፃ ነው የሚሰጠው/ ይገርማል ዘንድሮ።

ስለ ኤች አይ ቪ ከተነሣ ብዙ ፖዘቲፎች የሚረዳኝ የለም ብለው በመዋሸት በተለያዩ ድርጅቶች ይረዳሉ። ይህም መስተካከል ያለበት ነው።ስለዚህ ጉዳይ ሳስብ በልመና ብቻ ለመኖር አዕምሮዋን ያሳመነች አንዲት ሴት ያደረገችው ትዝ አለኝ ለብዙዎቻችን ትምህርት ይሆነናልና እንደሚከተለው አቅርቤዋለሁ።

የሥምንት ወር ልጅ በጀርባዋ አዝላለች የልጁ አባት ጦርሜዳ ሄዶ ስለሞተብኝ እና እኔም ሠርቼ ለመብላት ጤና ስለሌኝ ሁልጊዜ ስለሚያመኝ እርዱኝ ብላ ነው ወደ ቤተክርስቲያናችን መጥታ የተገናኘነው። እኔም ጤና የለኝም ብዙ ጊዜ ያመኛል ስላለችና ደግሞም በዚያ ሰሞን ከቀበሌ ጋር በመተባበር ለኤች አይ ቪ ታማሚዎች ድጋፍ ለማድረግ አዲስ ቢሮ በቤተክርስቲያናችን ከፍተን ሥራ ለመጀመር ታማሚዎች እየመለመልን ያለበት ጊዜ ሥለሆነ ምናልባት እርሷም የኤች አይ ቪ ቫይረስ በደሙዋ ውስጥ ከተገኘ በዚህ እድል ተጠቃሚ እንድትሆን በማለት ኤች

አይ ቪ ምርመራ እንድታደርግ ፈቃደኝነቷን ጠየኳት፡ እርሷም ፈቃደኛ ሆነች የምትመረመርበትንም ገንዘብ ሰጠኋትና ሄዳ ተመርምራ ውጤት ይዛ መጣች። በውጤቱ ግን ደስተኛ አልነበረችም በጣም አዝና ነበር እኔም ፊቷን አይቼ ላጽናናትና ልፀልይላት በማሰብ ውጤቱ እንዴት እንደሆነ ስጠይቃት ፊቷን ቅጭም አርጋ "በጣም አዝናለሁ ኤች አይ ቪ የለብሽም አሉኝ በቃ አትረዱኝም ማለት ነው? " ብላኝ እርፍ። በልመና በታወረው አስተሳሰቧ አዝኜ ልክ አንዳይደለች ጤነኛ ከሆነች ወጥታ ገብታ በጉልበቷ የበለጠ ሠርታ እርሷንም ልጇንም ማስተዳደር እንደምትችል መከርኳት። ይህች ሴት ጤነኛ ከሆንኩ የሰው ቤት ውስጥ እንካ እየሰራሁ ልጄን አሳድጋለሁ እኔም እኖራለሁ የሚለው በጉ አስተሳሰብ ምነው ጠፋባት? ወይስ እርሷም እንደነዚያ ልጆች ከልጅነቷ ጀምሮ "ፈረንጅ ፈረንጅ መኒ" እያለች ይሆን ያደገችው ?እስቲ የልመናን አስተሳሰብ አስወግደን በላባችን ሠርተን ለመለወጥ እንነሣ። አዕምሮአችንንም ከልመና ውጪ ሌላ ሥራ ፈጥሮ እንዲሰራ እናሳምነው።

አንድ ሌሊት ሌሊት በአንድ ጋራጅ ውስጥ በጥበቃ ሥራ የሚተዳደሩ አዛውንት ከሠፈራቸው ርቀው ሄደው ቀን ቀን ሲለምኑ የሚያውቃቸው ሰው አገኛቸውና " ምነው አቶ አክሌ አረ ባባጃሌው ምነካምት ሙሉ አካል ይዘው ሥራ እያለወት ይለምናሉ" ቢላቸው " ጌታዬ አሁን ኑሮ ውድ ነው በአንድ ሥራ ብቻ ረክቶ መቀመጥ ደግሞ አላዋጣም ብለውት አረፉ።" ሌላ ሥራ ለመስራት ማሰባቸው ጥሩ ነበር፡ ነገር ግን ምነው በልመና ባያደርጉት ፡ ምናልባት እሳቸውም "ፈረንጅ ፈረንጅ መኒ" እያሉ አድገው ይሆን? እስቲ በልመና የታወረው አዕምሮአችንና

ልባችን ይቀየር።ልመናና ኢትዮጵያዊነት እኮ አብሮ አይሄድም። የኮራች፤ የታፈረችና፤ የተከበረች ምድር ነው አባቶቻችን ያስረከቡን። እኛም አሞተ ኮስታሮች ሆነን በላቤ ጥሬ ግሬ እኖራለሁ እግዚአብሔርም ይረዳኛል በሚል አዲስ መንፈስ ልመናን ተቃውመን ዛሬ እንነሣ። ያን ጊዜ አስደሳች ለውጥና እርካታ እናገኛለን። ያን ጊዜ አገራችን ኢትዮጵያ ከዳቦ ቅርጫ ወጥታ የዳቦ ቅርጫት ትሆናለች። ልመናም ተረት ይሆናል።

አገር የጋራ ነው

ድህነት የግል ነው!

ምዕራፍ 17

ኢትዮጵያችን የዳቦ ቅርጫት የምትሆነው ሚዛኑን የጠበቀ የሥራ አመለካከት ሲኖረን ነው።

ሥራ ሥራ እያልን በምድራዊ ነገር ብቻ ተይዘን ደግሞ የሰማያዊውን ማለት የነፍሳችንን ጉዳይ እንዳንረሣ እስቲ ሚዛኑን የጠበቀ ኑሮ እንኑር። እስከአሁን ሁላችንም ለራሳችንና ለአገራችን እድገት ሥራ እንድንሰራ በእጅጉ ሳበረታታችሁ ቆይቸአለሁ። አሁን ደግሞ ከሥራ ወደ እረፍት እንድንመለስ አስገንዝቤአችሁ ላጠቃልል ነው። ሥራ ሥራ እያልን ሙልጭ ብለን ከእግዚአብሔር እንዳንርቅ በእጅጉ ስለ ሕይወታችን ልናስብና የሰው ሕይወት በሥራው ሳይሆን ክርስቶስ በመስቀል ላይ በሰራው ሥራ ብቻ እንደሚድን አውቀንና አምነን ወደነፍሳችን ጠባቂ ልንመለስ ይጋባናል።

"ከሥነ ፍጥረት ታሪክ እንደምንረዳው፣ የፍጥረት ግብ ፈጣሪን ማሰብ ነው። ማለትም ሁለመናችንን ለሥራ ሰጥተን ፈጣሪያችንን እንድንረሳ አይደለም። መሥራት እንዳለ ሁሉ ከፈጣሪም ጋር ጎብረት አለ። ሰውን ሰው ያሰኘው ማርክሳውያኑ እንደሚሉት ሥራው ሳይሆን፣ አምልኮው ነው። እውነተኛ ደስታና እርካታ ብዙ በሠራን ጊዜ ብቻ ሳይሆን ከአምላካችንና ከፈጣሪያችን ጋር ብዙ በተራከብን /ጎብረት ባደረግን/ ጊዜ ነው። ምክንያቱም የሕይወት ግብ እግዚአብሔር እንጂ ሥራ አይደለም። ሥራ የራሱ የሆነ አምላካዊ ግብ ቢኖረውም መላ

ነገራችንን ግን ከእግዚአብሔር ሊነጥለው አይገባም። ሰባኪው እንዳለው *"ሁሉ ነገር ከንቱ ነው፣ እንዲያውም የከንቱ ከንቱ ነው"* /መክብብ 1:1 ለዚህ ሰባኪ "ከፀሐይ በታች" /ማለትም ያለ እግዚአብሔር ሁሉም ነገር ከንቱ ነው። ለእኛም ሆነ ለሥራችን ትርጉም የሚሰጠው እግዚአብሔር ነውና። ሕይወት ያለ እግዚአብሔር ትርጉም የላትምና።

የሥነ ፍጥረት ታሪክ ሥራን ከዕረፍት እንዳናፋታ ወይም እንዳንለያይ ያስጠነቅቀናል። ሥራ በእግዚአብሔር የተፈጠርንበትን ዓላማ እውን ሲያደርግ፣ ዕረፍት ደግሞ በእግዚአብሔር ሥራ ደስ እንድንሰኝ ያደርጋል። በዚህ ዓለም የእግዚአብሔርን ሥራ ማድነቅ የሚችለው ሰው ብቻ ነው። ሥራ አምላካዊ በረከት እንደሆነ ሁሉ፣ ዕረፍትም አምላካዊ በረከት ነው። የሚሠሩ ሰዎች ማረፍ አለባቸው። ምክንያቱም የመጀመሪያው ሠራተኛ፣ እርሱ ራሱ ከሥራው አርፏልና። *"እግዚአብሔርም የሠራውን ሥራ ሁሉ በሰባተኛው ቀን ፈጸመ። በሰባተኛውም ቀን ከሥራው ሁሉ ዐረፈ። እግዚአብሔርም ሰባተኛውን ቀን ባረከው፤ ቀደሰውም፤ እግዚአብሔር ሊያደርገው ከፈጠረው ሥራ ሁሉ በእርሱ አርፎምአልና"* /ዘፍ 2፣ 2-3/። እግዚአብሔር የሰንበትን ቀን ለሰዎች የሰጠው ፍቅሩን ለመግለጽ ነው። ይህ ዓለም ለእርሱ ውድ ዓለም ነው። እርሱ ለዚህ ዓለም ያስባል። ለዓለሙም መልካም የሆነውን ያደርጋል።

እግዚአብሔር ሰንበትን የሰጠን ከሥራችን እንድናርፍ ነው። እግዚአብሔር ከሥራው ሁሉ ያረፈው ስለ ደከመው አይደለም። ሥራውን ስለጨረሰ ነው። የእኛም ዕረፍት ይህን ምሳሌ መከተል አለበት። የምናርፈው ሥራችንን ስለጨረስን ነው፤ አሁን

የሠራነውን መለስ ብለን የምንመለከትበትና በሠራነውም ደስ የምንሰኝበት ነው። እግዚአብሔር ሰባተኛውን ቀን ያሳለፈው በድካም ሳይሆን በመንፈስ እርካታ ነው። ደግሞም እግዚአብሔር ሰንበትን የሰጠን በእርሱ እንድናርፍ ነው። በእርሱ መታመንን የምንማረው በእርሱ ስናርፍ ነው። እስራኤልም በሰባተኛው ቀን እንድታርፍ የታዘዘችው በዚህ አምላክ መታመንን እንድትማር ነው። ያኔም ሆነ አሁን ሕይወት በእኛ ጥረት የተመሰረተች አይደለችም። እኛ ካልሠራን ሕይወት ብን ብላ አትጠፋም። ምክንያቱም ሕይወት ስጦታ ናት። በሚያሳርፈው ታምኖ ማረፍ ተገቢ ነው፡ እርሱ ታማኝ ነውና። እንዲሁም እግዚአብሔር ሰንበትን የሰጠን ሁላችንም በእርሱ ፊት እኩል መሆናችንን ሊያሳየን ነው።

ሰንበት ለሰው ልጆች ሁሉ /ለሀብታሙም ሆነ ለደኻውም/ የተሰጠ በረከት ነው።

እግዚአብሔር የመጀመሪያው ሠራተኛ ነው። ሥራውም ሙሉ ነው። ከፍቅሩ የተነሣ ዓለምንና ሰውን ፈጠረ። ከፍቅሩም የተነሣ ሰንበትን ለሰው ልጆች ሰጠ። ሰንበት ስለ እግዚአብሔር ማንነት የሚያስተምረን አንድ ብርቱ ነገር አለው። ይኸውም እግዚአብሔር የሚያርፍና የሚያሳርፍ አምላክ ነው። እንደ ባቢሎናዊያን አማልክት ዘመኑን ሳምንቱንና ቀኑን ሁሉ በስጋት አያሳልፍም። የሰው ልጆች ጉድ ይሰሩኝ ይሆን ብሎ ሲጨነቅ አይውልም። በሰንበት ቀን ስናርፍ እግዚአብሔርን አንተ ጌታ ነህ ማለትም መጋቤ ኩሉ ነህ በማለት እያወጅን ነው። በሰንበት ቀን ከሥራችን ሁሉ እናርፋለን፤ ምክንያቱም ተስፋችን ሥራችን ሳይሆን እግዚአብሔር ነውና። እንግዲህ በሰንበት ቀን አለማረፍ

በሥርዐቱ ፈጣሪ ማለትም ሥርዐቱን ባቆመው አለማረፍ ነው። ደግሞም ሰንበትን አለማክበር የሥርዐቱን ፈጣሪ አለማክበር ነው፡ ለሕይወታችን ትርጉም የሚሰጠው ሥራ ሳይሆን እግዚአብሔር ነውና።

እዚህ ላይ አንድ በአግባቡ ሊጤን የሚገባው ነገር እንዳለ ለማሳሰብ እንወዳለን። ይኸውም ሥራ ክቡር ተግባር ቢሆንም፣ ዝንተ ዓለማችንን በሥራ ተጠምደን ትልቁን ነገር እንድንረሳ የእግዚአብሔር ፈቃድ አይደለም። አንድ ወዳጄ ከአንድ አዛውንት የሰማሁት ተረት ነው ብሎ ያጫወተኝ ቁም ነገር አሁን ላነሣነው፣ ጥሩ ምሳሌ ሊሆነን ይችላል፡- "ዓሳማ በእድሜዋ ዘመን ሁሉ ሰማይን የምታየው አንድ ቀን ብቻ ነው አሉ፣ ልትታረድ ገልበጥ ስትደረግ። ከእርሷ በላይ ሌላ የተለየ ዓለም እንዳለ የምታሰተውለው፣ በዚያች ቢለዋው ካንገቷ በሚገናኝበት ቅጽበት ነው። ታዲያ ምን ያደርጋል፣ከቶ መመለስ ወደማትችልበት ዓለም ስለ ሄደች ያስተዋለችውን አዲስ ዓለም ለማየት ጊዜው አልፎባታል። ዓሳማዋ ዘመኗን ሁሉ ያሳለፈችው ምድር ምድሯን (ምግቧ ምግቧን) ስትል ነው። ለምግቧ እንጂ በዙሪያዋ ስላለው ዓለም ደንታ አልነበራትም። ወደ ታች ብቻ እንጂ ወደ ላይ ሌላ ዓለም ያለ አልመሰላትም።ራስ ራሷን ስታይ ሰማዩ ተከደነ። ሰወች የተፈጠሩት ወደ ታች እያዩ ወደ ታች እንዲቀሩ አይደለም። ወደ ታችም ወደ ላይም እንዲያዩና የምድር ሥራቸውን ለሰማዩ አምላካቸው ክብር እንዲያውሉት ነው። ኑሮአቸውንም ከፈጣሪያቸው ጋር እንዲያዛምዱት ነው። ምክንያቱም የለፋንበት ሁሉ ያለ እግዚአብሔር ከንቱ ነው። እዚሁም ይቀራል፣ እግዚአብሔር ብቻ ነው የመጨረሻው

ተስፋችን። [18]

"ሰባኪው " በዚህ ምድር ላይ ትልቅ ሀብት ሊኖረን ይችል ይሆናል፣ ዝናችንም በዓለም የታወቀ ይሆናል። በዚህ ሁሉ ግን ክርስቶስ ከሌለን ከንቱዎች ነን፣ ምክንያቱም ሀብትም፣ ዝናም ክብርም፣ በዚህ ይቀራሉ። ክርስቶስ ግን የዘላለም ነው። ዛሬ የምንመካበት ትልቁ ሀብታችን ብርና ወርቅ ሳይሆን ጌታ ኢየሱስ ብቻ መሆን አለበት።" የሚለውን ትምህርቱን ለአድማጮች ለማስገንዘብ ይህንን ምሳሌ ተጠቀመ።

"አንድ ማዳበሪያ በመነገድ የታወቀ ሀብታም ሰው ነበር። አንድ ወቅት ላይ ግን ድርጅቱ በእሳት ወደመ። ሰውየውም ከዚህ የተነሣ አበደና በከተማ መዞር ጀመረ፣ አንድ ወንጌላዊ አገኘውና ፀለየለት። ስለ ጌታም መሰከረለትና አእምሮውም ልቡም ተፈወሰ፣ ልብስ ለብሶ ጌታን በደህና መከተል ጀመረ። አንደገና ከጥቂት ዓመታት በኋላ የሚከታተለው ወንጌላዊ ጨው መነገድ እንዳለበት መከረውና ከአንዳንድ ወገኖቹ ተበድሮ የጨው ንግድ ጀመረ፣ ተሳካለትም። ዕዳውንም ከፍሎ ከጨረሰ በኋላ እንደገና አንድ ቀን የውኃ ሙላት መጣና የጨውን መጋዘን ባዶ አስቀረው። በዚህ ጊዜ ይህንን አደጋ ወንጌላዊው ሰማ እንዲህም አለ "በቃ ባለፈው ማዳበሪያው በእሳት ሲበላ አብዶ ነበር አሁን ራሱን ይሰቅላል፣ ለማንኛውም ቶሎ ልሂድና ልየው!" ብሎ ሲሄድ ሳያብድና ራሱን ሳይገድል ነገር ግን ልብሱን እንደለበሰ የመጋዘኑ ትንሽ የውስጥ ቢሮ ውስጥ ቁጭ ብሎ መጽሐፍ ቅዱሱን ያነባል። ወንጌላዊው አንኳኩቶ ከገባ በኋላ " ደህና ነህ ወይ?" እያለ ወተወተው። እርሱም " አዎን ደህና ነኝ ማዳበሪያውን እሳት በላው ጨውንም ውኃ ወሰደው ኢየሱስ ግን

[18] ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር ሚኒሊክ አስፋው ገጽ 57-59

ከእኔ ጋር አለ።" አለው። አሜን


"በላይ ያለውን አስቡ እንጂ በምድር ያለውን አይደለም።" /ቆላ. 3:6/።

አም ትልቁ የሰው ልጅ ሀብት ብልና ዝገት የማይበላው፣ የማይከዳና የማይጠፋ ክርስቶስ ብቻ ነውና ።" ቃሉም እንደሚል *" እኛ አገራችን በሰማይ ነውና ከዚያም ደግሞ የሚመጣ መድኃኒት እርሱንም ጌታን ኢየሱስ ክርስቶስን እንጠባበቃለን።"*

ቀሪውን የሕይወታችንን ዘመን በምድር ለእርሱ ክብር እየሰራን ለነፍሳችን ደግሞ ጌታ በሰራው ስራ እያመንን ከእርሱ ጋር በእርሱ ጉያ ሆነን እንድናሳልፍ መድኃኒዓለም ይርዳን።


እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይባርክ !! አሜን !

ወንጌላዊ ደመወዝ አበበ የአገር እድገት የሚመጣው ሥራ በመሥራት እንደ ሆነ በዚህ አነስተኛ መጽሐፍ ማቅረቡ አብዛኛው ሕዝበ ክርስቲያንና የአገራችን ሕዝብ ስለ ሥራና እድገት ካለው የተዛባ አመለካከት ነጻ ለማውጣት የሚደረገውን ጥረት የሚያመለክትና የወንድማችን አገልግሎት ለሁለንተናዊ ለውጥ ምሳሌ መሆኑን የሚያሳይ ነው። ይህ የወ/ዊ ደመወዝ ዓይን ከፋች መጽሐፍ፣ ከመጽሐፍ ቅዱሳዊው የሥራ ሥነ ምግባርና ከአገር እድገት አንጻር ቀጣይነት ባለው መንገድ በመድረኮቻችን ለማስተማርና ለአንባቢያን ጽሑፍ ለማቅረብ ሰፊና ጠለቅ ያለ ዝግጅት እንደሚያስፈልግ ጠቋሚ እንደሆነ አስባለሁ።



አቶ ቴዎድሮስ በየነ

ከመሠረተ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን



ማጠቃለያ

እንግዲህ ሥራ - ሥራ ኢትዮጵያ የዳቦ ቅርጫት ትሆናለች የሚለውን ይህንን መጽሐፌን የማጠቃልለው የመጽሐፉን አጠቃላይ ጎላብ ለአንባቢዎቼ <u>እንደገና እንደሚከተለው በማስታወስ ነው</u>።

- ኢትዮጵያችን የዳቦ ቅርጫት የምትሆነው መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነውን የሥራ ሥነ ምግባር መርሆ ስንከተል ነው።
- ኢትዮጵያችን የዳቦ ቅርጫት የምትሆነው ሥራን ላንጋት ሥንሠራ ነው።
- ኢትዮጵያችን የዳቦ ቅርጫት የምትሆነው <u>ስንፍናን</u> ከሕይወታችን ስናስወግድ ነው።
- ኢትዮጵያችን የዳቦ ቅርጫት የምትሆነው የተዛባ ኃይማኖታዊ የሥራ አመለካከታችን ስንተው ነው።
- ኢትዮጵያችን የዳቦ ቅርጫት የምትሆነው ባቋራጭ መክበርን ሥናቆም ነው፡
- ኢትዮጵያችን የዳቦ ቅርጫት የምትሆነው የተዛባ የሥራ አመለካከታችንን ስንተው ነው።
- ኢትዮጵያችን የዳቦ ቅርጫት የምትሆነው ወላጆች ልጆቻቸውን ለሥራ ማነሳሳት ሲችሉ ነው።
- ኢትዮጵያችን የዳቦ ቅርጫት የምትሆነው ቤተክርስቲያን ምዕመናኗን ለስራ ስታነሣሣ ነው።

ሥራ ... ሥራ ... በአገርህም ኩራ!

- ኢትዮጵያችን የዳቦ ቅርጫት የምትሆነው መንግስት ሠራተኞችን ለበለጠ ሥራ ሲያበረታታ ነው።
- ኢትዮጵያችን የዳቦ ቅርጫት የምትሆነው የቁጠባ ባህላችን የበለጠ ሲዳብር ነው።
- ኢትዮጵያችን የዳቦ ቅርጫት የምትሆነው በአንድ ሥራ ረክተን መቀመጣችንን ሥናቆም ነው።
- ኢትዮጵያችን የዳቦ ቅርጫት የምትሆነው ጥሬ ኃ
- ብታችንን በትክክል መጠቀም ስንችል ነው።
- ኢትዮጵያችን የዳቦ ቅርጫት የምትሆነው አላስፈላጊ ጦርነቶች ውስጥ መግባትን ስናቆም ነው።
- ኢትዮጵያችን የዳቦ ቅርጫት የምትሆነው ውጭ አገር በመሔድ ብቻ ሳይሆን በአገራችንም ጌታ እንደሚባርከን ስናምን ነው።
- ኢትዮጵያችን የዳቦ ቅርጫት የምትሆነው ጊዜያችንን በአግባቡ መጠቀም ስንችል ነው።
- ኢትዮጵያችን የዳቦ ቅርጫት የምትሆነው በልመና ለመኖር ማሰባችንን ስናቆም ነው።
- ኢትዮጵያችን የዳቦ ቅርጫት የምትሆነው ሚዛኑን የጠበቀ የሥራ አመለካት ሲኖረን ነው።

በዚህ አድራሻ ያገኙናል: 0911404554

ከዚህ ቀደም የታተሙ መጻሕፍት

1. የሰባኪው ምሳሌ፣ አንደኛ መጽሐፍ
2. የሰባኪው ምሳሌ፣ ሁለተኛ መጽሐፍ
3. ሁለት ጉልቻ

ወደፊት የሚታተሙ መጻሕፍት

1. ሦስት ጉልቻ
2. የአገልጋዩ የግል ሕይወት ምስክርነት
3. አስደናቂ አባባሎች
4. የሰባኪው ምሳሌ፣ ሦስተኛ መጽሐፍ

ልዩ ማስታወሻ

ወ/ሮ ደመወዝ አበበ እና ባለቤታቸው ወ/ሮ የሺወርቅ ሺመልስ ከዘጠኝ ዓመት በፊት ጀምሮ የምድር ጨው መጽሐፍ ቅዱሳዊ የማማከር አገልግሎት ሥር በደብዳቤ፣በአካል፣ በራዲዮ፣ እንዲሁም በኢንተርኔት ምክር ሲሰጡ ቆይተዋል።አሁንም ይህንኑ አገልግሎት በምድሪቱ ላይ በስፋት በመስጠት ላይ ይገኛሉ። በጋብቻ ትምህርት ላይም በሲዲ በካሴት እና በመጽሐፍ አዘጋጅተው እያገለገሉ ይገኛሉ። አሁንም ይህንን <u>ሥራ ሥራ</u> የሚለውን መጽሐፋቸውን ጨምሮ ምክር ስልጠናና ትምርት የሚሰጡባቸውን የተለያዩ ቁሳ ቁሶች (ማቴሪያሎች) ያዘጋጁ ስለሆነ ጌታና ጊዜ በፈቀደ ሁሉ ከዚህ በታች ያሉትን የአገልግሎት ክፍሎች ሁሉ በእነዚህ ርዕሶች ለማገልገል ተዘጋጅተዋል።

1. ለቤተክርስቲያን መሪ አገልጋዮች / የተቀናጀና የተደራጀ ስልታዊ አመራር /
2. ለመጋቢያን ለቄሶች እና ለወንጌላዊያን /የገላጭ ስብከት አዘገጃጀት ዘዴ እና የአቀራረብ ስልቱ /
3. ላላገቡ ወጣቶች ሁሉ / ቅድስናና ክርስትና፣ሥራና ቅድመ-ጋብቻ /
4. ለመዘምራን/ ዘመናዊነት እና መንፈሳዊነት፣መሰጠትና የአገልግሎት ምንነት /
5. ለኮምፓሽን ታዳጊ ወጣቶች/ የህይወት ግብና ዓላማ. ሥራ ፣ ጸታዊ ጥያቄዎች እና ኢትዮጵያነት /
6. ላገቡ ባለትዳሮች ሁሉ / ምሳሌነት ያለው የክርስቲያን ቤት እና

ቤተክርስቲያን /

7. ለወርልድ ቪዥን ስታፍ /ሥራ ትዳር የቲም ወርክ መንፈስና አገልግሎት /
8. ለወንጌል ስርጭት ክፍሎች / የሰመረና የሰከነ የወንጌል አሰረጫጨት ክህሎት /
9. ለመድረክ መሪዎች በሙሉ / ተቀባይነትና ተወዳጅነት ያለው የመድረክ አመራር ክህሎት/
10. ለተለያዩ የክርስቲያን በጎ አድራጎት ድርጅት ለሰራተኞች / የአገልግሎት ዋጋው፣ አብሮ የመስራት ጥበብ እና ትዳር /

ዋቢ መጻሕፍት

መጽሐፍ ቅዱስ (1954) እና (1980) ዓ.ም

ሚኒሊክ አስፋው ክርስቲያናዊ ስነ ምግባር አ.አ 1999 ዓ.ም

የብልጽግና ቁልፍ አ.አ 1999 ዓ.ም

ወ/ሮ ደመወዝ አበበ የሰባኪው ምሳሌ -አንደኛ መጽሐፍ. አ.አ 1994 ዓ.ም

በዶ/ር ተሰማ አቤት ውሸት አ.አ

ዶ/ር ወሮታው በዛብህ ኢንተርፐረነርሽፕ አ.አ 1998 ዓ.ም

የቤተክርስቲያን ሁለንተናዊ ተሐድሶ በ21ኛው ክ/ዘመን. በኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤ/ክ መንፈሳዊ አገልግሎት ዘርፍ የተዘጋጀ ገጽ 124-125 1998 ዓ.ም

ጉልበት እንደዋዛ አ.አ 1997 ዓ.ም

ከመሰረተ ክርስቶስ ቤ/ክን ት/ት ዝግት ክፍል የተወሰደ ጽሑፍ 1997 ዓ.ም

ምህረቱ ጴ.ጉታ የንባብ ባህል አ.አ 1999 ዓ.ም

ቴዎድሮስ በየነ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሥራ ምን ያስተምራል ለስልጠና የተዘጋጀ ጽሑፍ አ.አ 2000 ዓ.ም

Jerry and Marry White /1989/ On the Job.
Zondervan Corporation, USA

Ben Patterson (1994) Work and Worship.
Inter Varsity press, USA

Ryken (1987) Work and Leisure in Christian Perspective.
Portland Oregon, USA

Doug Sherman and William Hendricks (1987) Your Work Matters to God.
Zondervan Bible publisher, USA